# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሐሙስ

83ኛ ዓመት ቁጥር 073 ኅዳር 13 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# በጉባኤው የኢትዮጵያን ውጤታማ ሥራዎች ማሳወቅ ተችሏል



አቶ ማሞ ምሕረቱ

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እና ልዑካቸው በጀርመን በተካሄደው ጉባኤና ከተለያዩ ሀገራት መሪዎች ጋር በተደረጉ ውይይቶች የኢትዮጵያን አህጉራዊ፣ ቀጣናዊና ሀገራዊ ውጤታማ ሥራዎችን ማሳወቅ እንደተቻለ የብሔራዊ ባንክ ገዢ አቶ ማሞ ምሕረቱ ተናገሩ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በጀርመን በተካሄደው የኮምፓክት ዊዝ አፍሪካ ጉባኤና በተጓዳኝ ስብሰባዎች ያደረጉትን ተሳትፎ በተመለከተ የብሔራዊ ባንክ ገዢ አቶ ማሞ ምሕረቱ በሰጡት ማብራሪያ፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በጉባኤው ባደረጉት ንግግር የኢትዮጵያን የኢኮኖሚ ልማትንና የአየር ንብረት ለውጥ ሥራዎች በተመለከተ እንዲሁም መንግሥት በሀገራዊ፣ በአህጉራዊና በቀጣናዊና ጉዳዮች ላይ እየሠራቸው ያሉትን ሥራዎች ማሳወቅ ተችሏል ብለዋል፡፡

መድረኩ ከተለያዩ ሀገር መሪዎች፣ ከተለያዩ የፋይናንስ ተቋማት መሪዎችና በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለውን ጂኦፖለቲካ ለመገምገምና

በጉባኤው የኢትዮጵያን... ወደ ገጽ 6 ዞሯል










# የባሕር በር ለምን የሕልውና ጉዳይ ሆነ?

**አዲሱ ገረመው**

ኢትዮጵያ ፍትሐዊ የዓለም አቀፍ ንግድ መከወኛ የባሕር በር የማግኘት መብቷ እንዲረጋገጥ በኢትዮጵያውያን ዘንድ መወያያ አጀንዳ ሆኗል፡፡ በአሁን ወቅት የተነሳው የኢትዮጵያ የባሕር በር ጥያቄ ለምን የሕልውና ጉዳይ ተደርጎ ተቆጠረ?

ጸሐፊና የታሪክ አጥኚው ተሾመ ብርሃኑ "የቀይ ባሕር ጂኦ ፖለቲካዊ ሁኔታ ልዩ ትኩረት በአፋር ሦስት ማዕዘናዊ አቀማመጥ" በሚለው ጽሑፋቸው፤ በሦስተኛውና በአራተኛው ክፍለ ዘመን ከክርስቶስ ልደት በኋላ የአክሱም አፄያዊ መንግሥት ግዛቱን እስከ ደቡባዊ ምዕራብ ድረስ አስፋፍቶ እንደነበር፤ በዚህም ዘመን "አይላ" ወይም "አዩላስት" የተባሉት ግዛቶች በዚያኔው የአክሱም መንግሥት ሥር እንደነበሩ፤ የሪቻርድ በርተንን

የባሕር በር... ወደ ገጽ 6 ዞሯል



## በቀይ ባሕር አካባቢ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ኢትዮጵያን ያገለሉ መሆን የለባቸውም

ገጽ 6

# የቀድሞ ታጣቂዎችን መልሶ ለማቋቋም 850 ሚሊዮን ዶላር ያስፈልጋል

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- የቀድሞ ታጣቂዎችን መልሶ ለማቋቋም 850 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር እንደሚያስፈልግ ብሔራዊ ተሐድሶ ኮሚሽን ገለጸ።

የብሔራዊ ተሐድሶ ኮሚሽን የኮሙኒኬሽንና ዓለምአቀፍ ትብብር ዳይሬክተር አቶ ልዑልሰገድ በላይነህ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በስምንት ክልሎች 371 ሺህ 971 የቀድሞ ታጣቂዎች አሉ። እነዚህን የቀድሞ ታጣቂዎች መልሶ ለማቋቋም 850 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ያስፈልጋል።

በመጀመሪያው ዓመት 50ሺ ከትግራይ እንዲሁም 25ሺህ ከሌሎች ክልሎች በአጠቃላይ 75 ሺህ የቀድሞ ታጣቂዎችን መልሶ ለማደራጀት ዕቅድ ተይዞ እንደነበረ የተናገሩት ዳይሬክተሩ፤ ዕቅዱን ለማሳካት የገንዘብ ችግር አጋጥሟል ብለዋል።

እንደ አቶ ልዑልሰገድ ገለጻ፤ እቅዱን ዝቅ በማድረግ 50 ሺ የትግራይ የቀድሞ ታጣቂዎችን መልሶ ለማደራጀት ዕቅድ ቢያዝም ለሥራው የሚያስፈልገውን 162 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ማግኘት ባለመቻሉ ኮሚሽኑ ዕቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ መቸገሩን ገልጸዋል። የሚፈለገው ገንዘብ የሚገኝ ከሆነ በመጪው ጥር ወር ዕቅዱ

የቀድሞ ታጣቂዎችን... ወደ ገጽ 6ዞሯል



አቶ ልዑልሰገድ በላይነህ







# በተገልጋዮች የተወደሰው የመሬት አስተዳደር ኤጀንሲ

**ቃልኪዳን አሳዬ**

በመዲናዋ የሚነሱ የመሬት ይዞታ ጉዳይ ክርክሮች ለዘመናት የመልካም አስተዳደር ጥያቄ መነሻ እንደነበሩ የሚታወስ ነው።

በተለያዩ ወቅቶች በመሬት ይዞታቸው ላይ ለሚነሱ ክርክሮች መፍትሔ ለማግኘት ወራትን አለፍ ሲልም ዓመታትን የሚጠብቁ ዜጎች አገልግሎቱን በሚሰጠው ተቋም አማካኝነት ምሬት ውስጥ ገብተው እንደነበር በተደጋጋሚ ጊዜያት ሲገለጽ ቆይቷል።

በአሁኑ ጊዜ ደግሞ በመሬት ይዞታ ጉዳይ የሚነሱ ችግሮችን መፍትሔ ለመስጠት የሚደረገው ጥረት መሻሻሉንና አሠራሩ ቀልጣፋ መሆኑን የተለያዩ ተገልጋዮች ይገልጻሉ።

በመሬት ይዞታቸው ላይ ቅሬታ ይዘው ወደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ያቀኑት አቶ ውብሸት ጀምበር፤ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ጥያቄያቸውን በፍጥነት ምላሽ አግኝቶ ለተጨማሪ አገልግሎት ወደ ክፍለ ከተማቸው መመለሳቸውን አስረድተዋል።

በወቅቱ በመልካም ሥነምግባርና ፈጣን አገልግሎት የተቀበሏቸው የኤጀንሲው ሠራተኞች መሆናቸው አስታውሰዋል፡፡

የአገልግሎት አሰጣጡ ምቹና ቀልጣፋ በመሆኑ የመልካም አስተዳደር ችግር አያስነሳም ያሉት አቶ ውብሸት፤ ፈጣን አገልግሎት አሰጣጡ በተለያዩ ተቋማትም ሊስፋፋ ይገባል ሲሉ ሃሳባቸውን ሰጥተዋል።

ወደ ኤጀንሲው ከመምጣታቸው በፊት የሚፈልጉትን አገልግሎት በፍጥነት አላገኝም የሚል ስጋት በውስጣቸው እንደነበር የገለጹት ደግሞ የአዲስ አበባ ነዋሪዋ ወይዘሮ እሙዬ መላኩ ናቸው።

የመሬት ይዞታ ክሊራንስ ለመቀበል ወደ ኤጀንሲው ያቀኑት ወይዘሮ እሙዬ፤ አገልግሎቱን በአጭር ጊዜ



አቶ ውብሸት ጀምበር፤



ወይዘር እሙዬ መላኩ



አቶ ግፋወሰን ደሲሳ

ውስጥ በማግኘቴ ከፍተኛ ደስታ ተሰምቶኛል ብለዋል።

ወደ ማዕከሉ ከመጡ በኋላ ስጋታቸው ተቀርፎ ሳይጉላሉ አገልግሎቱን ማግኘት በመቻሌ፤ ቀሪውን ጊዜዬን ለምፈልገው ሥራ ማዋል የምችልበት ዕድል አግኝቻለሁ ያሉት ተገልጋይዋ፤ ለተሰጠኝ አገልግሎት ምስጋና አቅርቤ ወጥቻለሁ፤ ይህ ሊለመድ የሚገባው ቀልጣፋ አሠራር ነው ሲሉ አስተያየታቸው ሰጥተዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ በበኩሉ፤ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በመቅረፍ ረገድ ውጤታማ ሥራ እያከናወነ መሆኑን ይገልጻል።

ከኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር ጀምሮ ታችኛው እርከን ድረስ የሚገኙ ሠራተኞች መመሪያን ተከትለው የሚሠሩ መሆናቸውንና የቀድሞ ብልሹ አሠራሮችን በማደስ የተሻለ ሥራ እያከናወኑ እንደሚገኝ በአካል ተግኝቼ ተረድቻለሁ ይላሉ።

የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር አቶ ግፋወሰን ደሲሳ፤ በመሬት ይዞታ ላይ የሚነሱ ክርክሮች በአብዛኛው በኤጀንሲው አሠራር ሂደት የሚነሱ የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች እንደሚሆኑ ለኢፕድ አስረድተዋል።

በ2016 በጀት ሩብ ዓመቱ ወደኤጀንሲው ለመጡ 15 ሺህ የመሬት ይዞታ ክርክር መዝገቦች መፍትሔ በመስጠት የመልካም አስተዳደር ችግሮች እንዲቀንሱ መደረጉን ነው ያስታወቁት።

በተጨማሪ 25 ሺህ የተለያየ ይዞታ ያላቸው የመሬት ባለቤትነት ጥያቄዎች ላይ መፍትሔ ለመስጠት ጥረት እየተደረገ መሆኑን ያመላክታሉ።

እንደ አቶ ግፋወሰን ከሆነ፤ ዜጎች በካርታው ላይ ከተመዘገበላቸው የተለየ የመሬት ይዞታ ካላቸው ጉዳዩ ተጨማሪ ምርመራን ይጠይቃል፤ በመሆኑም በክርክር መዝገብ ተይዞ መፍትሔ እንዲገኝለት ይደረጋል።

ወደኤጀንሲው የሚመጡ የመሬት ይዞታ ክርክሮች ውሳኔ እንዲያገኙ በማድረግ ለመሬት ባለቤቶቹ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት እንደሚሰጥ አስገንዝበዋል።

ተቋሙ በመሬት ጉዳይ የመልካም አስተዳደር ችግሮች እንዳይከሰቱ የተለያዩ የአሠራር ሥርዓቶችን ዘርግቶ እየሠራ ሲሆን፤ የሪል እስቴት ካዳስተር ሥርዓት አንዱ የመፍትሔ አሠራር ሆኖ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል ይላሉ።

የሪል እስቴት ካዳስተር ሥርዓት የመሬት መረጃን በካርታ ላይ ሰብስቦ ወደዘመናዊ ሥርዓት የሚገባበትና ስለይዞታው ባለቤቱ መብት፣ የሕግ ክልከላና ኃላፊነት የሚያስረዳ የተደራጀ የቁጥጥር ሥርዓት መሆኑን ነው የሚገልጹት።

ወደተቋሙ የሚመጡ የመሬት ጉዳይ የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች መፍትሔ እንዲያገኙ ከአዲስ አበባ የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ ጋር በቅንጅት እየተሠራ መሆኑን ይጠቁማሉ።

ኤጀንሲው 24 አይነቶችን የአገልግሎቶችን እየሰጠ መሆኑን ያስረዱት ዋና ዳይሬክተሩ፤ የአዲስ መሬት ይዞታ ምዝገባ፣ የካዳስተር አገልግሎት፣ የወሰን ክርክር መፍታት፣ የንብረት ዝውውር፣ የወሰን ይዞታ ቅያሪና ሌሎችም አገልግሎቶች በቀልጣፋ መንገድ እየሰጡ መሆኑን ነው ያመላከቱት።



ጫልቱ ሳኒ እና ፍሬሕይወት ታምሩ

# በከተሞች የሚሰጡ አገልግሎቶችን ዲጂታላይዝ ለማድረግ ጥረት እየተደረገ ነው

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- በከተሞች የዜጎችን እንግልት ለማስቀረት በዲጂታላይዜሽን በመታገዝ የተለያዩ አገልግሎቶችን ለመስጠት እየተሠራ መሆኑን የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴርና ኢትዮ ቴሌኮም ሰሞኑን የከተሞች አገልግሎትን ለማዘመን የሚያስችል ስምምነት አድርገዋል።

የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስትር ወይዘሮ ጫልቱ ሳኒ እንደገለጹት፤ የከተሞችን አገልግሎት አሰጣጥ ቀልጣፋ ለማድረግ የቴክኖሎጂ አማራጮችን በመጠቀም ረገድ ሰፊ ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛል።

በከተሞች የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት፣ የመሬትና ከተማ ልማት ቢሮዎች እንዲሁም የተለያዩ ቢሮዎችን አገልግሎቶች በበይነ መረብ ከማከናወን በተጨማሪ ጉልበትና ጊዜ የሚቆጥቡ የዲጂታላይዜሽን አማራጮች እንዲጠናከሩ እየተሠራ ይገኛል ብለዋል።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በከተሞች ላይ የሚሰጡ አጠቃላይ አገልግሎቶችን ለማዘመን እየሠራ መሆኑን ጠቁመው፤ ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር በመተባበር የዘርፉን የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃን ለማሳደግ እየተሠራ መሆኑን አመልክተዋል።

ያልዘመነና በማንዋል የሚሰጥ አገልግሎት በማኅበረሰቡ ላይ ከፍተኛ እንግልት አስከትሏል ያሉት ወይዘሮ ጫልቱ፤ የዘርፉን ችግሮች ለመቅረፍ አገልግሎት አሰጣጡን በቴክኖሎጂ አማራጮች የመደገፍ ሥራ ወሳኝነት አለው ሲሉ አስረድተዋል።

በመግባቢያ ሰነዱ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አሰጣጥን ለማዘመን የሚያስችል መሆኑን ጠቅሰው፤ ዜጎች ግብር ለመክፈል የሚቆዩበትን ጊዜ ለመቆጠብ እንደሚረዳ ገልጸዋል፡፡

ሚኒስቴሩ ከኢትዮ ቴሌኮም ስምምነት በማድረግ የከተሞች ገቢ የተሻለ ለማድረግና የዜጎች የአገልግሎት እርካታ ከፍ ለማድረግ እንደሚሠራ ጠቁመዋል።

በኮንስትራክሽን ዘርፉ የሚስተዋለውን የመረጃ አያያዝ ሥርዓት ማዘመን እንደሚያስፈልግ የገለጹት ሚኒስትሯ፤ በዘርፉ የሚከናወን የዲጂታላይዜሽን አገልግሎት ወጪን ለመቀነስና የሀብት ብክነትን እንደሚያስቀር ተናግረዋል፡፡

የኢትዮ ቴሌኮም ዋና ሥራ አስፈጻሚ ፍሬሕይወት ታምሩ በበኩላቸው፤ ኢትዮ ቴሌኮም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በቴክኖሎጂ የታገዘ ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት የሚያደርገውን ጥረት ይደግፋል ብለዋል፡፡

በዲጂታል ኢትዮጵያ ተቋማት በቴክኖሎጂ ታግዘው ውጤታማ እንዲሆኑ እየተሠራ ነው ሲሉ ሥራ አስፈጻሚዋ ጠቁመዋል።

በተለያዩ ከተሞች የሚገኙ ዜጎች በተንቀሳቃሽ ስልካቸው አማካኝነት የመንግሥት አገልግሎቶችን ማግኘት የሚችሉበት ሥርዓት እንደሚዘረጋ አስታውቀዋል።

የማዘጋጃ ቤቶችና የከተሞች አገልግሎትን ዲጂታላይዝ ማድረግ ለዜጎች ቀልጣፋ አገልግሎትን ለመስጠት እንደሚያስችል በመግለጽ፤ የከተሞችን ገቢ በቀላሉ ለመሰብሰብ የሚያስችል ሥርዓት መሆኑን አስረድተዋል።

የኮንስትራክሽንና መሠረተ ልማት ዘርፎችን በቴክኖሎጂ በመደገፍ በዘርፉ የሚስተዋለውን ወጪ መቀነስ እንደሚያስፈልግ አመልክተው፤ የመረጃ አያያዝ ሥርዓቱን በማዘመን የሀብት ብክነትን የሚያስቀር ነው ብለዋል፡፡

በተጨማሪም ስምምነቱ ከከተሞች የሚሰበሰበውን ክፍያ በቴሌ ብር አማካኝነት ለመሰብሰብ የሚያስችል መሆኑን አስታውቀዋል።

# የኢንዱስትሪዎችን ምርታማነት ለማሳደግ በፋይናንስ ተደራሽነት ላይ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- የአምራች ኢንዱስትሪዎችን ምርታማነትን ለማሳደግ በሰው ኃይል ክህሎትና በፋይናንስ ተደራሽነት ላይ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት እንደሚያስፈልግ ተገለጸ፡፡

በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ላይ በሚስተዋሉ ተግዳሮቶችና የወደፊት አቅጣጫዎች ላይ ያተኮረ የፓናል ውይይት ከትናንት በስቲያ ተካሂዷል፡፡

በመድረኩ የኢፌዲሪ ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋም የአካዳሚክ ጉዳዮች ዳይሬክተር ገነነ አበበ (ዶ/ር) ባቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፍ፤ አምራች ኢንዱስትሪውን ለማንቀሳቀስ የክህሎት አቅምን ማሳደግና ፋይናንስ የሚያገኙበትን ሁኔታ መፍጠር ተገቢ ነው ብለዋል።



ገነነ አበበ (ዶ/ር)

ክህሎትን በማሳደግ ረገድ በቴክኒክና ሙያ ተቋማትና በአምራች ኢንዱስትሪዎች በኩል ያለው ትስስር ዝቅተኛ ነው ያሉት ዶክተር ገነነ፤ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ዘርፉ በኢንዱስትሪው እንዲመራ በሕግ ቢደነገግም ከአፈጻጸም አንጻር ውጤታማነቱ አመርቂ እንዳልሆነ ገልጸዋል፡፡

ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚፈልጉትን የሰው ኃይል ወስደው ለማሠልጠን በቂ አቅም እንደሌላቸው የጠቆሙት ዋና ዳይሬክተሩ፤ አምራች ኢንዱስትሪዎች ከትምህርት ተቋማት ጋር በተመጋጋቢነት በመሥራት የሠለጠነ የሰው ኃይል እጥረታቸውን የሚቀርፉበትን አቅም ማጠናከር እንደሚገባቸውን አስረድተዋል።



ካሊድ አሕመድ (ዶ/ር)

በተጨማሪ ከተግባር ላይ ልምምድ በኋላ ወጣቶች ምን ያህል የተመደቡበትን ተቋም ፍላጎት አሟልተዋል የሚለውን መፈተሽና በኢንዱስትሪዎችና በትምህርት ተቋማት መካከል ዘላቂ ግንኙነት እንዲፈጠር በማድረግ የሠለጠነ የሰው ኃይል እጥረቱን ማቃለል እንደሚቻል ተናግረዋል።

የትላልቅ ሜጋ ፕሮጀክቶች ግንባታ ሂደት፣ የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት ባለሙያዎቻቸውን እንዲለዋወጡ መደረጉ የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማፍራት የሚደረገውን ጥረት እንደሚደግፍ ጠቁመው፤ በጎ ልምዶችን ማጠናከርና ችግሮችን በቅንጅት መፍታት እንደሚገባ አመልክተዋል።

በመድረኩ ጥናት ያቀረቡ ካሊድ አሕመድ (ዶ/ር) በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ከክህሎት ባለፈ ኢንዱስትሪዎች ላይ ያለውን የፋይናንስ ችግር በመቅረፍ ምርታማነታቸውን ማሳደግ ይገባል ብለዋል።

ከሰሃራ በታች ከሚገኙ የአፍሪካ ሀገራት መካከል ለኢንተርፕራይዞች የፋይናንስ አቅርቦትን ተደራሽ ከማድረግ አንጻር ኢትዮጵያ ዝቅተኛ አፈጻጸም ካላቸው ሀገራት ተርታ ትመደባለች ሲሉ አመልክተዋል።

የዓለም ባንክና የተለያዩ ተቋማት ከሚያቀርቡት ብድር ውስጥ በጣም ጥቂት ተቋማት ብቻ የፋይናንስ አቅማቸውን ለማጠናከር የሚያስችል ብድር ያገኛሉ ያሉት ዶክተር ካሊድ፤ የኢንዱስትሪ ምርትን ለማሳደግ በፋይናንስ አቅርቦት ላይ ይበልጥ መሥራት እንደሚገባ ተናግረዋል።

የገንዘብ አቅርቦቱ ማስፋት ካልተቻለ የአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ ይበልጥ እየተዳከመ ይሄዳል ያሉት ጥናት አቅራቢው፤ የፋይናንስ አቅርቦቱን ለማሳደግ ሌሎች የዓለም ሀገራት የሚከተሉትን አሰራር ወደሀገር ውስጥ ማምጣትና ብዙዎችን ተጠቃሚ ማድረግ ይገባል ብለዋል።

የድርጅቶችን ብድር የመመለስ አቅም፣ ግብር የመክፍል ሁኔታ፣ የሠራተኞች ብዛትና የምርት ሂደቶችን በመገምገም ለአምራች ተቋማት አስፈላጊውን ብድር እንዲያገኙ ማድረግ ያስፈልጋል ያሉት ዶክተር ካሊድ፤ በተጨማሪ እንደ ቴሌ ብር ያሉ ዘመናዊ የክፍያና የብድር አማራጮችን አቅም በማሳደግ ችግሩን ለመቅረፍ መሥራት እንደሚገባ አመላከተዋል።



## “ኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል በተገበረችው ልክ ድጋፍ እንድታገኝ ይሠራል”

ነመራ ገበየሁ (ዶ/ር)
- የፕላንና ልማት ሚኒስትር ዴኤታ

ታደሠ ብናልፈው

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ በአየር ንብረት ለውጥ ላይ እየተከተለችና እየተገበረች ያለውን ልማት በማስተዋወቅ ማግኘት የሚገባትን ድጋፍ እንድታገኝ የማድረግ ሥራ እንደሚሠራ የፕላንና ልማት ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

ኢ.አ.አ ከኅዳር 30 እስከ ታኅሳስ 12 ድረስ 2023 28ኛው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የአየር ንብረት ለውጥ ጉባዔ በዓረብ ኤምሬት ይካሄዳል፡፡

ጉባዔውን አስመልክተው በትናንትናው ዕለት ጋዜጣዊ መግለጫ የሰጡት የፕላንና ልማት ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ነመራ ገበየሁ እንደገለጹት፤ የአደጉ ሀገራት በየዓመቱ ለአየር ንብረት ለውጥ ለታዳጊ ሀገራት ሊያደርጉ የገቡትን የ100 ቢሊዮን ዶላር የፋይናንስ ድጋፍ እያደረጉ አይደለም፡፡

ኢትዮጵያም በተመሳሳይ በአየር ንብረት ለውጥ ማግኘት የሚገባትን የፋይናንስ ድጋፍ እያገኘች እንዳልሆነ ጠቅሰው፤ በጉባኤው ላይ ሀገሪቱ በአየር ንብረት ለውጥ ላይ እየተከተለችና እየተገበረች ያለውን ፖሊሲ ማቀፍ፣ ስትራቴጂና እየሠራች ያለውን ልማት በማስተዋወቅ ማግኘት የሚገባትን ድጋፍ እንድታገኝ የማድረግ ሥራ ይሠራል ብለዋል፡፡

የተባበሩት መንግሥታት የአየር ንብረት ለውጥ ጉባዔ በየዓመቱ የሚካሄድ ሲሆን ባለፉት ዓመታት በተካሄዱ ጉባዔዎች ያደጉ ሀገራት በየአየር ንብረት ለውጥ ለታዳጊ ሀገራት የፋይናንስ ድጋፍ ሊያደርጉ ስምምነትና ቃል ገብተው እንደነበር አስታውሰው፤ ነገር ግን የገቡትን ቃልና ያደረጉትን ስምምነት ተግባራዊ እያደረጉ አለመሆኑን ገልጸዋል፡፡

በየአየር ንብረት ለውጥ ብዙ ሀገራት እየተጎዱ ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ጉዳቱንም ለመቀነስና ለመከላከል ሰፋፊ ሥራዎችን እየሠሩ መሆኑን ጠቅሰዋል።

የአየር ንብረት ለውጥን የመከላከል ሥራ ትልቅ የፋይናንስ ድጋፍ የሚጠይቅ በመሆኑ ያደጉ ሀገራት አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርጉ በጉባኤው ግፊት ይደረጋል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት የአየር ንብረት ለውጡን የሚመጥን ግልጽ የሆነ የብድርና የድጋፍ አሰጣጥ ፖሊሲና ስትራቴጂ የላቸውም ሲሉ አብራርተዋል፡፡

የአየር ንብረት ለውጥ የሚያደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ ሀገራት ፕሮጀክት ቀርፀው እንዲተገበሩ ቢደረግም ችግሩን ለመቅረፍ ትኩረት ሰጥተው ለሚሠሩት ሀገራት የፋይናንስና የቴክኖሎጂ ድጋፍ እየተደረገላቸው አለመሆኑን አብራርተዋል፡፡

በአሁኑ ጉባኤ ለታዳጊ ሀገራት ድጋፍ እንዲደረግላቸው የሚያስችል ውይይት ይደረጋል ተብሎ ይገመታል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ዶክተር ነመራ ኢትዮጵያ በአየር ንብረት ለውጥ ላይ የሚጠበቅባትን ግዴታ እየተወጣች ትገኛለች ሲሉ አብራርተዋል፡፡

ከኅዳር 30 እስከ ታኅሳስ 12/2023 በአረብ ኤምሬት የሚካሄደው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ ተግባራዊ ያልተደረጉ፤ የፋይናንስ ድጋፎች፣ የብድር አገልግሎቶችና ድርድሮች ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል ተብሎ ይጠበቃል ሲሉ አመልክተዋል።

# በመዲናዋ ከሁለት ሚሊዮን በላይ ነዋሪዎች የጤና መድን ተጠቃሚ ሆነዋል

ስምስም መንግሥቱ

አዲስ አበባ፤ ከሁለት ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ የከተማዋ ነዋሪዎች የማኅበረሰብ የጤና መድን ተጠቃሚ መሆናቸውን የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ አስታወቀ። በጤናው ዘርፍ ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን ለማስፈን እየሠራ መሆኑን ገልጿል።

የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ዮሐንስ ጫላ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት(ኢፕድ) እንደገለጹት፤ በማኅበረሰብ የጤና መድን ሁለት ሚሊዮን ሁለት ሺህ የሚሆኑ የከተማዋ ማኅበረሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ ሆነዋል። ከእነዚህ ውስጥ ወደ 350 ሺህ የሚሆኑት ከፍለው መታከም የማይችሉ መሆናቸው የከተማ አስተዳደሩ ሙሉ ወጪያቸውን ሸፍኗል።

የከተማ አስተዳደሩ እነዚህ የማኅበረሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ በ2015 በጀት ዓመት 600 ሚሊዮን ብር ለማኅበረሰብ የጤና መድን ድጎማ ማድረጉንና መክፈል ለሚችሉትም የከተማ አስተዳደሩ ለመመዝገቢያ 500 ብር በተጨማሪ መደጎሙን ገልጸዋል።

የማኅበረሰብ ጤና መድን ተጠቃሚዎች በፌዴራልም ሆነ በአዲስ አበባ ከተማ ሥር በሚገኙ የጤና አገልግሎት መስጫዎች በነፃ አገልግሎት ማግኘት እንደሚችሉ የጠቀሱት ዶክተር ዮሐንስ፤ በተያዘው በጀት ዓመትም ማኅበረሰቡ በማኅበረሰብ የጤና መድን ተጠቃሚ እንዲሆን ምዝገባ እየተካሄደ መሆኑን አመልክተዋል።

በከተማዋ የሚስተዋለውን የፍትሐዊ ተጠቃሚነት



ዶክተር ዮሐንስ ጫላ የአዲስ አበባ ከተማ ጤና ቢሮ ኃላፊ፤

ችግር ለመፍታት ጤና ቢሮውና የከተማ አስተዳደሩ በትኩረት እየሠሩ እንደሚገኙም ገልጸዋል።

እንደ ዶክተር ዮሐንስ ገለፃ፤ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥር ብቻ 7 ሆስፒታሎች፣ 101 ጤና ጣቢያዎች አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ። ከእነዚህ በተጨማሪ በፌዴራልና በግል አገልግሎት የሚሰጡ በርካታ የጤና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት አሉ። ይሁን እንጂ ከፍትሐዊነት አንፃር ጥያቄ ያስነሳል።

በከተማ አስተዳደሩ በሚገኙ 119 ወረዳዎች በሁሉም ጤና ጣቢያዎች እንደሌሉ የጠቆሙት ዶክተር ዮሐንስ፤ አገልግሎቱ በሌለባቸው አካባቢ የሚኖሩ የማኅበረሰብ ክፍሎች ወደ ሌላ ወረዳ ለመሄድ ይገደዳሉ ብለዋል።

እንደ ዶክተር ዮሐንስ ማብራሪያ፤ የፍትሐዊነት ጥያቄን ለመመለስ የጤና ተቋማት በሌለባቸው ክፍለ ከተሞች በዚህ ሦስት ዓመታት ግንባታዎች ተከናውነዋል። 400 መኝታ ክፍሎችና የተለያዩ አገልግሎቶችን ያካተተ፣ በግብዓትና በባለሙያ የተደራጀ ምቹና ዘመናዊ ሐያት አካባቢ የተገነባው አበበች ጎበና የእናቶችና ሕፃናት አገልግሎት ይጠቀሳል። በቦታ ርቀት ሲንገላቱ፣ ሆስፒታል ከደረሱ በኋላም ፈጣን አገልግሎት ሳያገኙ ቀርተው ወንበር ላይ እስከ መውለድ የሚደርሱ እናቶችን እንግልትና የሌሎች ሆስፒታሎችንም ጫና በመቀነስ አግዟል።

እያንዳንዳቸው 450 በላይ መኝታ ያላቸው አጠቃላይ ሆስፒታሎች ኮልፌ ቀራኒዮና በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተሞች በመገንባት ላይ እንደሚገኙ ጠቁመው፤ በተለይም በኮልፌቀራኒዮ ክፍለ ከተማ በመገንባት ላይ ያለው ቤቴል ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የሚኖሩ የኅብረተሰብ ክፍሎችና በዙሪያው ላሉ አጎራባች ከተሞች ተደራሽ በማድረግ የነበረባቸውን ችግር ያቃልላል ነው ያሉት።

ሌላው በጤና ዘርፍ ፍትሐዊነትን ለማረጋገጥ ከፍለው መታከም የማይችሉ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ የማኅበረሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ማድረግ እንደሆነ የጠቆሙት ዶክተር ዮሐንስ፤ እነዚህን የማኅበረሰብ ክፍሎች በማኅበረሰብ አቀፍ የጤና መድን አገልግሎት እንዲያገኙ በማድረግ ፍትሐዊነትን ለማረጋገጥ ጥረት መደረጉን አመልክተዋል።

# አዲስ አበባ በጤናማ ከተሞች ውድድር ተመረጠች

በጋዜጣው ሪፖርተር


አዲስ አበባ፡-አዲስ አበባ በጤናማ ከተሞች ውድድር እንደተመረጠች የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ አስታወቀ። የመንገድ ደህንነት ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ማስፈፀሚያ የሚውል 75 ሺህ ዶላር የገንዘብ ሽልማት ማግኘቷንም ገልጿል።

ኤጀንሲው ለዝግጅት ክፍላችን በላከው መግለጫ እንዳስታወቀው፤ አዲስ አበባ በጤናማ ከተሞች ውድድር ተመርጣለች። በዚህም የመንገድ ደህንነት ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ማስፈፀሚያ የሚውል 75 ሺህ ዶላር የገንዘብ ሽልማት አግኝታለች።

በመዲናችን አዲስ አበባ የሕይወትና የንብረት ጥፋት እያደረሰ ያለውን የመንገድ ትራፊክ አደጋ ለመቀነስ እንዲያስችል የከተማዋ አስተዳደር የመንገድ ደህንነት ስትራቴጂ በመንደፍና ካውንስል በማቋቋም ወደ ትግበራ መግባቱን ያስታወሰው ኤጀንሲው፤ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲም የካውንስሉ ጸሐፊ በመሆን የከተማዋን የትራፊክ ፍሰት ምቹ ከማድረግና ደህንነቱንም ከመጠበቅ አንጻር በግንባር ቀደምትነት በመሰለፍ የመንገድ ትራፊክ አደጋውን ለመከላከል በርካታ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል።

ባለፉት ዓመታትም በተለይም በጠጥቶ ማሽከርከር የሚደርሰውን የትራፊክ አደጋ ለመቀነስ በቁጥጥሩና በግንዛቤው ዘርፍ ባካሄደው እንቅስቃሴ በ2015 በጀት ዓመት በትራፊክ ግጭት የሚከሰተውን የሞት ቁጥር መቀነስ እንደተቻለ ጠቅሶ፤ ይኸው እንቅስቃሴም በዓለም አቀፍ ደረጃ ምልከታን አግኝቷል።

‹አጋርነት ለጤናማ ከተሞች› የተሰኘው ዓለም አቀፋዊ የትስስር አውታር ከተሞች ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን፣ ጉዳትን አስቀድሞ በመከላከል ረገድ ያዘጋጁዋቸው ፖሊሲዎችንና ፕሮጀክቶችን እንዲሁም የተሠሩ ሥራዎችን ገልጸው እንዲያቀርቡ ተጠይቆ እንደነበር አመላክቶ፤ በከተማዋ የሚደርሰውን የትራፊክ አደጋ ለመከላከል በተለይም በጠጥቶ ማሽከርከር ዙሪያና በሌሎች አደጋን ተከላክሎ በማሽርከር የተሠሩ እና እየተሠሩ ያለ ፕሮጄክቶችን እና ወደ ተግባር የተለወጡ ስትራቴጂዎች እንዲቀርቡ ተደርጓል። 70 ከተሞች




በተሳፉበት በዚህ ውድድር አዲስ አበባ ተመርጣለች።

በተጨማሪም በአደጋ መከላከል ዘርፍ ለምታካሂደው እንቅስቃሴ ከጥቅምት 23 ቀን 2023 እስከ ታህሳስ 31 ቀን 2024 ድረስ በከተማዋ የትራፊክ አደጋን ለመከላከል እየተተገበሩ ለሚገኙ የመንገድ ደህንነት ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ማስፈፀሚያ የሚውል 75 ሺህ ዶላር የገንዘብ ሽልማት አግኝታለች ብሏል ኤጀንሲው በመግለጫው።

ቫይታል ስትራቴጂስ የተሰኘ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት በዓለም አቀፍ ደረጃ 70 ከተሞች አባል የሆነበት አጋርነት ለጤናማ ከተሞች (Partnership for Healthy Cites) የተሰኘ ዓለም ዓቀፋዊ የትስስር አውታር ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችንና መሰል ጉዳቶችን ለመከላከል በመንገድ ደህንነት በምግብ ፖሊሲ፣ በትምባሆ ቁጥጥር፣ በሰላማዊ እንቅስቃሴ፣ በቁጥጥር እና መሰል ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ላይ የሚሠራ ድርጅት እንደሆነ ተመላክቷል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ለሰላም የተዘረጉ እጆችን አለመቀበል አሸባሪነትን ዳግም ማረጋገጥ ነው!

መንግሥት ለሰላም ካለው ቁርጠኝነት የተነሳ የተወካዮች ምክር ቤት በአደባባይ ሽብርተኛ ብሎ ከሰየመው ከሸኔ ቡድን ጋር ወደ ሰላም መምጣት የሚያስችሉ ሁለት ዙር የሰላም ውይይቶችን አድርጓል። ልበ ሰፊ በመሆን ከቡድኑ ጋር ያደረጋቸው ውይይቶች በተለይ ሰላም ወዳድ በሆነው ሕዝባችን ዘንድ ከፍ ያለ ተስፋ ማጫሩ ይታወሳል።

ሰላም ለሀገራችን መረጋጋት፣ ከዚህ ለሚመነጨው ልማት ካለው ሁለንተናዊ አስተዋጽኦ አንጻር ፣ መንግሥት ቡድኑን በማነጋገር በሰላማዊ መንገድ በውይይት ለመፍታት የሄደበት ርቀት ፣ እንደ ሀገር በልማት ድህነትን ታሪክ ለማድረግ ለጀመርነው የአዲስ ታሪክ ግንባታ ትልቅ አቅም እንደሚሆን ይታመናል።

የመንግሥት ጥረት ከዚህም ባለፈ ልዩነቶችን በስክነትና በሠለጠነ መንገድ በጠረጴዛ ዙሪያ በውይይት የመፍታት ባህል በማዳበር፡- ሀገር እንደ ሀገር ካለችበት የግጭት አዙሪት እንድትወጣ ለማስቻል ሊኖረው የሚችለው አስተዋጽኦም ከፍ ያለ እንደሚሆን በብዙ መልኩ ለጥያቄ የሚቀርብ አይሆንም።

ይህንን ታሳቢ በማድረግም መንግሥት ከዚህ ቀደም ፡- ነፍጥ አንስተው ሕገ መንግሥቱን በመጣስ ሥልጣን ለመያዝ ከሞከሩት ኃይሎች ጋር ሳይቀር በተደጋጋሚ በውይይትና በሰጥቶ መቀበል መርህ ሰላምን ለማስፋት ጥረት አድርጓል፡- አሁንም እያደረገ ነው። በዚህ የተገኙ ውጤቶች ተስፋ ሰጪ ስለመሆናቸው የፕሪቶሪያ የሰላም ስምምነት ማሳያ ሊሆን የሚችል ነው።

መንግሥት ሕገ መንግሥቱንና የሀገሪቱን ሉዓላዊነት ለመቀበል ዝግጁ ከሆነ ከማንኛውም ኃይል ጋር ልዩነቶችን በሰላማዊ መንገድ በውይይት ለመፍታት በስፋት ተንቀሳቅሷል። ይህም ሆኖ ግን ይዘነው ከመጣነው፣ በመንግሥት ውስጥ መንግሥት የመሆን ልክፍት አንጻር ችግሮችን በውይይት ለመፍታት የሚደረጉ ጥረቶች ተገቢውን ከበሬታ ሳያገኙ የሚቀሩባቸው አጋጣሚዎች መከሰታቸው አልቀረም።

በኦሮሚያ ክልል አንዳንድ አካባቢዎች በመንቀሳቀስ በሕዝቦች ሕይወትና ንብረት ላይ ጉዳት በማድረስ የሰላም ጠንቅ ሆኖ ከቆየው የሸኔ የሽብር ቡድን ጋር በታንዛንያ ዛንዚባር ከወራት በፊት የተጀመረው ውይይትም ይህንን የመንግሥትን እምነት መሬት በማውረድ ቡድኑ በሰላማዊ መንገድ የሚታገልበትን እድል ለመፍጠር ያለመ ነበር።

ይህም ሆኖ ግን የሽብር ቡድኑ ከ60 ዓመታት በፊት የኦሮሞም የሌሎች የኢትዮጵያ ብሔረሰቦችም ሁሉ ጥያቄዎች የነበሩ፡- ምላሽ አግኝተው አሁን ላይ ሕዝባችን ፍሬያቸውን በተጨባጭ እያጣጣማቸው ያሉ ቆሞ ቀር ጥያቄዎችን በማንሳት ውይይቱ ትርጉም አልባ እንዲሆን አድርጓል።

በተለይም ከለውጥ በኋላ በሥራ ላይ የዋሉ ፖለቲካዊ፡- ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ አጀንዳዎችን አንስቶ ከማነብነብ ውጪ የሚቆጠርና የሚቋጠር አጀንዳ ማምጣት ሳይቻለው ቀርቷል። “መንግሥት አዝሎ መንግሥት ያድርገኝ” ከሚል አጉራ ዘለልነት ያለፈ የድርድር ነጥብ ማምጣትም አልቻለም።

መንግሥት በኩል በሀገሪቱ ሰላም ሰፍኖ ኢትዮጵያ ያሏትን ጸጋዎች ወደ ተጨባጭ ሀብትና አቅም ቀይራ ብልጽግናዋን ታረጋግጥ ዘንድ ካለው ጉጉት በመነጨ ከግማሽ መንገድ በላይ ተጉዞ ለጉዳዩ እልባት ለመስጠት ቢሞክርም ፡- የሽብር ቡድኑ በሰላም ጊዜ እንዴት መኖር እንዳለበት ለማሰብ ቸግሮት ታይቷል። በዜጎች ደምና እንግልት መንገዱን መርጧል።

ሰላም በአንድ ወገን ፍላጎት ብቻ የሚሆን ካለመሆኑ አንጻር ፣መንግሥት ከቡድኑ ጋር ያለውን አለመግባባት በሰላማዊ መንገድ በድርድር ለመፍታት የሄደበት ርቀት ከፍያለ ከበሬታ እና እውቅና የሚሰጠው ነው። የመላው ሕዝባችን የሰላም መሻት መገለጫ ጭምር ነው።

ይህ አቋሙ በውይይት ሰጥቶ በመቀበል መርህ ዘመኑን የሚዋጅ የፖለቲካ ባህል እንደሀገር ለመገንባት ለጀመርነው ጥረት ትልቅ አቅም እና ተሞክሮ ተደርጎ የሚወሰድ ነው። አርቆ አሳቢነት፡- ከትናንት ተምሮ ዛሬን የተሻለ ለማድረግ የሚያስችል፡- ነገን ብሩህ ማድረግ የሚያስችል አቅም የተላበሰ በቀጣይም ተጠናክሮ ሊቀጥል የሚገባ ነው።

ይህም ሆኖ ግን መንግሥት ካለበት የሕዝብን ደኅንነት ጨምሮ ሕገመንግሥታዊ ሥርዓቱን ከመጠበቅ ኃላፊነት አንጻር ፡- አሸባሪው ቡድን የሕዝባችን የሰላምና የልማት ፀር የማይሆንበት ደረጃ ላይ ማድረስ ይጠበቅበታል፡- ለዚህ ሕገመንግሥታዊ ሥርዓቱን የመጠበቅ ተልዕኮውን በተቀናጀ መልኩ አጠናክሮ መቀጠል ይጠበቅበታል።

መላው ሕዝባችን በተለይም የኦሮሞ ሕዝብ አሸባሪ ቡድኑ የቁን ያህል ፀረ - ሕዝብ፣ ፀረ -ሰላም እና ፀረ ልማት መሆኑን ከቀደሙት ተግባሮቹ ባልተናነሰ ለሰላም የተዘረጉ እጆችን በመንከስ በተጨባጭ ያሳየ እንደመሆኑ የቡድኑን የጥፋት ተልዕኮ ለማምከን በሚደረገው ጥረት ከመንግሥት ጎን በቁርጠኝነት ሊሰለፍ ይገባል!።


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ኅዳር፣ፖለቲካው፣ኢኮኖሚው...፣ሁሉም ይታጠን !

**በቁምላቸው አበበ ይማም(ሞሼ ዳያን)**

ወረርሽኙ ኅዳር ወር ላይ ስለገባ ” የኅዳር በሽታ” ተባለ ፡- ወደ ወሊጋ ሲዛመት ደግሞ የንፋስ በሽታ ‘ዱኩባ ቂሌንሳ’ ተሰኘ።“... ይህ መቅሰፍት በሀገራችን በ1911 ዓ.ም ወርዶ ብዙ ሰው ጨርሷል። ወረርሽኙ በጉንፋን በሳል ይጀምርና ትኩሳት፣ ማስለቀስ፣ ነስር፣ ተቅማጥና ተውከት ከማስከተሉ ባሻገር አእምሮም ያስት ነበር። ከዚያም በሦስት በአራት ቀን ይገድላል። የቤተሰቡ አባላት በሙሉ አልጋ ላይ ይውሉ ስለነበር አስታማሚ ስለሚጠፋ በርሀብና በውሃ ጥም ብዙ ሰው ይጎዳ ነበር። ከአራት ቀን ያለፈ ሕመምተኛ ግን ይድናል። አፍላው በሽታ ከኅዳር 7 እስከ 20፣ 1911ዓ.ም ነበር።

በየቀኑም ሁለት ሦስት መቶ ከዚህ በላይም ይሞት ነበር። በአንድ መቃብር ሁለት ሦስት ሬሳ እስከ መቅበር ተደረሰ። በዚህ ሰሞን መቃብር የሚቆፍርና ሬሳ ተሸክሞ ወደቀብር የሚወስድ ሰው ማግኘት ችግር ነበር። ባል የሚስቱን፡- አባት የልጁን ሬሳ እየተሸከመ ቀበረ። መቃብር ይቆፍርና ቤቱ ሄዶ ሬሳ ይዞ ሲመለስ ሌላው ቀብሮበት ያገኘዋል።

ቤተሰብ በሙሉ የታመመባቸው በየቤታቸው እየሞቱ አውሬ በላቸው። በበሽታው ልዑል አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪና ልዕልት ወ/ሮ መነን በጠና ታመው ነበር፡- ንግሥት ዘውዲቱም አልጠናባቸውም እንጂ ታመው ነበር። ከመኳንት ከንቲባ ወሰኔ ዘአማኒኤል፡- ከካህናትም ሐዲስ አስተማሪው አለቃ ተገኘ ሞቱ። አለቃ የመምህር ወ/ጊዮርጊስ ደቀ መዝሙር ነበሩ።

በዚያ ወራት በአዲስ አበባ የነበረው ጭንቀት በስፍራው ተገኝቼ ተመልክቼዋለሁ። የኔታ ወልደጊዮርጊስ በሰፈራቸው በጉለሌ ክፍል በየቤቱ እየዞሩ ለበሽተኞችና ለገመምተኞች እንጀራና ውሃ ሲያድሉ ሰነበቱ። በእግዚአብሔር ቸርነት ከበሽታውአምልጠን ነበርና እኔንና ጎጃሜ ኃይለማርያምን ውሃ በገንቦ እያሸከሙ እሳቸው ቁራሽ እንጀራ ይዘው ይሄዱና ከቤቱ ደጃፍ ሲደርሱ እኛን ውጪ አስቀርተው ውሃውንና ቁራሹን ይዘው ይገቡ ነበር።

እኛን ማስቀረታቸው በሽታ እንዳይዘን ስላሰቡልን ነው። በሌላ ስፍራም የዚህን ዓይነት ትሩፋት የሰሩ መንፈሳውያን ሰዎች ነበሩ። ለምሳሌ ሙሴ ሴደርኩይስት የተባሉ ስዊድናዊ ሚስዮናዊ አስተማሪ በየሰፈሩ እየዞሩ ለበሽተኞች እህልና ውሃ መድኃኒት በመስጠት ትሩፋት መስራታቸውን ሰምቻለሁ። እኒህ ሽማግሌ ከጥቂት ቀናት በኋላ በዚሁ በሽታ ታመሙና ሞተው ጉለሌ ተቀብረዋል።

የኅዳር በሽታ (ግሪፕ) በአዲስ አበባ ብቻ አልተወሰነም። ወደ ባላገር ተላልፎ ብዙ ሰው ፈጅቷል። ሆኖም በባላገር የአዲስ አበባን ያህል አልጠነከረም ይባላል። በዚህ በሽታ በመላ ኢትዮጵያ የሞተው የሕዝብ ቁጥር እስከ 40 ሺህ ድረስ መገመቱንም አስታውሳለሁ።በተለይ ኅዳር 12፣ የሚካኤል ዕለት ብዙ ሰው ሞተ። ስለሆነም ወረርሽኙ እስከዛሬ በየዓመቱ የኅዳር ሚካኤል ዕለት በየሰፈሩ ቆሻሻ ሰብስቦ በማቃጠል ‘ኅዳር ሲታጠን ‘ በሚል ይዘከራል። ...” በማለት ‘ የሃያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ ‘ ደራሲ መርስኤ ኀዘን ወ/ቂርቆስ ይነግሩናል። ...”

> **የኅዳር በሽታ (ግሪፕ) በአዲስ አበባ ብቻ አልተወሰነም። ወደ ባላገር ተላልፎ ብዙ ሰው ፈጅቷል። ሆኖም በባላገር የአዲስ አበባን ያህል አልጠነከረም ይባላል። በዚህ በሽታ በመላ ኢትዮጵያ የሞተው የሕዝብ ቁጥር እስከ 40 ሺህ ድረስ መገመቱንም አስታውሳለሁ።በተለይ ኅዳር 12፣ የሚካኤል ዕለት ብዙ ሰው ሞተ። ስለሆነም ወረርሽኙ እስከዛሬ በየዓመቱ የኅዳር ሚካኤል ዕለት በየሰፈሩ ቆሻሻ ሰብስቦ በማቃጠል 'ኅዳር ሲታጠን' በሚል ይዘከራል። ...” በማለት ' የሃያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ ' ደራሲ መርስኤ ኀዘን ወ/ ቂርቆስ ይነግሩናል። ...”**

የ20ኛው ክፍለ ዘመን የመጀመሪያ ሁለት አስርት ዓመታት ለመላው የዓለም ህዝብ የሰቆቃ ዓመታት ነበሩ፡- ምክንያቱ ደግሞ የወቅቱ ሃያላን መንግሥታት በሁለት ጎራ ሆነው ጦርነት ውስጥ ገብተው ስለነበር ነው። እ.ኤ.አ ከ1914 ዓ.ም እስከ 1918 ድረስ የዘለቀውና የ15 ሚሊዮን ሰዎችን ህይወት የቀጠፈው ይህ ጦርነት፣ በታሪክ የመጀመሪያው የዓለም ጦርነት ተብሎ የሚታወቀው ነው።

የጦርነቱ ማብቃት ሊታወጅ ጥቂት ሲቀረውና ዕልቂቱ ቆመ ሲባል ግን የዓለም ህዝብ ሌላ ፍዳ ማስተናገድ ግድ ሆነበት፡- በሰው ሰራሽ ችግሮች (በዋነኝነት በጦርነት) ተወጥሮ የቆየው መላው የአለም ህዝብ አሁን ደግሞ በእንፍሉዌንዛ በሽታ ከዳር እስከ ዳር ተጠቃ ይሉናል ሀብታሙ ግርማ የተባሉ ጸሐፊ በአንድ ድረ ገጽ ለንባብ በበቃ ጹሑፋቸው።

በተለምዶ የስፓኒሽ ፍሉ ተብሎ የሚታወቀው ይህ ወረርሽኝ፣ መነሻው ከወደ አሜሪካ እንደሆነ ይታመናል። እ.ኤ.አ በጥር ወር 1918 ዓ.ም በአንደኛው የአለም ጦርነት ማብቂያ ዋዜማ፣ በጦርነቱ ለመካፈል የአሜሪካ ወታደሮች ወደ አውሮፓ ለመጓዝ ዝግጅት በሚያደርጉበት ወቅት ከተከሰተው ወረርሽኝ ጋር ይያያዛል። በካንሳስ በሚገኘው ፉንስተን የወታደራዊ ማሰልጠኛ ማዕከል የተቀሰቀሰው ወረርሽኙ፣ በሶስት ቀናት ብቻ 45 ሺህ የሚሆኑ ወታደሮችን አጠቃ፡- ወታደሮቹ አትላንቲክን አቋርጠው አውሮፓን እንደረገጡ በሽታውም አውሮፓ ደረሰ።

የእንፍሉዌንዛ በሽታው በአውሮፓ ለመጀመሪያ ጊዜ የታየው በፈረንሳይ ቢሆንም በጦርነቱ ምክንያት ለፕሮፓጋንዳ መጠቀሚያ ይሆናል በሚል ወረርሽኙ ለህዝብ ሳይገለጽ ተደብቆ ቆይቷል። በሽታው ይፋ የሆነው እ.ኤ.አ በህዳር ወር 1918 ዓ.ም በስፔን ለመጀመሪያ ጊዜ በሽታው መታየቱን ተከትሎ ነበር። የበሽታው አማጪ ቫይረስ ባለመታወቁ መድኃኒትም ሆነ ማስታገሻ አልተገኘለትም። (እ.ኤ.አ በ1933 ዓ.ም በእንግሊዛዊያን ሳይንቲስቶች እንደተረጋገጠው የበሽታው አማጪ ቫይረስ በሳይንሳዊው አጠራር H1N1 ተጠራ /በዚህም የተነሳ የበሽታውን ስርጭት ለማቆም አልተቻለም።

በጥቂት ጊዜም ከአሜሪካ እስከ አውሮፓ፣ ከኤሽያ እስከ አፍሪካ፣ከአርክቲክ እስከ ፓስፊክ ደሴቶች ድረስ በከፍተኛ ፍጥነት ተዛመተ። በሽታው እንዲዛመት የአለም የወቅቱ ነባራዊ ሁኔታ ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል። ይህም ወታደሮች ከአንዱ የአለም ክፍል ወደ ሌላው ለዘመቻ

ወደ ገጽ 14 ዞሯል

ዜና

# በቀይ ባሕር አካባቢ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ኢትዮጵያን ያገለሉ መሆን የለባቸውም

ዘላለም ግዛው

አዲስ አበባ፡- በቀይ ባሕር አካባቢ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ብሔራዊ ጥቅምን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪም መንገድ ስለሚነኩ ኢትዮጵያን ያገለሉ መሆን እንደሌለባቸው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር ምስጋኑ አርጋ ገለጹ።

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የውጭ ግንኙነትና ሠላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርን የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ዕቅድ አፈጻጸምን ትናንት ገምግሟል። ከቋሚ ኮሚቴ ለተነሱ ጥያቄዎች የሚኒስቴሩ የተለያዩ ዘርፎች ኃላፊዎች ምላሽና ማብራሪያ ሰጥተዋል።

የቀይ ባሕር ጉዳይ አንዱ የትኩረት መስካችን ነው ያሉት አምባሳደር ምስጋኑ፤ የቀይ ባሕር እና የወደብ ጉዳይ የተለያዩ መሆናቸውን አብራርተዋል።

በቀይ ባሕር አካባቢ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች የሀገርን ብሔራዊ ጥቅም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪም መንገድ ስለሚነኩ በአካባቢው የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ኢትዮጵያን ያገለሉ መሆን የለባቸውም ብለዋል።

ይህ ጥቅም በሠላማዊ መልኩ የሚደረግ፣ በሌሎች ሀገራት ላይ ስጋት የሚደቅን ሳይሆን ዕድል የሚያመጣ መሆኑን ገልጸው፤ ኢትዮጵያ በዚህ ማዕቀፍ ሳትገፋ ጥቅሟን የምታስከብርበት የትኩረት ማዕከል መሆን አለበትም ነው ያሉት።

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ ቀይ ባሕር አብዛኛው የዓለም የንግድ እንቅስቃሴ የሚካሄድበት መስመር በመሆኑ፤ አካባቢው በአሉታዊ መልኩ ችግር ውስጥ ከወደቀ የኢትዮጵያም ጥቅም ይነካል።

የትኛውም የሽብር እንቅስቃሴ፣ የባሕር ደህንነት ጉዳይ፣ ከሩቅም ከቅርብም መጥተው የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም ስለሚጎዳ በቀይ ባሕር አካባቢ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ኢትዮጵያን የሚያገል መሆን የለበትም ሲሉም ገልጸዋል።

በአካባቢው የሀገሪቱ ንግድ የሚካሄድበት፣ የባሕር በሮቻችንም የምንጠቀምበት በመሆኑ ኢትዮጵያን ያገለለ እንቅስቃሴ ውጤታማ እንደማይሆንም ነው የተናገሩት።

በጎረቤት ሀገራት በርካታ የወደብ አማራጮች አሉ ያሉት አምባሳደር ምስጋኑ፤ የወደብ አማራጭ ሠላማዊ በሆነና ቀጣናዊ ትስስርን በሚያጠናክር በድርድር፣ ሰጥቶ በመቀበልና በተለያየ መልኩ የሚካሄድ መሆኑን ጠቅሰው፤ ተግባሩ ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል፡፡



አምባሳደር ምስጋኑ አርጋ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ

የሩብ ዓመት አፈጻጸሙ የዲፕሎማሲ ሥራዎቹ የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ ወደ ከፍታ እየተሻገረ መሆኑን የሚያሳይ ነው። ባለብዙ ወገን የዲፕሎማሲ ግንኙነት ላይ የተደረጉ እንቅስቃሴዎችም ውጤታማ እንደነበሩ የሚኒስቴሩን እቅድ ያቀረቡት አቶ መኮንን ጎሣዬ አመልክተዋል።

እየተሻሻለ የመጣው የውስጥ ሠላም በተለይም የፕሪቶሪያ የሰላም ስምምነት ከሀገሮችም ከባለብዙ ወገኖች ጋርም ያለውን ግንኙነት በማሻሻል ጉልህ ሚና መጫወቱንና ስምምነቱም በጥሩ ሁኔታ እየተፈጸመ ነው ብለዋል።

ከአሜሪካ፣ ከአውሮፓ እና ከዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር ያለውን ግንኙነት ማሻሻሉን እና የፋይናንስ ትብብር የተጀመረበት አጋጣሚ መፍጠሩንም ነው የጠቀሱት።

ከሪሚታንስ አንድ ነጥብ 1 ቢሊዮን በላይ ዶላር ወደ ሀገር እንዲገባ ድጋፍ መደረጉንም ገልጸዋል።

በመጀመሪያው ሩብ ዓመት አፈጻጸም ግምገማው፤ ከቆንስላ አገልግሎቶች እና ሕንጻ ኪራይ ከ341 ሚሊዮን ብር በላይ መሰብሰብ መቻሉ ተጠቅሷል።26 የተቋሙ አገልግሎቶች በኦን ላይን እየተሰጠ መሆኑም ነው የተነሳው፡፡

በውጭ ሀገር አንድ ሺህ 067 የመብት ጥሰት የደረሰባቸው ዜጎች ካሳ እንዲያገኙ መደረጉን እና በሕገ ወጥ መንገድ የተጓዙ 10 ሺህ 672 ዜጎች ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ መደረጉም ተጠቅሷል።

# በጉባኤው የኢትዮጵያን...

ከገጽ 1 የዞረ

ለመወያየት ዕድል ሰጥቷል ብለዋል።

በጉባኤው የተለያዩ የአውሮፓ ሀገራት በኢትዮጵያ እየተሠራ ያለውን ለውጥ በተሻለ ሁኔታ መረዳት መቻላቸውን አስታውቀዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ከጀርመኑ መራሔ መንግሥት አላፍ ሾልዝ ጋር ተገናኝተው በሁለትዮሽ፣ ቀጣናዊና ዓለም አቀፍ ጉዳዮች ዙሪያ ጠቃሚ ውይይት ማድረጋቸውን አስታውሰዋል።

የኢትዮጵያ መንግሥት በተለያዩ ጉዳዮች የሚሠራውን ሥራ ከማሳወቅ ባለፈም ጀርመን ከኢትዮጵያ ጋር በታዳሽ ኃይል፣ በማዳበሪያ ምርት፣ በኢኮኖሚ ማሻሻያውና በተለያዩ ዘርፎች ላይ አብሮ ለመሥራት መስማማታቸውን ገልጸዋል።

ጀርመን እ.ኤ.አ. በ2030 ለሚተገበረው የአውሮፓ ኅብረት አፍሪካ ግሪን ኢነርጂ ኢኒሼቲቭ አራት ቢሊዮን ዩሮ እንደምትመድብ ያስታወቀች ሲሆን፤ ኢትዮጵያም ከድጋፉ ተጠቃሚ ትሆናለች ተብሎ እንደሚጠበቅ አመላክተዋል።

በአውሮፓ በኢኮኖሚው ከፍተኛ ዕድገት ካላቸው ሀገራት መካከል ጀርመን አንዷ ስትሆን በዓለም አቀፍ ኢኮኖሚም ከሦስት እስከ አራት ያለውን ደረጃ የምትይዝ ጠንካራ ሀገር ናት ብለዋል።

በመሆኑም ኢትዮጵያ ከጀርመን ጋር ያላት ግንኙነት ጠንካራ በመሆኑ ለሀገራችን ብሔራዊ ጥቅምና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ከፍተኛ ጠቀሜታ የሚያስገኝ ዲፕሎማሲያዊ ውይይት ተደርጓል ሲሉ አስረድተዋል።

የኮምፓክት ዊዝ አፍሪካ ኢኒሼቲቭ ዓላማ በአፍሪካ ዘላቂ የሆነ እድገት እንዲኖር ማስቻል፣ ሪፎርም የሚፈልጉ ዘርፎችን ማበረታታትና መደገፍ፣ የማክሮ ኢኮኖሚውና የፋይናንስ ዘርፉ የተሻለ ማሻሻያ እንዲኖረው ማድረግ እንዲሁም የንግድና የኢንቨስትመንት ዘርፎችን ማገዝ መሆኑን ገልጸዋል።

ከምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት ከኮምፓክት ዊዝ አፍሪካ ኢኒሼቲቭ ተጠቃሚ የሆነችው ሀገር ኢትዮጵያ ብቻ መሆኗን ጠቁመዋል።

በአጠቃላይ በጉባኤው የተደረገው ውይይት ኢትዮጵያ ድምፅዋን ያሰማችበትና በአፍሪካ ያላት ተሰሚነት መጨመሩ የተረጋገጠበት ውጤታማ መድረክ እንደነበር አስገንዝበዋል።

በሌላ በኩል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከፈረንሳዩ ፕሬዚዳንት ኢማኑዌል ማክሮን ጋር ቅርብ የሆነ ግንኙነት እንዳላቸው ገልጸው፤ ሁለቱ መሪዎች በተደጋጋሚ መገናኘታቸውን አስታውሰዋል።

በበርሊን የኮምፓክት ዊዝ አፍሪካን መድረክ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከፕሬዚዳንት ማክሮን ጋር ውይይት ማድረጋቸውን ገልጸዋል። ።

በውይይቱም ሁለቱን ሀገራት በባሕል፣ በኢኮኖሚ ትብብርና በኢንቨስትመንት ግንኙነት ያሉበትን ደረጃ በተመለከተ ውይይት መደረጉን ጠቁመዋል።

መሪዎቹ በሀገራዊና ቀጣናዊ ጉዳዮች ሀሳብ ተለዋውጠዋል ያሉት አቶ ማሞ፤ በተጨማሪም ኢትዮጵያ ተግባራዊ የምታደርገውን የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም የፈረንሳይ መንግሥት ሊደግፍ በሚችልባቸው መንገዶች ዙሪያ መምከራቸውን ገልጸዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ጀርመን ከአምስት ዓመት በፊት በጀመረችው የኮምፓክት ዊዝ አፍሪካ ኢኒሼቲቭ የተሳተፉ ሲሆን፤ ሰሞኑን ያደረጉት ጉዞም ሁለተኛው የጉባኤው ተሳትፎ ነው።

# የቀድሞ ታጣቂዎችን...

ከገጽ 1 የዞረ

እንደሚተገበር ጠቁመዋል፡፡

274 ሺህ የሚጠጉትና 75 በመቶ የሚሆኑት የቀድሞ ታጣቂዎች በትግራይ ክልል የሚገኙ መሆኑን ጠቁመው፤ ቀሪዎቹ በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ አፋር፣ ጋምቤላ፣ በቀድሞው ደቡብ እና ደቡብ ምዕራብ ክልሎች እንደሚገኙ ተናግረዋል፡፡

የቀድሞ ታጣቂዎቹን መልሶ ለማቋቋም የሚያስፈልገው 850 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ታጣቂዎቹን ከማደራጀት ጀምሮ ከኅብረተሰቡ ጋር እስከመቀላቀል ድረስ ለሚሆነው ሥራ የሚውል መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ያጋጠመውን የገንዘብ ችግር ለመቅረፍና በአፋጣኝ ወደ ሥራ ለመግባት ኮሚሽኑ ከተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማትና አምባሳደሮች ጋር እየተወያየ መሆኑን ያመላከቱት አቶ ልዑልሰገድ፤ ኮሚሽኑ አሁን ላይ አደረጃጀት የመፍጠር፣ የሰው ኃይል የማሟላት፣ የሥልጠና ሰነዶችን የማዘጋጀት ሥራዎችን እያከናወነ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በሀገር ውስጥ ከሚገኙ ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ጋርም ንግግር እየተደረገ መሆኑን ገልጸው፤ ድርጅቶቹ የበኩላቸውን ድጋፍ እንዲያደርጉም መግባቢያ ስምነት መፈራረሙንም ተናግረዋል፡፡

የቀድሞ ታጣቂዎቹን ለማቋቋም ዕቅድ ሲታቀድ 85 በመቶ የሚሆነውን ገንዘብ ከዓለም አቀፍ ተቋማትና ለጋሽ ድርጅቶች ለማግኘት እንዲሁም 15 በመቶ የሚሆነውን ከመንግሥት ለማግኘት ታቅዶ እንቅስቃሴ መጀመሩን አውስተው፤ ባለው አጠቃላይ ሀገራዊ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ አሁን ላይ ብሩ እንዳልተለቀቀ ገልጸዋል፡፡

ዓለም አቀፍ ተቋማት በሰላም ስምምነቱ ወቅት የገንዘብ ድጋፍ ለማድረግ ቃል የገቡ ቢሆንም እስከ አሁን ያደረጉት ድጋፍ ከቢሮ ማደራጀት ተግባር የሚበልጥ እንዳልሆነ የተናገሩት አቶ ልዑልሰገድ፤ እያጋጠመ ያለው የገንዘብ ችግር ኮሚሽኑ ወደ ሥራ እንዳይገባ እንቅፋት እንደሆነበት ጠቁመዋል፡፡

ሥራው ሠላምን ለማጽናት እጅግ አስፈላጊ መሆኑን በመረዳት ዓለም አቀፍ የልማት አጋሮች ድጋፎቻቸውን እንዲሰጡ ጠይቀው፤ መንግሥትም ለሥራው ትኩረት እንዲሰጥ ጠይቀዋል፡፡ የንግድ ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ኅብረት፣ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ እንዲሁም ሁሉም ዜጎች የቀድሞ ታጣቂዎችን በማደራጀቱ ሂደት የበኩላቸው አስተዋፅዖ እንዲወጡ ጠይቀዋል፡፡

# የባሕር በር ስምን ...

ከገጽ 1 የዞረ

“ፈርስት ፋትስቴፕ ኤንድ ሊስት ኦፍ ሀካ” ‹‹ለንደን 1856›› የተሰኘን መጽሐፍ አጣቅሰው ይገልጻሉ።በዚህ ጊዜ የአክሱም መንግሥት ሥልጣኑን እስከ ተጠቀሰው ግዛት ሲያስፋፋ በመርከብ እየተጓጓዘና የንግድ ሥራ እያካሄደ እንደነበረ ይጠቅሳሉ፡፡

ኤም ፐርሐም የተባለ የታሪክ ጸሐፊ ‹‹ዘ ገቨርንመንት ኦፍ ኢትዮጵያ›› በሚል ርዕስ በ1948 እ.ኤ.አ. ባሳተመው መጽሐፍ እንደገለጸው ደግሞ በስምንተኛው ክፍለ ዘመን የደቡብ ዓረቢያ ግዛት ብቻ ሳይሆን አዱሊስን የዓረቦችና የኢትዮጵያ ሕዝቦች በመርከቦች ንግድ ልውውጥ ማድረግ መቀጠሉ እንዳልቀረ ይገለጻል።

ፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክረስት ‹‹ዘ ኢትዮጵያን ቦርደርላንድስ ገጽ 168-169›› ዓረብ ፊቂን ‹‹ሺሃበዲን›› የተባለውን የመናዊው የአሕመድ ግራኝ ዜና መዋዕል ጸሐፊን ጠቅሰው፤ አፄ ልብነ ድንግል ወርቅ፣ የዝሆን ጥርስና መሰሎችን ወደ ዓረብ ሀገር ለሚሄዱ ነጋዴዎች ይልኩ ነበር ይላሉ።

ምሑራኑ ኢትዮጵያ በቀይ ባሕር በኩል ከመካከለኛውና ከሩቅ ምሥራቅ ሀገራት ጋር የንግድ ልውውጥ ታደርግ እንደነበር በርካታ ታሪኮች በማጣቀስ ነው የሚያረጋግጡት።

በፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት የምጣኔ ሀብት ተመራማሪ የሆኑት ዶክተር ጀማል መሐመድ፤ ኢትዮጵያ ምንም እንኳን በዘመናት የታሪክ ሂደት ውስጥ የባሕር በርን ስትጠቀም ብትቆይም፤ በተለያዩ ምክንያቶች ወደብ አልባ ሆናለች ነው ያሉት። ብዙ የሕዝብ ቁጥር ያላት ኢትዮጵያ የባሕር ወደብ አልባ መሆኗ ያስቆጫል ይላሉ።

ምንም እንኳን ቅኝ ተገዝተናል ባንልም ኢትዮጵያ የባሕር በር ያጣችበት ምክንያት የኮሎኒያሊዝምና ቅኝ ግዛት እንቅስቃሴዎች ባመጡት ተፅዕኖ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

የባሕር በር ጉዳይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሲያሳስበው የኖረ ጉዳይ ነው የሚሉት ዶክተር ጀማል፤ ከፖለቲካና ከኢኮኖሚ ደህንነት አንጻር የኢትዮጵያ ሕዝብ ሕልውና መሠረት ከሚባሉ ዋና ዋና ጉዳዮች አንዱ የባሕር በር መሆኑን ይጠቅሳሉ፡፡

የኢንዱስትሪና ሌሎች መሣሪያዎች፣ የጤና ግብዓቶች እንዲሁም ነዳጅ ከውጭ እንደመግባታቸው፤ ዙሪያውን ካሉ ሀገራት ጋር ችግር ቢፈጠር “ብሎክ እንደረጋለን” ሲሉም ይናገራሉ። በዚህም ከፍተኛ የሆነ የኢኮኖሚ ደህንነት ችግር እንደሚያጋጥምና፤ የእነዚህን ሀገራት ፍላጎት ሁልጊዜ ለመቀበል መገደድ ሊኖር እንደሚችል በመጥቀስ ይህ ደግሞ ትልቅ ዋጋ የሚያስከፍል ነው ይላሉ።

ዶክተር ጀማል እንደሚያብራሩት፤ ኢትዮጵያ የባሕር በር አልባ በመሆኗ በወደብ አካባቢ ያሉ የሌሎች ሀገራት ነጋዴዎች የኢትዮጵያን ገበያ ታላሚ ያደርጋሉ። ትልልቅ የኢኮኖሚ ዞን በመፍጠር እንደየአስፈላጊነቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ገበያና ከውጭ የሚገቡ ዕቃዎችን በዋናነት ይቆጣጠራሉ። በሌላ ሀገር ሕግ ስለሚተዳደሩ የኢትዮጵያ መንግሥት ሊያስገድዳቸውና ቁጥጥር ሊያደርግባቸው አይችልም። የሚቆጣጠሩት ግን የኢትዮጵያን ገበያና ኢኮኖሚ ነው።ይህ በሀገሪቱ የዋጋ ንረት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሳድር ነው።

ጥያቄውን መንግሥት ያንሳ እንጂ የሕዝብ የሕልውና ጉዳይ ነው የሚሉት ዶክተር ጀማል፤ ወደብ አልባነት ለሌሎች ሀገራት ፍላጎት ተገዢና ተጋላጭ የሚያደርግ ጉዳት የሚያደርስ በመሆኑ የሕልውና ጉዳይ ተደርጎ ይቆጠራል ሲሉ ይናገራሉ። “አሁን ላይ ኢትዮጵያ ውስጥ ሕዝቡ የሕልውና አደጋ ጥያቄ ውስጥ ነው ያለው። በዋጋ ንረት ምክንያት የሚፈልገውን ምርት ማግኘት አለመቻል ጥያቄ ውስጥ ነው። ኢኮኖሚው የዜጎችን ሕልውና እየፈተነው ነው” በማለት ለኢትዮጵያ የባሕር በር የማግኘት ጉዳይ የግድ የሚል መሆኑን ያነሳሉ፡፡

እንደ እርሳቸው ማብራሪያ፤ ሰው ከአቅሙ በላይ የኑሮ ጫናውን ተቋቁሞ የሚኖረው በአንድ በኩል የባሕር በር ባለመኖሩ ምክንያት ነው። ከውጪ የሚመጡ ዕቃዎች ዋጋቸው ከፍተኛ በመሆናቸው ብቻ ነው ባይባልም አብዛኛው የዋጋ ንረት መንስዔ በወደብ አልባነት የሚከሰቱ ናቸው። ጥያቄው እውን ሆኖ የባሕር በር ማግኘት ቢቻል በዋጋ ንረት ምክንያት የሚፈጠር ችግር ሊቀረፍ ይችላል።

በሌላ በኩል በዚህ አካባቢ ካሉ ሀገራት ጋር ግጭት ውስጥ ቢገባ እንኳን፤ መድኃኒትና ነዳጅን ጨምሮ በወደብ በኩል የሚገቡ ዕቃዎች ላይ ትልቅ ጫና ይፈጠራል ባይ ናቸው። ስለዚህ ወደብ የቅንጦት ጉዳይ ሳይሆን ከፍተኛ የሕልውና ጉዳይ ተደርጎ ይቆጠራል ነው የሚሉት።

ኢትዮጵያ ውስጥ የዋጋ ጭማሪና ቅናሽ ከሚከሰትባቸው ምክንያቶች አንዱ ወደብ ላይ ያሉ ትልልቅ ነጋዴዎች የኢትዮጵያ ገበያ ላይ ትኩረት በማድረግ በሚፈጥሩት ተፅዕኖ ሲሆን፤ የባሕር በር አለማግኘት በርካታ ዋጋ ሊያስከፍል እንደሚችል ይጠቅሳሉ፡፡

በሰጥቶ መቀበል መርሕ፣ በሕዝቦች መካከል ያለውን ግንኙነት በማጠናከር፣ ግብይት ተኮር ኢኮኖሚያው መስተጋብር በመፍጠር፣ መንግሥታት እርስበርሳቸው ያላቸውን ጠንካራ ግንኙት በማሳደግ ስምምነቶችን በመፍጠርና በዓለም አቀፍ አስቻይ ሁኔታዎች የባሕር በር ጥያቄው ምላሽ የሚያገኝበትን ሁኔታ መፍጠር እንደሚገባም ይመክራሉ፡፡

# ‹‹ መንግሥት በጤና ዘርፍ ትኩረት አድርጎ እየሠራ ያለው ፍትሐዊ ተጠቃሚነት ላይ ነው››

**- ዶክተር ዮሐንስ ጫላ**
**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ ኃላፊ**

ስምስም መንግሥቱ

ጤና ከሰው ልጅ የቅድሚያ ፍላጎቶች ውስጥ አንዱ ነው። ከግለሰብም አልፎ እንደ ማህበረሰብና ሀገር ጭምር የጤና ጉዳይ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው ነው።ጤናማ ትውልድ እስካልተገነባ ድረስ ጤናማ ሀገር ሊኖር አይችልም።

ይህን መነሻ በማድረግም መንግሥት ለጤና ዘርፍ ሰፊ መዋዕለ ነዋይ በመመደብ የተለያዩ የጤና መሰረተ ልማቶችን እያስፋፋ ከመሆኑም ባሻገር አክሞ ለማዳን እና ለቅድመ መከላከል ግዙፍ መዋዕለ ንዋይ በመመደብ የህብረተሰቡን ጤና ለመጠበቅ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል።

ይህ የመንግሥት ጥረት ከሚታይባቸው አካባቢዎች አንዱ አዲስ አበባ ነው።በአዲስ አበባ ጤና ቢሮ አማካኝነት የህብረተሰቡን ጤና ሊያስጠብቁ የሚችሉ የተለያዩ መሰረተ ልማቶች እየተገነቡ ከመሆኑም ባሻገር ባሉት የጤና ተቋማት አማካኝነት የቅድመ መከላከልና የፈውስ ህክምናዎች በመከናወን ላይ ይገኛሉ።

በአዲስ አበባ ከተማ በጤና አገልግሎት ተደራሽነትና መሠረተ ልማት ግንባታ የተከናወኑትን ተግባራት፡- እንዲሁም በአገልግሎት ዙሪያ ከተጠቃሚው የሚነሱትን ቅሬታዎች በተመለከተ በእንግድነት ከጋበዝናቸው ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ዮሐንስ ጫላ ጋር ያደረግነውን ቆይታ እንደሚከተለው አቅርበናል።

**አዲስዘመን፡- ለከተማዋ ነዋሪ የጤና አገልግሎትን ተደራሽ ለማድረግ የተሰሩ ሥራዎች ምን ይመስላሉ?**

**ዶክተር ዮሐንስ፡-** በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥር 7 ሆስፒታሎች፣ 101 ጤና ጣቢያዎች በአገልግሎት ላይ ይገኛሉ። ከነዚህ በተጨማሪ በፌዴራልና በግል አገልግሎት የሚሰጡ በርካታ የጤና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በመኖራቸው የተደራሽነት ላይ ችግር የለም።

አዲስ ዘመን ፡- ተደራሽነት ላይ በዚህን ያህል ከተሰራ ፍትሀዊነትን በማረጋገጥ በኩል ያለው ሁኔታ ምን ይመስላል?

ዶክተር ዮሐንስ፡- የከተማ አስተዳደሩም ሆነ የጤና ቢሮ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ የሚገኘው ፍትሐዊ ተጠቃሚነት ላይ ነው። በከተማ አስተዳደሩ ውስጥ ወደ 119 ወረዳዎች ይገኛሉ። ሁሉም የጤና ጣቢያ የላቸውም። ወደሌላ ወረዳ ሄደው ነው አገልግሎት የሚያገኙት። ይሄ የፍትሐዊነት ጥያቄ ያስነሳል። በሌላ በኩልም ሆስፒታሎቹ በመኻል ከተማ ውስጥ ነው የሚገኙት። ሰፊ ቁጥር ያለው ማህበረሰብ የሚኖረው ደግሞ ከመኻል ከተማ የራቀ በመሆኑ የጤና አገልግሎት ፍለጋ ረጅም ርቀት ይጓዛሉ። ሌላው ፍትሐዊነትን ለማረጋገጥ ከፍለው መታከም የማይችሉ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ማድረግ ሲሆን እነዚህን የማህበረሰብ ክፍሎች በማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን ኢንሹራንስ አገልግሎት እንዲያገኙ በማድረግ ፍትሐዊነትን ለማረጋገጥ እየተሞከረ ነው።

የጤና መድህን ኢንሹራንስ እንደሀገር ከ10 አመት በፊት የተጀመረ ሲሆን፣ በከተማ አስተዳደሩ ደግሞ 2009 ዓ.ም በ10 ወረዳዎች ላይ መተግበር ተጀምሯል። በአሁኑ ጊዜ ግን በሁሉም የከተማ አስተዳደሩ ወረዳዎች ማህበረሰቡን ያቀፈ ሥራ ተሰርቷል።

በማህበረሰብ የጤና መድህን ኢንሹራንስ ወደ ሁለት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሺ የሚሆኑ የከተማዋ ማህበረሰብ ክፍሎች ተካተዋል። ከነዚህ ውስጥም ወደ 350 ሺ የሚሆኑት ከፍለው መታከም የማይችሉ በመሆናቸው የከተማ አስተዳደሩ ሙሉ ወጪያቸውን ሸፍኖላቸዋል። የከተማ አስተዳደሩ እነዚህ የማህበረሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ በ2015 በጀት አመት ወደ ስድስት መቶ ሚሊዮን ብር ለማህበረሰብ የጤና መድህን ኢንሹራንስ ድጎማ አድርጓል። መክፈል ለሚችሉትም የከተማ አስተዳደሩ ለመመዝገቢያ 500 ብር ድጎማ ያደርጋል።

የማህበረሰብ ጤና መድህን ኢንሹራንሽ ተጠቃሚዎች በፌዴራልም ሆነ በአዲስ አበባ ከተማ ሥር በሚገኙ የጤና አገልግሎት መስጫዎች በነፃ አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ። በዚህ መልኩ ነው ፍትሐዊነትን ከማስፈን አንጻር ሥራዎች እየተሰሩ ያሉት። በተያዘው በጀት አመትም ማህበረሰቡ በማህበረሰብ የጤና መድህን ኢንሹራንስ ተጠቃሚ እንዲሆኑ



ምዝገባ እየተካሄደ ነው።

**አዲስዘመን፡- በፍትሐዊነት ላይ ሥራዎች መሰራታቸው ተደራሽነትን ያረጋግጣል?**

**ዶክተር ዮሐንስ፡-** ተደራሽነት ከህዝብ ቁጥር፣ ካሉት ጤና ተቋማትና ባለሙያዎች ጋር ይያያዛል። ከዚህ አንጻር ተደራሽነት ላይ ችግር የለም። አካባቢው ላይ አገልግሎቱን ማግኘት ሲገባው ወደሌላ አካባቢ መሄዱ የፍትሐዊነት ጥያቄ ያስነሳል። ከፍሎ መታከም በሚችልና በማይችል መካከል የሚፈጠረውም ክፍተት እንዲሁ የፍትሐዊነት ጥያቄ ያስነሳል። ከዚህ አንጻር ነው ልዩነቶቹ የሚገለጹት።

አንድ ጀነራል ሆስፒታል ከአንድ ሚሊዮን በላይ ለሚሆኑ አገልግሎት ፈላጊዎች፣ሪፈራል ሆስፒታል ደግሞ እስከ አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ህዝብ አገልግሎት ይሰጣሉ ተብሎ ይጠበቃል። በዓለም ጤና ድርጅት በተቀመጠው መስፈርት መሠረት ተደራሽነት ላይ ችግር የለም።

**አዲስ ዘመን፡- የጤና መሠረተ ልማት ግንባታ ላይ የተከናወኑት ተግባራትን ቢገልጹልን**

**ዶክተር ዮሐንስ፡-** ቀደም ሲል እንዳነሳሁት የፍትሐዊነት ጥያቄን ለመመለስ የጤና ተቋማት በሌለባቸው ክፍለ ከተሞች በዚህ ሶስት አመታት ግንባታዎች ተከናውነዋል። ለዚህም ማሳያ የሚሆነው በክብርት አበበች ጎበና የተሰየመ «የእናቶችና ህፃናት አገልግሎት » የሚሰጥ ሆስፒታል ግንባታ ነው። ሐያት አካባቢ የሚገኘው ይህ ሆስፒታል ወደ 400 መኝታ ክፍሎችና የተለያዩ አገልግሎቶችን ያካተተ፣በግብአትና በባለሙያ የተደራጀ ምቹና ዘመናዊ ሆኖ የተገነባ ሆስፒታል ነው።

ይህ ሆስፒታል መገንባቱ ቀደም ሲል ወደ ዳግማዊ ሚኒልክ፣የካቲት፣ጋንዲ ሆስፒታሎች የሚላኩ እናቶች ይደርስባቸው የነበረው እንግልት ሆስፒታል ከደረሱ በኋላም ፈጣን አገልግሎት ሳያገኙ ቀርተው ወንበር ላይ እስከ መውለድ የሚደርሱበት አጋጣሚ እንዲያበቃ አድርጎታል ። ሆስፒታሉ በማዋለድ አገልግሎት ከፍ ያለ ሥራ የሚሰራና በወር ከአንድ ሺ በላይ ለሚሆኑ እናቶች የወሊድ አገልግሎት በመስጠት ሌሎች ሆስፒታሎች ላይ የነበረ ጫና በመቀነስ እፎይታ ሰጥቷል። በዚህ መልኩ የጤና አገልግሎቱን ተደራሽ በማድረግ ፍታዊነትን ከማረጋገጥ በተጨማሪ ጥራትንም አብሮ ማስጠበቅ ተችሏል።

ሌላው ኮልፌ ቀራኒዮና በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተሞች ውስጥ ግንባታቸው ከ50 በመቶ በላይ የደረሰና በጥሩ ሁኔታ በመካሄድ ላይ ያለው አጠቃላይ ሆስፒታሎች ናቸው። ሆስፒታሎቹ እያንዳንዳቸው ከ450 በላይ መኝታዎች ያሏቸው ዘመናዊ ሲሆኑ፡- እያንዳንዳቸው የግንባታ ወጪያቸው ከሶስት ነጥብ አምስት ቢሊየን ብር በላይ ነው።

እነዚህ ግንባታቸው በመፋጠን ላይ የሚገኙት ሆስፒታሎች በ 2002 ዓ.ም ላይ ነበር ይገነባሉ ተብለው ለህዝቡ ቃል ሲገባ የነበረው። በዚህ አምስት አመት የለውጥ ሂደት ውስጥ ግን ብዙ ሥራዎች መሥራት ተችሏል። እነዚህ ሆስፒታሎች ለአገልገሎት ሲበቁ በተለይም በኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ በመገንባት ላይ ያለው ቤተል ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎችና በዙሪያው ላሉ አጎራባች ከተሞች ተደራሽ በማድረግ የነበረባቸውን ችግር ያቃልላል።

ሌላው የጤና መሠረተ ልማት ደግሞ የማስፋፊያ ሥራ ነው። እንደ ሚኒልክ፣የካቲት ሆስፒታሎች አንድ መቶ አመት አገልግሎት የሰጡ ናቸው። ሚኒልክ ሆስፒታል በአይን ህክምና ይታወቃል። ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የሚመጡ ታካሚዎችን ያስተናግዳል። ሆኖም ግን አገልግሎቱን በተለያየ ክፍል መስጠቱ ምቹ አልነበረም። አሁን ላይ በተከናወነው በማስፋፊያ ሥራ ባለ አራት ወለል ዘመናዊ ህንጻ ተገንብቶ የነበረውን የመኝታ ክፍል በአራት እጥፍ እንዲሁም የቀዶ ጥገና ህክምና ክፍልን በሁለት እጥፍ፣ የተመላላሽ ታካሚ ክፍል ሥራንም በአራት እጥፍ በማሳደግ የነበረውን ችግር ማቃለል ተችሏል።

ዘውዲቱ መታሰቢያ ሆስፒታልም የነበረው መሠረተ ልማት ከሚሰጠው አገልግሎት ጋር የተመጣጠነ አልነበረም። በዚህ ሆስፒታል ውስጥም አሁን ላይ ሆስፒታሉ እየሰጠ ካለው አገልግሎት በላይ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችለው፡- በአንድ ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር ባለ ስምንት ወለል ዘመናዊ ህንፃ በመገንባት ላይ ይገኛል። በዚሁ ሆስፒታል ውስጥ ተዘግቶ የቆየው የአይን ህክምና ክፍል አገልግሎት እንዲሰጥ ተደርጓል።

ለእናቶችና ህፃናት አገልግሎት እንዲሰጥ ታስቦ የተገነባው ጥሩነሽ ቤጂንግ ሆስፒታል፡- በአካባቢው ላይ የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች የተለያየ የህክምና አገልግሎት እንዲሰጥ ከ300 በላይ የመኝታ አገልግሎት የሚሰጥ የማስፋፊያ ግንባታ ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል።

በጤና ጣቢያዎች የሚሰጠው አገልግሎት እየሰፋ በመሄዱ ነባር ጤና ጣቢያዎችንም ከማጠናከር አንጻር፡- በ2015 በጀት አመት ብቻ ወደ 28 የማስፋፊያ ፕሮጀክቶች በየጤና ጣቢያዎች ተተግብሯል። የማስፋፊያ ሥራዎች ማስፋፊያ ይባሉ እንጂ ለየተቋማቱ የህክምና አገልግሎት ትልቅ አቅም የሚፈጥሩ ናቸው።

ባለፉት አምስት አመታት በተከናወኑት ሥራዎች 18 ጤና ጣቢያዎች በቀዶ ህክምና የማዋለድ አገልግሎት መስጠት ችለዋል። ። ይሄ በጤናው ዘርፍ የተመዘገበ ውጤት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ከሀገራዊ ለውጡ በፊት በተለይም ከመኻል ከተማ ወጣ ባሉ አካባቢዎች የጤና መሠረተ ልማት ግንባታ ለማከናወን ተብለው የመሠረት ድንጋይ ተጥሎ አንዳንዶችም ግብአት ቀርቦ ግንባታቸው ሳይከናወን ለረጅም ጊዜ የቆዩትን ለይቶ ወደ ሥራ በማስገባት በኩል የተከናወነ ተግባር ካለ ቢገልጹልን?**

**ዶክተር ዮሐንስ፡-** ከ10 አመት በፊት የመሠረት ድንጋይ ተጥሎ ሳይሰሩ የቀሩትን ነው በዚህ ሶስት አመት ውስጥ መሥራት የተቻለው። በ2016 በጀት ወደ አምስት ጤና ጣቢያዎች ለመገንባት ታቅዷል። የግንባታ ሥራዎችንም ከዲዛይንና ኮንስትራክሽን ተቋም ጋር በመሆን ቅድሚያ በሚሰጣቸው ላይ ትኩረት በማድረግ ነው ሥራዎች በመከናወን ላይ የሚገኙት።

ለግንባታ ተብለው ታጥረው የተቀመጡት ላይም ክፍተቶች ነበሩባቸው፡ ለምሳሌ የባለቤትነት ማረጋገጫ ( ካርታ) አለመኖር፣ ጨረታ ከወጣባቸው በኋላ ቅሬታዎች መምጣት ጋር በተያያዘ በርካታ ምልልሶች ያጋጥሙ ነበር። አሁን ላይ እንዲህ ያሉ ችግሮችን ለማስቀረት ወደ ግንባታ ከመገባቱ በፊት ቀድመው ሥራዎች እንዲሰሩ በከተማ አስተዳደሩ አቅጣጫ ተቀምጦ በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት ነው ሥራዎች የሚሰሩት።

**አዲስ ዘመን፡- የጤና መሠረተ ልማት ከፍተኛ በጀት የሚጠይቅ በመሆኑ ስለበጀት ሁኔታውም ቢገልጹልን?**

**ዶክተር ዮሐንስ፡-** ከተማ አስተዳደሩ በራሱ በጀት እንደሚተዳደር ይታወቃል። ከተማው ነዋሪም ሰፊ የልማት ጥያቄዎች ያቀርባል። የከተማ አስተዳደሩ ለምገባ፣ለኩላሊት እጥበት ታካሚዎች፣ ለማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን ኢንሹራንስ ተጠቃሚዎች እና ሌሎችም ፕሮግራሞች ወደ ዘጠኝ ቢሊዮን ብር ድጎማ ያደርጋል። ሆኖም ግን ከተማ አስተዳደሩ ጤናው የተጠበቀ አምራች ዜጋ ማፍራትን ታሳቢ ያደረገ ለጤናው ዘርፍ የሚመጥን በጀት በጅቷል። ምንም እንኳን ከተማው ከሚፈልገው የጤና አገልግሎት አቅርቦት አንጻር የሚቀር ነገር ቢኖርም ባለፉት አምስት አመታት አበረታች ተግባሮች ታይተዋል።የተሰሩት ስራዎችም ባለፉት 50 አመታት ያልተሰሩ ናቸው ማለት ይቻላል።

ከጤና መሠረተ ልማት ግንባታ ጋር በተያያዘ ሌላው የተከናወነው ሥራ የመረጃ ሥርዓትን ማዘመን ነው። ከወረቀት አሰራር መውጣት መረጃዎችን በተደራጀ መልኩ ለመያዝና የተቀላጠፈ አገልግሎትም ለመሥጠት ከማገዙ በተጨማሪ ለክፍተቶች ፈጣን የእርምት እርምጃ ለመውሰድ፣ ለወረቀትና ለተያያዥ ጉዳዮች የሚወጣ ወጪንም ለማዳን ያግዛል። የዲጂታል ትግበራው በአብዛኛው የጤና አገልግሎት መስጫዎች ውስጥ የተከናወነ ሲሆን፣የቀሩትንም በማዳረስ ሙሉ ለሙሉ ዲጂታላይዝ ለማድረግ እየተሰራ ነው።

ከጽንስ ጀምሮ የሚደረግ ኢንቨስትመንት የሚያስገኘው ውጤት ከፍተኛ እንደሆነም ጥናቶችን መሠረት በማድረግ በዚህ ረገድም ከተማ አስተዳደሩ በቀዳማዊ የልጅነት እድገት

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

# ‹‹ መንግሥት በጤና ዘርፍ ትኩረት...

ከገጽ 7 የዞረ



ልማት ፕሮጀክት በመጀመር በትኩረት እየሰራ ይገኛል። በዚህ ፕሮጀክት ለራሱም ለሀገርም ጠቃሚ የሆነ ትውልድ ለማፍራት ምቹ የሆነች ከተማ በመፍጠር ከአፍሪካ ሀገራት ቀዳሚ ለመሆን ነው እየተሰራ ያለው።

ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ለማድረግም የቤት ለቤት የወላጅና የአሳዳጊዎች ምክር አገልግሎት የሚሰጡ ወደ አምስት ሺ ባለሙያዎች ተመልምለው ስልጠና እየተሰጠ ይገኛል። ከነዚህ ውስጥ 2 ሺ 500 ዎቹ ወደ ሥራ የገቡ ሲሆን፡- የተቀሩት እየሰለጠኑ ነው። ይህን ጅምርም ከአንድ ወር በፊት የክልል አስተዳደሮችና ከተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት የመጡ ከንቲባዎች የተገኙበት አንድ የልምድ ልውውጥና የተሞክሮ መድረክ ተካሂዶ በመልካም ጎኑ ተወስዷል። በተለይም ከተማ አስተዳደሩ ለሌሎች ልምድ ያካፈለበት መድረክ ነበርም ማለት ይቻላል ።

**አዲስ ዘመን፡- ከተማዋ የህክምና ቱሪዝም መዳረሻ እንድትሆንም የሚደረጉ ጥረቶች በምን ደረጃ ላይ ይገኛሉ ?**

**ዶክተር ዮሐንስ፡-** ሁሉንም የጤና አገልግሎት በመንግሥት ብቻ መሸፈን ስለማይቻል የግሉን ዘርፍ ማበረታታት አስፈላጊ ከመሆኑም በላይ አሁን ላይ መንግሥት አገልግሎት ሰጪዎችን ከማበረታታት አልፎ የቁጥጥር ስራም ይሰራል ። ይህ ግን በሰለጠነው ዓለም የለም ። በመሆኑም ከተማዋ የጤና ቱሪዝም ማዕከል እንድትሆን ማስቻል አስፈላጊ በመሆኑ ሜዲካል መንደር (ሲቲ) እንገነባለን ብለው ጥያቄ ለሚያቀርቡ አስፈላጊውን ሁኔታ እያመቻቸን ሲሆን በጤናው ዘርፍ ኢንቨስት ለማድረግ ጥያቄ ላቀረቡ 20 ለሚሆኑ ኢንቨስተሮች የመሬት አቅርቦት ተከናውኗል ።

እዚህ ላይ ጥያቄ ካቀረቡት ባለሀብቶች 13 ቱ በቡድን ሆነው ሜዲካል ሲቲ ለመገንባት ዝግጁ የሆኑ ናቸው። በአሁኑ ወቅትም ወደ ግንባታ ለመግባት አስፈላጊውን የቅድመ ዝግጅት ሥራ በማድረግ ላይ ይገኛሉ። በግል አገልግሎት እየሰጡ ያሉ ነባር ሆስፒታሎችም ለማስፋፊያ የሚሆን መሬት ጠይቀው ወደ 13 ለሚሆኑ ምላሽ ተሰጥቷል።

በዚህ ረገድ ክፍተቶች እንዳይኖሩም ክትትል ይደረጋል። ለአብነትም በየአመቱ አንዳንድ ሆስፒታል በመሥራት አምስት ሆስፒታሎችን ለመገንባት ቦሌ ላይ መሬት የተሰጣቸው ሆራ የተባለ ስያሜ ያላቸው ባለሀብቶች በገቡት ቃል መሠረት አምስቱን ሳይሆን፣ የአንዱን ብቻ ግንባታ ነው የጀመሩት። የጀመሩትን ብቻ እንዲያጠናቅቁ በከተማ አስተዳደሩ አቅጣጫ ተሰጥቶ እየሰራ ይገኛል።

እዚህ ላይ ካለፈው ተሞክሮ መውሰድ የሚቻለው ወደ ልማት ሳይገቡ መሬት ይዘው ረዘም ላለ አመታት የቆዩ አጋጥመዋል። ከተማ አስተዳደሩ በመንግሥትም ሆነ በግል ለግንባታ የተወሰደ ወደ ልማት ያልገባ መሬት ላይ እርምጃ እየወሰደ ይገኛል።

ከዚህ ቀደም ያለው ተሞክሮዎች የሚያሳዩት ባለሀብቶቹ መሬቱን ከወሰዱ በኋላ ነው ለግንባታ ዝግጅት የሚያደርጉት። ይሄ ደግሞ ወደ ሥራው እንዳይገቡ አድርጓቸዋል። አሁን ባለው አሰራር ግን ችግሩ እንዳይደገም በግልም ሆነ በተናጠል ለማልማት ጥያቄ የሚያቀርብ ያለውን የገንዘብ አቅም ጨምሮ በወረቀት ላይ በሰፈረ እቅድ(ፕሮፖዛል) መሰረት ነው ወደ ኢንቨስትመንቱ መግባት የሚችሉት።

**አዲስ ዘመን፡- በአንዳንድ የህክምና ዘርፍ ላይ ተኪ ባለሙያዎች የሉም የሚባል ነገር ይነሳል። ለአብነትም የአስክሬን ምርመራ የሚያካሂዱ ባለሙያዎችን ማንሳት እንችላለን ፡- እርስዎ በዚህ ላይ ምን ይላሉ ?**

**ዶክተር ዮሐንስ፡-** የዓለም ጤና ድርጅትም ሆነ ጤና ሚኒስቴር ባስቀመጠው መስፈርት (ስታንዳርድ) መሠረት አንድ የጤና ባለሙያ ለነዋሪው ጥመርታ ሲሰራ በከተማ አስተዳደሩ ውስጥ የሚገኙ በፌዴራልም በግልም የጤና አገልግሎት የሚሰጡትን ተቋማት ያካትታል። በከተማ አስተዳደሩ የሚገኙ የጤና ባለሙያዎች ከአጠቃላይ የከተማዋ ነዋሪ ጋር ያለው ጥመርታ ሶስት ነጥብ አራት አካባቢ ነው። በአጠቃላይ የጤና ባለሙያ ጥመርታ ከተቀመጠው መስፈርት በላይ ነው። እዚህ ላይ ክፍተት የለም።

በተተኪ ባለሙያዎች ዙሪያ ለተነሳው ጥያቄ በተለይም የአስክሬን ምርመራ የሚያደርግ ባለሙያ እንደ ከተማም ሆነ እንደ ሀገር እጥረት የለም። ቀደም ሲል በሀገር ውስጥ የፎረሲንክ ህክምና ትምህርት አይሰጥም ነበር። አገልግሎቱም ከኪዩባ ሀገር በሚመጡ ባለሙያዎች ነበር የሚሰጠው። አሁን ላይ ግን ቅዱስ ጳውሎስ ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ውስጥ ትምህርቱ እየተሰጠ ምርመራው ምኒሊክና አቤት ሆስፒታሎች ውስጥ በሀገር ውስጥ ባለሙያዎች እየተሰጠ ይገኛል።

በቀደሙት ጊዜያቶች ከነበሩት ጋር በንጽጽር ሲቀርብ እንደሀገር ባለሙያዎች እያፈራን በመሆኑ ክፍተቶችን ለመቀነስ ጥረት ይደረጋል ። አሁንም ግን ከፍተኛ ባለሙያ ወይንም ሰብእስፔሻሊስት የሚያስፈልጋቸው መስኮች ግን እንደተግዳሮት የሚነሳው የግብአት አቅርቦት እጥረት ነው። ለምሳሌ የልብ ቀዶ ህክምና፣ከአጥንት ዳሌ ሥብራት ቅያሬ ለማድረግ ካለመቻል፣ የጨረር ህክምና ጋር ተያይዞ በሚሰጡ አገልግሎቶች ዙሪያ አሁንም የአቅርቦት እጥረት በመኖሩ ታካሚዎች ለረጅም ጊዜ ወረፋ ይጠብቃሉ።

**አዲስ ዘመን፡- አንድ ታማሚ የሚከታተለው ሀኪም የተለያየ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በሚታዘዙ መድኃኒቶችና ሌሎችም ችግሮች እያጋጠሙ እንደሆነ ቅሬታዎች ይነሳሉ። እዚህ ላይ ምን ይላሉ?**

**ዶክተር ዮሐንስ፡-** እንዲህ አይነት ችግሮች የሚፈቱት አንድ ሀኪም እስከ መጨረሻው አንድን ታማሚ እንዲከታተል በማድረግ ሳይሆን፡- የታማሚውን የበሽታ ታሪክ በተደራጀ መልኩ ለመያዝ የመረጃ አያያዝ ሥርአትን በማዘመን ነው። ሀኪም ሲቀየር ህክምናው የተቀየረ አድርጎ ማሰብ ተገቢ አይደለም። ታማሚውን የሚያየው ሌላው ሀኪም ቀደም ሲል የነበረውን መረጃ መሠረት አድርጎ በመሆኑ ስጋቶችን መቀነስ የሚቻለው የመረጃ አያያዝን የተሻለ በማድረግ ነው።አንድ ሀኪም ያለው ክህሎትና የሥራ ልምድ እንዲዳብር በተለያዩ የህክምና ክፍሎች ተዘዋውሮ እንዲሰራ ይደረጋል።

**አዲስ ዘመን፡-የተገልጋዩን እርካታ ለማረጋገጥ እየተሰሩ ያሉ ስራዎች ምን ይመስላሉ?**

**ዶክተር ዮሐንስ፡-** የአገልግሎት ጥራትን ለማሻሻል፣ የተገልጋዩንም እርካታ ለመጨመር ዋን ስቶፕ ክሊኒክ የሚባል የአሰራር ሥርአት ተዘርግቷል። በዚህ የአሰራር ሥርአት ውስጥ ሰብስፖሻሊስት፣ስፔሻሊስት፣ሌሎችም ሀኪሞች ተካትተዋል። ታካሚው መመላለስ ሳይኖርበት በሁሉም ሀኪሞች ታይቶ አገልግሎቱን አግኝቶ ይሄዳል። ውሳኔ ሳያገኙ የሚቀሩ ታማማዎች እንዳይኖሩ ቅኝት (ራውንድ) ይደረጋል። በዚህ አሰራር የታካሚውን ቅሬታ ለመቅረፍ ጥረት እየተደረገ ነው። ቀድሞ በሚሰራ የበሽታ ልየታ ሥርዓት ቀጥታ ስፔሻሊስት ሀኪም የሚያየው ሆኖ ከተገኘ ታካሚው ስፔሻሊስት ሀኪም ጋር ይቀርባል።

የውጤት ተኮር ሥርዓት ትግበራ (ቢፒአር) ሲሰራ ታማሚዎችን ወይንም ታካሚዎችን ማዕከል ያደረገ ነበር። ቀደም ሲል የነበረው የህክምና ቡድን በጣም አነስተኛ በሆነ መልኩ ነበር የተደራጀው። በቢፒአሩ ግን ችግሮችን ሊፈታ በሚችል ከፍ ባለ አደረጃጀት ነው የህክምና ቡድን የተዋቀረው። በዚህ አሰራርም እያንዳንዱ የህክምና መስጫ ክፍሎች ባለቤት እንዲኖራቸው ተደርጓል። በተጨማሪም በተቀመጠው የህክምና አሰጣጥ መስፈርት መሠረት ህክምና መሰጠቱን የጥራት ተቆጣጣሪ በጤና ተቋማት ውስጥ ዳይሬክቶሬት ተቋቁሟል።

ሌላው ከጤና አገልግሎት መሻሻል ጋር የሚያያይዘው የመድኃኒት አቅርቦት ነው። በዚህ ረገድም ብክነትን የሚቀንስ፣ተጠያቂነትን የሚያሰፍን፣ ለብልሹ አሰራርም እንዳይጋለጥ የሚያደርግ የአሰራር ሥርዓት ተዘርግቷል። የፌዴራል ህክምናና መድኃኒት አቅርቦት ኤጀንሲ ከጤና ቢሮው ፋርማሲ ዳይሬክቶሬት ጋር ተናብበው የሚሰሩበት አሰራርም ተዘርግቷል። በዚህ አሰራርም አንዱ ተቋም ያለው መድኃኒት ምን አይነት እንደሆነ፣ እጥረት ያለበት ቦታ ደግሞ ከምችቱ ካለበት እንዲደርሰው በማድረግ ክፍተቶችን የመሙላት ሥራ እየተሰራ ነው።

ክፍተቶች ሲያጋጥሙ በተለይ ማህበረሰብ የጤና መድህን ኢንሹራንስ ተጠቃሚዎች ይጠይቁናል። በዚህ በኩል ሞጋች የሆነ ማህበረሰብ በመፍጠራችን አገልግሎታችንን ለማሻሻል አግዞናል። ለምሳሌ የማህበረሰብ የጤና መድህን ኢንሹራንስ ተጠቃሚዎች በከነማ የመድኃኒት አገልግሎት መስጫዎች እንዲጠቀሙ እድሉ ተመቻችቶላቸዋል። እነዚህ ሁሉ ሥራዎች ቢሰሩም በቂ ተብሎ እጅ አጣጥፎ ለመቀመጥ የሚያስችሉ እንዳልሆኑ ግንዛቤ ሊያዝ ይገባል።

**አዲስ ዘመን፡- ከግብአት አቅርቦት ጋር በተያያዘ በጣም አነስተኛ ከሆነ የእጅ ጓንት ጀምሮ ታካሚው ከውጭ እንዲገዛ የሚጠየቅበት አሰራር መኖሩን እኔም አጋጥሞኛል። በሀኪም የሚታዘዙ የላብራቶሪ ምርመራዎችም በአብዛኛው ወደ ውጭ ነው የሚላኩት የሚሉ ቅሬታዎች ይነሳሉ። እዚህ ላይ ምን ይላሉ?**

**ዶክተር ዮሐንስ፡-** የእጅ ጓንትን ጨምሮ መሠረታዊ የሚባሉ መድኃኒት አቅርቦቶች ላይ የሚስተዋል ችግርን በተመለከተ የጥናት ሥራ ሰርተን አነሰተኛ የሚባለው የመድኃኒት ዋጋ ገበያው ላይ መቶ በመቶ ነው ጭማሪ ያሳየው። እስከ አስር እጥፍ የጨመረ ግብአትም መኖሩም ተረጋግጧል። በተጋነነ ዋጋና በበቂ ሁኔታ አቅርቦት ካለመኖር ጋር ተያይዞ ችግሮች ይስተዋላሉ። ሌላው ጤና ጣቢያዎች በቂ በጀት የላቸውም። ቶሎ ይጨርሳሉ። አንዳንድ ጊዜ በጀትም ኖሮ ገበያ ላይ የማይገኙ ግብአቶች አጋጥመዋል። ኮቪድ 19 ቫይረስ ወረርሽኝ ከተከሰተ በኃላ ከፍተኛ እጥረት ያጋጠመው የጓንት አቅርቦት ላይ ነው። እስከ አራት እጥፍ ነው ዋጋው የጨመረው። የውጭ ምንዛሪ አቅርቦትም የራሱ የሆነ ተግዳሮት ፈጥሯል። እነዚህን ተግዳሮቶች ምክንያት በማድረግ ሰው ሰራሽ የሆነ ክፍተትም አይጠፋም። እነዚህ ሁሉ ተደራርበው ነው ችግሮች የሚፈጠሩት፡- ያም ሆኖ ግን የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት በመዘርጋት መፍትሄ ለመስጠት ጥረት እየተደረገ ነው።

አሁን ላይ ለሚነሱ ችግሮች በጤና ቢሮው በኩልም ሆነ በከተማ አስተዳደሩ ዘላቂ መፍትሄ ተደረጎ የተያዘው፡ - የህክምና አገልግሎቶችን በአጋርነት (ፓርትነርሺፕ) ውል በመግባት እንዲያቀርቡ (አውትሶርስ) ማድረግ ነው። በተለይም ህክምናቸው ወሰብሰብ ያሉና ከፍተኛ የህክምና መሳሪያ የሚያስፈልጋቸውን በውጭ አገልግሎት ለመፍታት ነው የታሰበው።

ችግሮች ቀጣይነት ስለሚኖራቸው የህክምና አይነቶችን ለይቶ በውጭ እንዲስተናገዱ በማድረግ ነው በዘላቂነት መፍታት የሚቻለው። ከመድኃኒት አቅርቦት ጋር የተያየዙ ችግሮችን ለመፍታትም ኢንቨስትመንት መሳብ ሌላው አማራጭ በመሆኑ በዚህ በኩልም በፌዴራልም በከተማ አስተዳደሩም ጥረቶች እየተደረጉ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ለከፍተኛ የህክምና አገልግሎት የሚውሉ እንደ ሲቲስካን ያሉ የህክምና መሣሪያዎች በመለዋወጫ እቃና በጥገና ምክንያት ያለ ሥራ መቀመጣቸው ይነገራል። እዚህ ላይም ሀሳብ ቢሰጡበት ?**

**ዶክተር ዮ ሐንስ፡-** ችግሩ ፈታኝ ሆኖ ነው የተገኘው። ይህንንም ልንወጣው የምንችለው በውጭ አገልግሎት ከሚሰጡ ጋር አብሮ በመሥራት ነው። በዚህ በኩል ያለውን ችግር ለመፍታት የኩላሊት እጥበት ላይ ተሞክሯል። በሌሎችም የህክምና አገልግሎቶች ላይ በተመሳሳይ በመተግበር ወደ ሥርዓቱ ለመግባት ነው የታቀደው።

**አዲስ ዘመን፡- ለህክምና የሚጠየቀው ዋጋ ውድ እየሆነ መምጣትም አንዱ የቅሬታ ምንጭ ነው ።**

**ዶክተር ዮሐንስ፡-** ከ30 እስከ 50 በመቶ የዋጋ ማሻሻያ ተደርጓል። ሆኖም ግን በመንግሥት የጤና አገልግሎቶች የሚጠየቀው ክፍያ የሚሠጠውን አገልግሎት የሚመልስ አይደለም። መክፈል የማይችለው በማሕበረሰብ የጤና አገልግሎት ኢንሹራንስ በመርዳት፣መክፈል የሚችለው ደግሞ በተመጣጣኝ ዋጋ አገልግሎቱን እንዲያገኝ ነው የተደረገው። እንደውም መክፈል ለሚችለውም ህብረተሰብ ድጎማ ተደርጓል ማለት ይቻላል። በተለይ ደግሞ ለእናቶችና ህፃናት በነፃ ነው አገልግሎት የሚሰጠው።

**አዲስ ዘመን፡- በአጠቃላይ በተግዳሮትና በጥንካሬ የሚነሱ ነገሮች ካሉ አያይዘውም ከህክምና ተቋማት የሚወገዱ ደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ ብክለት እንዳያስከትል እየተደረገ ስላለው ጥንቃቄ ቢገልጹልን?**

**ዶክተር ዮሐንስ፡-** በጥንካሬ የማነሳው ተጠያቂነትን ሊያሰፍን የሚችል የመረጃ አያያዝ ሥርዓት መዘርጋቱ ሲሆን ቀደም ሲል አንድ ሰራተኛ ፊርማ መፈረሙ እንጂ ምን ሠራ የሚለው አይታይም ነበር። አሁን አንድ ባለሙያ የሰጠው አገልግሎት ነው የሚለካው።

ሰዎች በሰሩት ልክ እንዲበረታቱ የሚደረግበት አሰራር መኖር እንዳለበት ታምኖበታል። በሥነምግባር ብልሹ የሆኑትን ተጠያቂ በማድረግ ሥራዎች ይሰራሉ። የህክምና ስህተት ተፈጽሞ ሲገኝ ባለሙያው በምግብና መድኃኒት ቁጥጥር ባለሥልጣን በኩል ተጠያቂ የሚሆንበት አሰራር በመዘርጋቱ በዚህ በኩልም ተገቢው ሥራ መሰራቱ በጥሩ ጎን ይወሰዳል።

ከቆሻሻ አወጋገድ ጋር ተያይዞ ለተነሳው፡- አሁን ላይ እየተሰራበት ያለ ቢሆንም ጊዜው የሚጠይቀው ዘመናዊ የቆሻሻ ማስወገጃ ወይንም ማቃጠያ ያስፈልጋል።ለጤና ተቋም ብቻ ሳይሆን ኬሚካል ለሚጠቀሙ ተቋማትም ጭምር ያገለግላል። ቆሻሻ የሚወገድብት አንድ ማእከል እንደሚያስፈልግም በከተማ አስተዳደሩ ግንዛቤ ተይዞ ታቅዷል። ትልቅ ኢንቨስትመንት ስለሚፈልግም ወደፊት ከአጋር ድርጅቶች ጋር መሥራት የሚያስፈልግበትም ሁኔታ ሊኖር ይችላል።

**አዲስ ዘመን፡- ባለሙያዎችን በሥራ ላይ ለማቆየት የተሰሩ ሥራዎች ካሉ ይገልጹልኝና በዚሁ እናጠናቅቅ**

**ዶክተር ዮሐንስ፡-** የጤና ባለሙያዎች ሊመሰገኑ ይገባቸዋል። ባለፉት አምስት አመታት እንደ ከተማም እንደሀገርም ኮቪድን ጨምሮ በርካታ ፈተናዎች አጋጥመዋል። የጤና ባለሙያው ህይወቱን እስከ መስጠት ነው ሙያዊ ግዴታውን ሲወጣ የነበረው። ጦርነት በተካሄደባቸው ቦታዎች እኔን ጨምሮ በመሄድ አገልግለናል።

ከተማ አስተዳደሩ ይህን የሚተጋ ባለሙያ የቤት ኪራይና የተለያዩ ድጎማዎችን በማድረግ ለማገዝ ጥረት አድርጓል። ማገልገል መታደል ነው። በጤናው ዘርፍ ለውጦች ሲመጡ ባለሙያው ከሚከፍለው ገንዘብ ይልቅ በውጤቱ ሊደሰት ይገባል።

አዲስ ዘመን፡-አመሰግናለሁ።

ዶክተር ዮሐንስ፡- እኔም አመሰግናለሁ።

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## የአምራች ዘርፉን ችግሮች መፍታው የአቅም ልማት ስትራቴጂ

አንተነህ ቸሬ

ኢትዮጵያ በኢንዱስትሪ ዘርፍ እምቅ አቅም ያላት ሀገር ናት። የሀገሪቱ አምራች ኃይል አቅም፣ ተፈጥሯዊ አቀማመጥ፣ ሕጋዊ ማዕቀፎችና ለዘርፉ እድገት አወንታዊ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ ሌሎች መልካም አጋጣሚዎችና አስቻይ ሁኔታዎችም አሏት።

ሀገሪቱ ለኢንዱስትሪው ያላትን ይህን አቅም በመጠቀምና ከዚሁ ዘርፍ የሚገኘውን ገቢ በማሳደግ ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ የምታደርገውን መዋቅራዊ ሽግግር እውን ለማድረግ ባለፉት ዓመታት በርካታ ተግባራትን አከናውናለች። በዓይነትም ሆነ በብዛት የሚታወቁት እነዚህ በርካታ የዘርፉ ችግሮች፡- የመንግሥትን፣ የግሉን ዘርፍና በአጠቃላይ የሕዝቡን የተቀናጀ ጥረት የሚፈልጉ እንደሆኑ በተደጋጋሚ ሲነገር ቆይቷል። ለችግሮቹ ዘላቂ መፍትሔ ለመስጠት ብዙ ሙከራዎች ተደርገው የማይናቁ ውጤቶች ቢመዘገቡም፣ - ከሀገሪቱ አቅምና ከችግሮቹ ስፋት አንፃር ግን መፍትሔዎቹ የሚፈለገውን ያህል ውጤት ሊያስገኙ እንዳልቻሉ በተደጋጋሚ ተገልጿል።

በፖሊሲ ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት የኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲ ጥናትና ምርምር ዘርፍ የሀገር ውስጥ የግል ባለሀብቶች በአምራች ኢንዱስትሪው ውስጥ ስላላቸው ሚና ይፋ ባደረገው ጥናት ላይ እንደተመለከተው፣ ምንም እንኳ መንግሥት ለአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ የተለየ የማበረታቻና ድጋፍ ፓኬጆች አዘጋጅቶ ወደ ሥራ የገባ ቢሆንም፡- አብዛኛው የሀገር ውስጥ የግል ባለሀብት የመጀመሪያ ምርጫው አምራች ኢንዱስትሪው ሳይሆን የንግድ፣ የሪል እስቴትና የአገልግሎት ዘርፎች ናቸው። ለዚህ ደግሞ ጥናቱ በምክንያትነት የጠቀሳቸው ቀድመው በአምራች ኢንዱስትሪ የተሰማሩ አብዛኛዎቹ ባለሀብቶች በብዙ ችግሮችና ማነቆዎች ምክንያት ውጤታማ ባለመሆናቸው ወደ ዘርፉ መግባት ለሚፈልግ ባለሀብት ጥሩ አርአያ መሆን አለመቻላቸውን እና በንግድና አገልግሎት ዘርፎች የሚገኘው ትርፍ በጣም የተጋነነና ሳቢ መሆኑን ነው።

ዘርፉ በግብዓት (ጥሬ ዕቃ)፣ በሰው ኃይል፣ በቦታ፣ በኃይል፣ በፋይናንስና በውጭ ምንዛሬ አቅርቦት ችግሮች ተተብትቦ የተያዘ ነው። የኃይል አቅርቦት፣ የውጭ ምንዛሬ እና የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት ተደጋግመው የሚጠቀሱ ችግሮች ናቸው። አብዛኞቹ የማምረቻ ዘርፎች ከ25 እስከ 50 በመቶ የሚሆነውን ጥሬ እቃዎቻቸውን የሚያገኙት ከውጭ ሀገራት በማስገባት ነው። አምራቾቹ ይህን ከውጭ የሚገባ ጥሬ እቃ በበቂ መጠን ለማግኘት የሚያስፈልገው የውጭ ምንዛሬ ከፍተኛ እጥረት ስላለባቸው የምርት ግብዓቶቻቸውን በበቂ ሁኔታ እንዳያገኙና በሙሉ አቅማቸው እንዳያመርቱ ያደርጋቸዋል።

ከውጭ የሚገቡ የምርት ግብዓቶች አቅርቦት አስተማማኝ አለመሆንም ሌላው የዘርፉ ችግር ነው። በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚፈጠሩ ፖለቲካዊ ክስተቶች ግብዓቶቹ በበቂ ሁኔታ እንዳይገኙ ማድረጋቸው በአምራቾች ላይ ተጨማሪ ጫና ይፈጥራል። የገበያ እድል እጦትም አምራች ኢንዱስትሪዎች በሙሉ አቅማቸው እንዳያመርቱ እንቅፋት ሆኗል። ለአንዳንድ ምርቶች በቂ የሆነ የሀገር ውስጥ ገበያ አማራጭ አለመኖር ኢንዱስትሪዎቹ በአቅማቸው ልክ እንዳያመርቱ ምክንያት ተደርጎ ይጠቀሳል። የብድር አቅርቦትም ሌለው የዘርፉ ችግር ነው። አምራቾች የጥሬ ገንዘብ እጥረት ሲገጥማቸው የምርት ግብዓቶችን በበቂ ሁኔታ አሟልቶ ለማምረትና ለገበያ ለማቅረብ ይቸገራሉ።

በእነዚህ ችግሮች ምክንያት ኢንዱስትሪዎች እያመረቱ ያሉት ከአቅማቸው በታች እንደሆነ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር መረጃዎች ያሳያሉ። በአሁኑ ወቅት የአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ ከአጠቃላይ ሀገራዊ ምርት የሰባት በመቶ ድርሻ ያለው ሲሆን በቀጣይ 10 ዓመታት ይህን ድርሻ ወደ 17 ነጥብ ሁለት በመቶ ለማሳደግ ታቅዷል። ከዚህ በተጨማሪም አሁን ያለውን ከ55 በመቶ ያልበለጠውን የኢንዱስትሪዎች የምርታማነት አቅም ወደ 85 በመቶ የማድረስ እቅድም ተይዟል።

የግብዓት (ጥሬ ዕቃ)፣ የሰው ኃይል፣ የቦታ፣ የኃይል፣ የፋይናንስና የውጭ ምንዛሬ አቅርቦት ችግሮችን በአስተማማኝነት ለመፍታት የአምራች ዘርፉን አቅም የሚያሳድግ የአቅም ልማት ስትራቴጂ ማዘጋጀትና መተግበር አንዱ ወሳኝ የመፍትሔ ርምጃ ተደርጎ ተለይቷል። በዚህ መነሻነትም የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ከባለድርሻና አጋር አካላት ጋር በመተባበር የዘርፉን ችግሮች በመለየት ወደ መፍትሔው የሚያደርሱ አሰራሮችን የሚመራ የአምራች ዘርፍ የአቅም ልማት ስትራቴጂ አዘጋጅቷል።

ስትራቴጂው የግሉ ዘርፍ በአምራች ኢንዱስትሪው እድገት ዋና ባለድርሻ እንዲሆን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተፅዕኖ ያላቸው አካላት ኃላፊነታቸውን በአግባቡ እንዲወጡ፣ መንግሥት ለባለሃብቶች በቂ ድጋፍና ክትትል እንዲያደርግ፣ ለባለሀብቱ የተፈቀዱ ማበረታቻዎች ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ እንዲደረጉ እንዲሁም አምራች ኢንዱስትሪው በግል ባለሀብቶች ተመራጭ ዘርፍ እንዲሆን ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር እንዲያግዝ ታስቦ የተዘጋጀ የአሰራር መመሪያ ነው።

በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የስትራቴጂክ ጉዳዮች ሥራ አስፈጻሚ አቶ ጥላሁን ዓባይ እንደሚገልፁት፣ የአምራች ኢንዱስትሪ አቅም ግንባታ ስትራቴጂ ማዘጋጀት ያስፈለገው በመንግሥትና በግል ተቋማት ያለው ተቋማዊ አቅም (የሰው ሀብት፣ አደረጃጀት፣ የአሠራር ሥርዓት፣ መሠረተ ልማት) በርካታ ክፍተቶች ያሉበት በመሆኑ ነው። ስትራቴጂው የአምራች ኢንዱስትሪ ባለድርሻ አካላት የዘርፉን ችግር በሚገባ ተረድተው የተሟላና ውጤታማ የሆነ ድጋፍ ለመስጠት እንዲሁም ዘርፉ ያለበትን አጠቃላይ ደረጃ ለመገምገም ያስችላል ተብሎ ይጠበቃል።

ከዚህ በተጨማሪም ስትራቴጂው ትልቅ አቅም ያላቸውን አምራቾች ለመሳብ፣ ከሌሎች ሀገራት ጋር ተወዳዳሪ ሆኖ ለመገኘት፣ የዘርፉ ተቋማዊ አቅም ሙሉ ቁመና እንዲኖረው ለማድረግ፣ ለውጦችን ቀጣይና ዘላቂ ለማድረግ እና በዘርፉ ያለውን የእውቀት፣ የአመለካከትና የክህሎት ክፍተት ለመሙላት ያግዛል። በአጠቃላይ ስትራቴጂው የግሉ ዘርፍ በአምራች ኢንዱስትሪው የምጣኔ ሀብት ድርሻ ውስጥ ትልቁን ሚና እንዲወጣ የሚያስችል መደላድል ለመፍጠር እገዛ እንደሚያደርግና በ10 ዓመቱ የልማት እቅድ በማምረቻው ዘርፍ የተቀመጠውን መዋቅራዊ ሽግግርን የማሳካት እቅድን እውን ለማድረግ ትልቅ ሚና እንደሚኖረው አቶ ጥላሁን አመልክተዋል።

‹‹ወደፊት የግል ዘርፉ በአምራች ኢንዱስትሪው ትልቁን ሚና እንዲጫወት ይፈለጋል። ስለሆነም ስትራቴጂው የግሉ ዘርፍ የራሱን አደረጃጀት አጠናክሮ እንዲሰራ ማድረግን ጨምሮ የዘርፍና የሙያ ማኅበራት እንዲጠናከሩ፣ ተወዳዳሪነት እንዲጎለብት፣ የቴክኖሎጂ አስተዳደር ብቃት እንዲያድግ እና የዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስር እንዲጠነክር ትልቅ ሚና ይኖረዋል›› ይላሉ። በስትራቴጂው ትግበራ በዘርፉ ቁልፍ ሚና ያላቸው ባለድርሻ አካላት በእውቀት ላይ የተመሠረተና ኢንዱስትሪውን መሠረት ያደረገ ድጋፍ በሚሰጡበት ሂደት ላይ መሠረታዊ ለውጥ ይመዘገባል ተብሎ እንደሚጠበቅም አቶ ጥላሁን ጠቁመዋል።

የኢንዱስትሪ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ታረቀኝ ቡሉልታ በበኩላቸው፣ ስትራቴጂው የአመራር አቅምን በማጎልበት መዋቅራዊ የምጣኔ ሀብት ሽግግሩን ለማሳካት እንደሚረዳ ይናገራሉ። እርሳቸው እንደሚሉት፣ የኢንዱስትሪ ዘርፍ የብዙ ዘርፎችን ተሳትፎ የሚፈልግ በመሆኑ ስትራቴጂው

> **ስትራቴጂው ትልቅ አቅም ያላቸውን አምራቾች ለመሳብ፣ ከሌሎች ሀገራት ጋር ተወዳዳሪ ሆኖ ለመገኘት፣ የዘርፉ ተቋማዊ አቅም ሙሉ ቁመና እንዲኖረው ለማድረግ፣ ለውጦችን ቀጣይና ዘላቂ ለማድረግ እና በዘርፉ ያለውን የእውቀት፣ የአመለካከትና የክህሎት ክፍተት ለመሙላት ያግዛል**

ይህን ዘርፈ ብዙ ተሳትፎ ለማቀናጀት በጎ ሚና ይኖረዋል። የስትራቴጂው ትግበራና ስኬት ከዘርፎች ቅንጅት በተጨማሪ የማኅበረሰብ ንቅናቄ ይፈልጋል። ‹‹የኢንዱስትሪ ዘርፍ እድገት ለኢኮኖሚ ችግሮች ፍቱን መድኃኒት ነው›› የሚሉት አቶ ታረቀኝ፣ ስትራቴጂውን የዘርፉን ችግሮች በመለየትና መፍትሔዎችን በማመላከት የኢኮኖሚውን ችግሮች ለማቃለል እገዛ እንደሚያደርግ ይገልፃሉ።

የስትራቴጂዎች መዘጋጀት ችግሮችን ለማቃለል ሁነኛ ግብዓት እንደሚሆን የሚናገሩት የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል፣ ትግበራውም ከዝግጅቱ የበለጠ ትኩረትና ክትትል የሚፈልግ ጉዳይ እንደሆነ ይናገራሉ። ‹‹ብዙ ጊዜ ‹በዚህ ጊዜ ይህን እናከናውናለን› ብለን እናቅዳለን፡- ‹እንዴት ይከናወናል/ይሳካል?› የሚለው ጥያቄ ግን አጥጋቢ ምላሽ አያገኝም። አንድ የእቅድ ዘመን ያለስኬት አጠናቅቀን፣ ሁለተኛውን የእቅድ ዘመን ስንጀምር በመጀመሪያው የእቅድ ዘመን እቅዱ ያልተሳካበትን ምክንያት ለይቶ ችግሩን ሊፈታ የሚችል አቅጣጫ በበቂ መጠን ማስቀመጥ ያስፈልጋል›› ሲሉ ያስገነዝባሉ።

በስትራቴጂዎች ዝግጅትና ትግበራ ላይ የሚፈጠሩ ክፍተቶች ችግሮች ሳይፈቱ ለበርካታ ዓመታት እንዲቀጥሉ ምክንያት እንደሚሆኑ ሚኒስትሩ የኢንዱስትሪ ፖሊሲውን በማስረጃነት ይጠቅሳሉ። ‹‹ነባሩን የኢንዱትሪ ፖሊሲ በዝርዝር ስንመለከተው ይዘቱ ጥሩ ነው። ነገር ግን የፖሊሲውን ዓላማ ሊያሳኩ የሚችሉና ከፖሊሲው ቀጥለው መውጣት የነበረባቸው ስትራቴጂዎች በበቂ ሁኔታ ተዘጋጅተው አለመተግበራቸው ትልቅ ጉድለት ነበር። ይህም ብዙዎቹን እቅዶች አየር ላይ የቀሩና የተንሳፈፉ ያደርጋቸዋል።›› ብለዋል።

‹‹ፖሊሲዎች ከተዘጋጁ በኋላ የፖሊሲዎቹን ማስፈፀሚያዎች ማዘጋጀትና መተግበር ያስፈልጋል›› ያሉት ሚኒስትሩ፣ ለእዚህም የማስፈፀም አቅምን ፈትሾ አቅጣጫ ማስቀመጥ እንደሚስፈልግ ይናገራሉ። ‹‹ኢንዱስትሪ እውቀት ይፈልጋል፡- ዘርፉን ስኬታማ ለማድረግ በእውቀት የታገዘ አሰራር መከተል ያስፈልጋል። ስትራቴጂዎችን ማዘጋጀትና መተግበር ለዚህ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል›› ይላሉ።

በትግበራ ያልታገዘ የስትራቴጂዎች ዝግጅት ፋይዳ እንደሌለው የሚገልፁት አቶ መላኩ፣ የአምራች ዘርፍ የአቅም ልማት ስትራቴጂ መዘጋጀቱ ብቻውን ለውጥ እንደማያመጣ ያስረዳሉ።

እርሳቸው እንደሚሉት፣ ስትራቴጂዎች ወደ መፍትሔ የሚወስዱ መንገዶች በመሆናቸው መፍትሔው ላይ ለመድረስ ስትራቴጂዎችን በሙሉ አቅም መተግበር ያስፈልጋል። ችግሮችን ለመፍታት የችግሩን መነሻና መድረሻ መረዳት ያስፈልጋል። መፍትሔ የሚገኘው በስትራቴጂዎች ትግበራ ነው። የስትራቴጂው ዝግጅት ብዙ ገንዘብና የሰው ኃይል ተመድቦ የተከናወነ በመሆኑ ሰበብና ምክንያት መፍጠር ሳያስፈልግ ለትግበራው ቁርጠኛ ሆኖ መሥራት ያስፈልጋል። ስትራቴጂዎች ለተሻለ አፈፃፀም እገዛ ያደርጋሉ ማለት እንጂ ከችግር ፍፁም የፀዱ ናቸው ማለት እንዳልሆነና በሂደት የሚደረጉ ማሻሻያዎች ሊኖሩ እንደሚችሉም ያመለክታሉ።

ከዚህ በተጨማሪም አቶ መላኩ የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፉ በርካታ መሰናክሎች እንዳሉበትና የሀገሪቱ አቅምና የገበያ ፍላጎትም ከዘርፉ አሁናዊ አፈፃፀም በላይ እንደሆነ ጠቁመው፣ በ‹‹ኢትዮጵያ ታምርት›› ንቅናቄ የተገኙ ውጤቶችን ዘላቂ ለማድረግ ለኢንዱስትሪዎች የሚደረጉትን ድጋፎች በብዛትም ሆነ በጥራት መጨመር እንደሚገባ በአፅንዖት ይገልፃሉ።

የሀገሪቱን የምጣኔ ሀብት መዋቅር ከእርሻ መር ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ ለማሸጋገር የሚያግዙ በርካታ መልካም አጋጣሚዎችና እድሎች እንዳሉ አይካድም። ይሁን እንጂ እነዚህን መልካም አጋጣሚዎች በመጠቀም የኢኮኖሚውን መዋቅራዊ ሽግግር ለማሳካት የተከናወኑ ተግባራት ሀገሪቱ ካላት አቅምና ፍላጎት የሚመጣጠኑ በመሆናቸው ለወቅቱ የሚመጥን ተግባራዊ ምላሽ መስጠት እጅግ አስፈላጊ ነው። ለዚህ ደግሞ የአምራች ዘርፉን ችግሮች መፍታት ከፍተኛ ትኩረት የሚሻ የመፍትሔ አቅጣጫ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። የአምራች ዘርፉን ችግሮች በዘላቂነት ለመፍታት ደግሞ የዘርፉ አጠቃላይ አሰራር የሚመራባቸውን አስፈላጊ ስትራቴጂዎችን ማዘጋጀትና በብቃት መተግበር ይገባል።

## ጎሜ

# ራስን ከዘመን ጋር ማስታረቅ

**የፌኔት እናት**

ሶስቱ ጓደኛሞች ከሌላ ጊዜ ለየት ያለ ቦታ መሔድ ፈልገዋል። ቀድመው በመነጋገራቸው ጋባዡ ተሰማ መንግስቴ የሚያውቀው መዝናኛ ቤት ሊጋብዛቸው ሁለቱም ጋር ደወለ። ዘውዴ መታፈሪያ እና ገብረየስ ገብረማርያም አዲስ ቤት በመግባት ጓደኝነታቸውን ለማደስ በመጓጓታቸው የተሰማን የሥልክ ጥሪ ተከትለው ወዲያው ተገኙ። ገና ሳይመሽ በጊዜ ከማምሻ ግሮሰሪ ውጪ፤ አለ የተባለ በዘመኑ አለኝ የሚል ሰው የሚጠጣውን መጠጥ ለመጠጣት እና በሰፊው ለመዝናናት በተቀናጣው መጠጥ ቤት ተገናኙ።

መቀመጫው እንደማምሻ ግሮሰሪ ደረቅ ወንበር ሳይሆን የተቀናጣ ሶፋ ነው። ገና በጊዜ በመግባታቸው ብዙ ሰዎች እና ሰፊ መስተንግዶ አላገኙም። እየቆየ ቤቱ መሙላት ሲጀምር ግን መስተንግዶ ተቀላጠፈ። የሙዚቃ ባንድ ቆሞ ዘፋኞች በየተራ እየወጡ መዝፈን ጀመሩ። አስተናጋጆች ሳይጠሩ፤ ‹‹ ምን እናምጣ? ምን ይጨመር?›› እያሉ ተክተለተሉ። አሻሻጭ ሴቶች ተኮለኮሉ። ለጠጪዎች ‹‹ ይህ መጠጥ እኮ ምርጥ ነው። ይህኛው ከዚህኛው ይሻላል። ያንን አምጡላቸው ይህንን ቀይሩላቸው።›› እያሉ በየጠረጴዛው የሚዞሩት አጫፋሪዎች፤ ምንም እንኳ ተኳኩለው መልካቸው ቢያምርም፤ ዘውዴ ግን ትኩረት ነፈጋቸው ።

ዘፋኞቹ ደጋግመው ተቀራራቢ ዘፈን ይዘፍናሉ። መጠጡም ሆነ ዘፈኑ አጠቃላይ የቤቱ ሁኔታ ዘውዴ እና ገብረየስን ብዙም አላዝናናቸውም። ተሰማ ግን እጅግ ደስ ብሎት አልፎ አልፎም ሲጨፍር ነበር። ብዙም ሳይቆይ ዘውዴ መውጣት ፈለገ፤ ነገር ግን ጓደኞቹ አልፈቀዱለትም። ተሰማ የዘውዴ አለመደሰት አልገባውም፤ እንደ እርሱ የተደሰተ መስሎት ነበር። የሚወደው ዘፈን ሲዘፈን ተሰማ ተነስቶ መጨፈር ቀጠለ። ገብረየስ ለዘውዴ፤ ‹‹እኛ ባንደሰት እንኳ እርሱ ሲደሰት ለማየት መፍቀድ አለብን። ያለበለዚያ ጓደኝነት ምንድን ነው?›› ብሎ ለጓደኛቸው ሲሉ እንዲቆዩ ገብረየስ ዘውዴን ጠየቀው።

ዘውዴ የተለመደ ግትርነቱን ማንፀባረቅ ጀመረ። ‹‹ ምንም ነገር የሚያስደስተው በጋራ ሁሉንም ሲያዝናና ነው። ለጋራ የማይሆን ነገር ያስጠላል። ከመታደስ ይልቅ የባሰ ያስረጃል፤ ከማስማማትና ከማቀራረብ ይልቅ ያቃቅራል፤ ያራርቃል።›› ሲል ገብረየስ ግን መለስ ብሎ፤ ‹‹ ዛሬ ፖለቲካ አይደለም። ዛሬ ፍሬ ነገሩ መዝናናት ነው። የጋራ ጥቅም፤ የጋራ ዕድገት የምትለውን ነገር ለዛሬ ተወት አድርገው። ተሰማ በቀናነት ሊያዝናናን ሞከረ፤ ነገር ግን ሁኔታው እኛን የሚያዝናና አልሆነም። በዚህ ጊዜ እርሱ ሲዝናና እያዩ መደሰት ይሻላል።

እኛም ከማምሻ ግሮሰሪ ትንሽ ራሳችንን ነጠል አድርገን እንየው። በተሰማ ስምም ቢሆን፤ ሌላውን ዓለም እንቃኝ። ሁሉን ነገር ደፍነህ፤ ብርሃን ቢሆን እንኳ የሚታይህ በፖለቲካ አይን ፅልመት ሆኖ ነው። ከብዙ ሰላም ይልቅ፤ ስለትንሿ ጦርነት እያሰላሰልክ ሰውነትህን አደከምክ። አሁን ስለአረጀው ሃሳብ ስለሰው ልጆች መሞት፤ ስለጦርነት ሳይሆን ስለሰው ልጆች ደስታ ማሰብ ጀምር፤ የዛን ጊዜ መድከምህ ቀርቶ ትታደሳለህ፤ መዛልህ ቀርቶ ትጠነክራለህ።

እባክህ ቢያንስ አንዳንድ ቀን ስለሰላም አስብ፤ የሰዎችን ደስታ ለማየት በእነሱ ደስታ ደስተኛ ለመሆን ሞክር። ዘመንህን ወደ ኋላ ከመጎተት ከዘመን ጋር ለዛውም በሰላማዊ መንገድ ለመሮጥ ጥረት አድርግ። ከጊዜውም ከሰውም ጋር ተጣልተህ አይሆንም። ምናልባት ከሰው ጋር ለመታረቅ ስትሞክር ከዘመኑም ጋር ትታረቃለህ።

**ራሱን በራሱ የሚያርም ከሰፊው ሕዝብ ጋር የሚጣመር በእርግጥም ከዘመን ጋር ለመታረቅ የፈቀደ ነው፡፡ ስህተት ይኖራል፤ ስህተቱን ለማረም ዝግጁነት ካለ አንተም ያለፈው ላይ ተተክለህ ከምታላዝን ቢያንስ አሁን ዛሬ ብቻ ያለውን በጎ ነገር አስተውለህ ከጊዜው ጋር ትታረቃለህ ማለት ነው**

ከዘመኑ ጋር ስንታረቅ ምናልባት የምናስበው ደስታ እና ሰላም ይሆናል። በዚህ መንገድ ብንታደስ ይሻላል።›› አለው።

ዘውዴ በበኩሉ፤ ‹‹ እኔ ከዘመን ጋር ለመታረቅ፤ ስለሰላም ለማሰብ እና ሰላም እንዲሆን ከመመኘት አልፌ ስለሰላም ለፈጣሪዬ እፀልያለሁ። እኔ አንዱ ብቻውን ከሚበላ እና ከሚኖር፤ ሁሉንም ያሳትፍ። አንዱ እየሞተ ሌላው ከሚገድል ሰላማዊ መንገድን እንምረጥ ሁላችንም እንሥራ፤ ሁላችንም እንብላ እና ሁላችንም በሰላም እንኑር እያልኩ ነው። ያለፈ ጥፋት ቢኖር እንኳ ማፈናቀል እና በቀል የሚያመጣው መልካም ውጤት አይኖርም። የሚሻለው ተመካክሮ ከዘመኑ ጋር ታርቆ፤ ያለፈውን ለታሪክ ትቶ ወደ ፊት መቀጠል ብቻ ነው። ነገር ግን ይህንን ሃሳብ አንቀበልም የሚሉ ትዕቢተኞችን ሳይ የሚፈፅሙትን ስህተት ሳስብ ያመኛል። ምንም ማድረግ አልችልም። አንተ እንዳልከው ሁሉ ነገር በብርሃን ተቃራኒ በፅልመት ውስጥ ሆኜ እንዳይ ያስገድደኛል።›› ሲል ሙዚቃው በማለቁ ተሰማ ጭፈራውን ጨርሶ ተቀላቀላቸው።

ገብረየስ ‹‹ በእርግጥ ትክክል ብለሃል። ሁላችንም አብረን ሰርተን፣ በልተን መኖር አለብን። ነገር ግን ሰዎች የተለያየን ነን። ለጋራ ጥቅም ከመሥራት እና ከማሰብ ይልቅ ያለፈውን ታሪክ እየጠቀሱ፤ በሃይል ፍላጎታቸውን ለመጫን የሚጥሩ ደካሞች የሉም ማለት አይቻልም። ነገር ግን ፍላጎትን ለማሳካት ወንድም ላይ ቃታ መሳብ በምንም በኩል ከማንም ጋር አያኗኑርም። ፍፁም የሰላም መደፍረስ እና ሞትን ማስቀረት ተገቢ ነው። ስለዚህ ጉዳይ ለምን አሰብክ ጭራሽ ማሰብ አልነበረብህም ማለት አልችልም። ምክንያቱም ሆን ተብሎም ባይሆን ተደጋጋሚ ስህተቶች ይኖራሉ። ነገር ግን ራሳችንን ከስህተት ነጻ ለማድረግ በማያቋርጥ መልኩ ራሳችንን ማረም አለብን።

ራሱን በራሱ የሚያርም ከሰፊው ሕዝብ ጋር የሚጣመር በእርግጥም ከዘመን ጋር ለመታረቅ የፈቀደ ነው። ስህተት ይኖራል፤ ስህተቱን ለማረም ዝግጁነት ካለ አንተም ያለፈው ላይ ተተክለህ ከምታላዝን ቢያንስ አሁን ዛሬ ብቻ ያለውን በጎ ነገር አስተውለህ ከጊዜው ጋር ትታረቃለህ ማለት ነው። አንድን ሰው ከሩቅ ሆነህ መልኩን እና ፀባዩን ሳታውቅ መጥላት ትልቅ ስህተት ነው። ቀርበህ ማየት አለብህ። ቀርበህ ማየት ካቃተህ ደግሞ ቢያንስ በደፈናው ከመጥላት መታቀብ ይገባሃል። ሌላውም አንተም እኔም ሁላችንም ከዘመኑ ጋር ለመታረቅ ራሳችንን በየጊዜው በደንብ ማረም አለብን። ይህ እያንዳንዳችንን የሚመለከት ጉዳይ ነው።›› አለው።

ተሰማ በበኩል፤ ‹‹ እንደው በጣም የምንገርም ሰዎች ነን። ‹ማምሻ ቦታ ቀይረን፤ ራሳችንን እናድስ ከጊዜው ጋር እንራመድ› ብለን ተነጋግረን ዞረን ያው ነን። ቢያንስ ምናልባት ዛሬ እንኳ ፖለቲካ ቢቀርብን። ምናለበት መዝናናት ስናስብ፤ ትኩረታችን መዝናናት ላይ ብቻ ለምን አይሆንም? ከሥራችን እና ከኃላፊነታችን እየወጣን በማያገባን እየገባን ልባችንን እና ምኞታችንን ሙሉ ንግግራችንን ፖለቲካ አድርገነው እየተሰቃየን ፣ ስቃያችን ሲያዝለን ወጣ ብለን ከመታደስ ይልቅ የነበርንበት ላይ እየተንከባለልን ዘመናችንን እናሳልፋለን።ደግሞስ ሁሉም ሰው እኮ እንዴት የፖለቲካ ጠበብት መሆን ይችላል።ፖለቲካውን ለፖለቲከኞች ብንተውላቸው የሚሻል ይመስልኛል ›› አለ።

ዘውዴ በመዝናኛ ቦታም ሆነ ሥራ ላይ ሰዎች ስለፖለቲካ የሚያወሩት ፈልገው ሳይሆን ሁኔታው አስገድዷቸው መሆኑን ለማስረዳት፤ ‹‹ ሰው ስለመዝናናትም ሆነ ስለ ሥራ የሚያስበው ሰላም ሲሆን ነው። ሰው ሰላም አለመሆኑን በየማህበራዊ የትስስር ገፅ እየተመለከትን ስለእዛ ጉዳይ አለማሰብ በእኔ እምነት ይቻላል ብዬ አላስብም።›› ሲል ገብረየስ ቀበል አድርጎ፤ ‹‹ ዋናው ጉዳይ ማሰብ አለማሰብ አይደለም። ሥራህን እና መዝናናትህን ትተህ ስለጦርነት ማሰብ የሚያስገኘው ጥቅም ምንድን ነው? የሚለው ነው። ወይ ስራህን አልሰራህ፤ ወይም ደግሞ መዝናናትህን አልተዝናናህ፤ ወይም ለሚያሳስብህ ጉዳይ መፍትሔ አላስገኘህ? ይሔ ምንም የሚያስገኘው ውጤት የለም።

በእኔ እምነት ተሰማ እንዳለው ከአንዱ ሳንሆን ዘመናችንን ከምናሳልፍ፤ ከአሁን ጋር እንታረቅ። መዝናናት ሲኖርብን መዝናናት፤ መሥራት ሲኖርብን መሥራት ይህ ከሆነ እንደውም ባልታሰበ መልኩ ሠላም እንዲመጣ አስተዋፅኦ እናደርጋለን። ከስራ ውጪ በወሬ ተጨንቀን፣ ወሬ ስናመላልስ ውለን ወንድም በወንድሙ ላይ እንዲነሳ ሁኔታዎችን ከማመቻቸት ይልቅ፤ ወንድም ወንድሙን በመልካም መልኩ እንዲደግፈው እና እንዲቀበለው ማበረታታት ይሻላል።›› ሲል በእርሱ በኩል ያለውን እምነት ገለፀ።

ተሰማ በበኩሉ፤ ‹‹በነገራችን ላይ መንግሥትም ሕዝብን ያምናል። ዕምነትን ማጉደል ትልቅ በድል ነው። መንግሥት እንዲሳካለት ጦርነት ሳይሆን ሰላም፤ ውድቀት ሳይሆን በዚህ ዘመን ዕድገት እንዲኖር የሚፈልግ ማንኛውም የዚህ ዘመን ሰው የመንግሥትን እምነት ማጉደል የለበትም። መንግሥት የሠጠውን እምነት አጉድሎ በሥራ ሰዓት ጦርነት የሚሰብክ ማህበራዊ የትስስር ገፅ እየተመለከተ መልስ እየተሰጣጠ መዋል በምንም መልኩ ከዘመን ጋር አብሮ መዘመን አይደለም።

ቴክኖሎጂውን ለጥሩ ነገር መፈፀሚያ፤ ሰውን ለበጎ ጉዳይ ማነሳሻ ከማድረግ ይልቅ የመጥፎ ቃላት አቅም ማሳይ ማድረግ አይገባም። በቴክኖሎጂው በተለይ በማህበራዊ የትስስር ገፅ ላይ እየፈፀምን ያለው ስህተት ወደ ፊት ብዙ ዋጋ እንዳያስከፍለን እሰጋለሁ። ባለፈው ታሪክ ላይ ተቸንክረን ዛሬን ከማበላሸት አልፈን ነገን እንዳናጣ እሰጋለሁ። ስለዚህ ትናንትን ትተን ከጊዜው ጋር እንታረቅ። ሀገር ውስጥ እየኖሩ ከሩቅ ሆነው እየተሳለቁ ‹አጀማመሩ ጥሩ ነበር። ነገር ግን መጨረሻው ሲያልቅ አያምር እንደሚባለው ነው› ብሎ ማሾፍ ምንም አያተርፍም። በዚህ ጊዜ ለሚኖር ልማትም ሆነ ጥፋት መንግሥት ብቻ ሳይሆን ተመስጋኝም ሆነ ተወቃሽ በዘመኑ ያለው አጠቃላይ ሕዝቡ ነው። ስለዚህ ገብረየስ እንዳለው ራሳችንን እንመልስ፤ ያለፈው ስህተት ይብቃን፤ ራሳችንን እናድስ፤ አትቃወሙ ማለት ባይቻልም። ተቃውሟችን ምክንያታዊ ይሁን።›› ብሎ ንግግሩን ሲጨርስ፤ ባንዱ ሞቅ ያለ ሙዚቃ ጀመረ። ተሰማ ፈጠን ብሎ ተነስቶ መደነስ ጀመረ።

ከአስር ዓመት በፊት በብዙ መልኩ ስታዝን፣ ስትከፋ እና በብዙ መልኩ ስትቸገር ነበር። ከአስር ዓመት በኋላ ዛሬም ተመሳሳይ ሁኔታ ላይ ነህ። ዛሬ ላይ ከራስህ ጋር መታረቅ ካልቻልክ ነገም ህይወትህ ተመሳሳይ ነው። ስለዚህ ያለፈው አልፏል፤ ቢያንስ ከዛሬ ጋር ታርቀህ ዘመንህን በደስታ አሳልፍ።›› ሲል ገብረየስ ለዘውዴ የጓደኝነት ምክሩን ለገሰው። ንግግራቸውን ከሩቅ ሆኖ ሲገምት የነበረው ተሰማ ዘውዴ ተነስቶ እንዲጨፍር ጋበዘው። ተሰማ ደስ ሳይለው እየፈራ ከመቀመጫው ተነሳ። ገብረየስ በዘውዴ ሁኔታ መሳቅ ጀመረ። ቀድሞ የነበረው የድብርት መንፈስ ርቆት ሲሔድ ታወቀው። የደስታ ስሜት ሲወረው፤ ‹‹ምን ዘውዴ ብቻ ለካ እኔም ከዛሬ ጋር አልታረቅኩም ነበር። መታረቁ ያዋጣኛል።›› ብሎ እርሱም እየሳቀ እየጨፈሩ ከነበሩት ከተሰማ እና ከዘውዴ ጋር አብሮ መጨፈር ጀመረ። ገብረየስ ተነስቶ ሲጨፍር ዘውዴ ከልቡ ፈገግ ሲል ተሰማም ተደሰተ። ሁለቱንም መሃል ገብቶ ወንድሞቼ ብሎ አቀፋቸው።

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

# እምቢ አልወለድም!

ሙሉጌታ ብርሃኑ






ገና ሳይወለድ፤ ከእናቱ ሆድ ውስጥ ቁልቁል ተዘቅዝቆና በውሀው ተዘፍቆ ሲንሳፈፍ በሀሳብ ተውጦ ነበር። ከሆድ ውስጥ ሳለ ጀምሮ ከውጭ የሚከናወነውን ሁሉ የሚመለከት፣ የሚሰማ፣ የሚያስብ፣ የሚናገር፣ ሁሉንም ነገሮች አስቀድሞ የሚያውቅ በእውቀት ባህር የጠለቀ ጉደኛ ህጻን፤ ከአንዲት ምስኪን እናት ሆድ ውስጥ ነበር። እናት ሆዷ ገፍቶ የምጧ ሰዓት በደረሰ ጊዜም አይኗን በአይኗ ለማየት ተመኝታ ነበር። ከብዙ ጭንቅ በኋላ የምታገኘውን ልጇን ታቅፋ ለመሳም ብትጓጓም እርሱ ግን "እምቢ አልወለድም" ሲል አንደበቱን አውጥቶ ተናገረ። የዚህን ህጻን ልጅ ድምጽ የሰማችው እናት ብቻ አነበረችም፤ ታላቁ ብዕረኛ አቤ ጉበኛ በትክክልም ሰምቶት ነበር። ጨቅላው ህጻን አልወለድም ሲል እሪ ለማለቱ እናት በውሉ ያላጤነችው፤ አስቀድሞ የተመለከተው አስፈሪ ነገር አለና ነው። እያለቀሰ ተወልዶ እያለቀሰ በመኖር፤ በለቅሶ ተጀምሮ በለቅሶ የሚያልቅን ሕይወት ለማየት አልፈለገም።

ልጄ እባክህን እሺ በለኝና ተወለድ። እምቢ አልወለድም! በእናቱ ተማጽኖ በልጁ እምቢታ መሃል ሆኖ አቤ ጉበኛ የሁለቱንም የልብ ትርታ አደመጠና "አልወለድም" ሲል ለመጻፍ ብዕሩን አነሳ። ያኔ ከዛሬ 61 ዓመታት በፊት። ገና በቅጡ ሳይከፈቱ በእንባ የረጠቡትን የህጻኑን አይኖች እየተመለከተ ልቡ በሀዘን በተሰበረ ጊዜ። ህጻኑም የሚረዳውን ሰው በማግኘቱ ደስ ብሎት የልቡን ከልቡ ያጫውተውና ይነግረው ጀመር። አልወለድም ይናገራል አቤም ይጽፋል። ብዕር የምናብ ህቅታ ብቻም ሳይሆን የልብን የደም ዕንባ ማንቢያ የደስታ ማጣጠሚያና የሀዘን መሸሸጊያም ነው። አቤ ጉበኛ ተወልዶ ካደገና ከጎለመሰ በኋላ መልሶ ግን አልወለድም ሲል እርሱም እንደ ህጻኑ ለመሆን ተመኘ። እናም አቤ በህጻኑ ውስጥ፤ ህጻኑም በእናቱ ሆድ ውስጥ ሆነው "አልወለድም" አሉ።

አልወለድም ማነው? አልወለድም የመጽሐፉ ርዕስና የዋና ገጸ ባህሪውን ውክልና የወሰደ የታሪኩ ተራኪም ጭምር ነው። ከእናቱ ሆድ ውስጥ ሆኖ አልወለድም የሚል ሞገደኛ ህጻን። በብዙ መጽሐፍት ላይ እንደምናውቃቸው አይነት ገጸ ባህሪያት ቁመቱ ረዘም ብሎ... ፊቱ ሾጠጥ ያለ...ባለ ግራጫ ካኪ ሱሪ...አዳፋው ኮቱ...በሳንቃው ደረቱ...ችፍ ችፍ ባለው ጺሙ...ጸጉሩ ተንጨፍርሮ..ከነበልባል አይኖቹ በታች ስልክክ ያለው አፍንጫው....ጉራማይሌ ጥርሱ...የሚሉ ምስል ከሳች ማንነቶች የሉትም። እንደሌሎቹ ህጻናት የመጠሪያ አባት ስም የለውም። አባቱም ማን እንደሆነ አይታወቅም። እዚህ ተወለደ እዚያ አደገ የሚባል ነገርም የለውም። ነገር ግን እያንዳንዱ የሚያነሳቸው ሀሳቦች የራሳቸው የሆኑ የገሀዱ ዓለም ውክልና አላቸው። ምንና ስለማን እያወራ ነው፤ ብለን ስንጠይቅ ከፊታችን፣ ከበስተጀርባችን አሊያም ከግራና ቀኝ ምላሾቹን እናገኛቸዋለን። ሁላችንም ግን አንድ አይነት ምላሽ ተመሳሳይ ምስል እንመለከት ይሆናል። በሚያጋጥመን፣ በምናየው፣ በምናውቀውና በምንረዳው መጠን ሊሆን ይችላል። እውነታው ግን በአልወለድም ውስጥ የኛ የሆነ ቢያንስ አንድ ጥያቄና አንድ እውነት አለ። የአልወለድምን መልክና ቁመና ደራሲው ለኛው የተወውም ለዚሁ ነው።

አንድ በሆድ ያለ ጨቅላ ህጻን እንዴት ይህን ያህል በእውቀት ይራቀቃል...እንዴትስ አንደበተ ጣፋጭ የቋንቋ ፈላስፋ ይሆናል...ህጻኑ አልወለድም በማይመስል ነገር ውስጥ የኛን የሕይወት እውነታ የሚናገር ነብይ፣ አስተማሪ፣ ጠቢብና እንዲሁም ፖለቲከኛም ጭምር ነበር። እናት በሆዷ የተሸከመችው የዚህ ጉደኛ ህጻን ነገር በእጅጉ አስደንቋታል። ግራም አጋብቷታል። የምትሰማው ድምጽ አንዳች መንፈስ እንጂ የልጇ ድምጽ ስለመሆኑ ማመን ከብዷታል። እሷ ለመውለድ በምጥ ስትታገል እሱ ግን "አልወለድም" ሲል በእምቢታው ጸና። እኛም እስቲ ከገጽ ወደ ገጽ እየዘለልን የሚለውን እናድምጠው።

"ታዲያ ለምን አትወለድም?" አለች። "ተወልጄ በችግር መሰቃየት አልፈልግም።" "እኔ በተቻለኝ መጠን አሳድግሃለሁ።" "ሊያኖረኝ የሚችል ሀብት አለሽ?" "እንደዚሁ ለምኜም ቢሆን አሳድግሃለሁ።"

"ሞት ይሻላል!...ልመናን ተማምኜ ነው የምወለድልሽ? በገዛ ሀገርሽ ላይ የምትችይውን ሰርተሽ በመኖር ፈንታ እንዴት ልመናን ተስፋ አድርገሽ ትኖሪያለሽ? ያንቺ በዚህ ሁኔታ መጎሳቆል አንሶ ደግሞ ማደሪያ ሌለው ልጅ ለምን ትወልጃለሽ?"

**‹‹ገና ሳይወለድ ይህንን ስቃይ መታገልና ከባርነት ነጻ ለመውጣት መፋለሙን ጀምሮ ነበረ። ከተኛበት ነቃ። ህጻኑ አልወለድም የተፈጥሮን ህግ ሽሮ አለመወለድ የማይቻለው ነገር ነበርና በመጨረሻም ተወለደ። ነገር ግን የተወለደውም ለነጻነት ትግልና ለአርነት ነበር። ከተወለደ በኋላም አላማው እናቱ የተዘፈቀችበትን ረሀብንና ድንቁርናን አሽንፎ ከዘመናት ቀንበር እሷን ነጻ ማውጣት ነበር። ይህቺ ምስኪን እናት ኢትዮጵያ ነበረች፤ ህጻኑ አልወለድም ደግሞ ለሀገራቸው የብርሃንን ላምባ ለመለኮስ ከንፋሱ ጋር የሚታገሉ ልጆቿ ናቸው።››**

.........

እሺ መሬት አለሽ?" "የለኝም"

"ቤት አለሽ?" "የለኝም"

"ታዲያ ምን አለሽ?"

"ምንም የለኝም።"

........

"ታዲያ ድህነትን፤ በሽታንና ድንቁርናን ልታወርሺኝ ነው ተወለድ የምትይኝ?"

"እድልህን እንዴት ታውቀዋለህ ልጄ?"

"ቀማኞችና ነፍሰ ገዳዮች፤ እንዲሁም የነፃነት ጠላቶች በሰለጠኑበት ደግሞ ምን እድል አለ? የድሆችን ልጆች የሚጠብቃቸው የወላጆቻቸው መከራና ችግር ብቻ ነው። መከራና ችግርን ከድሆች ትከሻ ለማውረድ እንደኔ ከሆድ ውስጥ ጀምሮ ለመብትና ለነፃነት መሟገት ያስፈልጋል።"

እያለ ሙግቱን ይቀጥላል። ይህ የአልወለድም ታሪክ ብቻ አይደለም። ገና ወደዚህች ምድር ሳንመጣ አስቀድሞ፤ በእናቶቻችን ሆድ ውስጥ ሳለን ልክ እንደ አልወለድም የወደፊቱን እጣ ፈንታችንን የማወቅና የመጠየቅ እድሉ ቢገጥመን፤ የአብዛኛዎቻችን ጥያቄ ሊሆን የሚችለው ይሄው ነው። አቤ ጉበኛ በምናብ እረቆ፤ በእውቀት ጠልቆ የወከለው ይህንን ገጸ ባህሪንም ሆነ ቅኔ በሆነው በዚህ መጽሐፍ ውስጥ፤ ወርቁን ከምናገኝበት ከርሰ ምድር ላይ ለመድረስ ብዙ ማወቅንና ያወቅነውንም መቆፈርን ይጠይቃል። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ አልወለድም ፖለቲካውን ብቻ ሳይሆን ማህበረሰቡንም ከተኛበት የጦፈ እንቅልፍ ውስጥ ቀስቅሶ ለማንቃት ሲጥር እንመለከተዋለን። ነገር ግን መጽሐፉ በወቅቱ ለነበረው የፖለቲካ ትኩሳት ዳፍ ሆነ። ሀሳቡን ያልወደዱት አካላት ደራሲውን ከነመጽሐፉ ጠምዝዘው መስቀለኛው የፖለቲካ መንገድ ውስጥ እንዲገባ ተደረገ። አልወለድም አስቀድሞ በሆድ ውስጥ ሳለ የተናገራቸው ትንቢቶች ይፈጸሙ ጀመረ። "አልወለድም" ዘውዳዊውን ሥርዓት ለመናድ የሚታገል 'ሽብርተኛ' ነው ሲባል ተፈረደበት። ከዚህም የተነሳ በውስጡ ከያዘው ታሪክ በተጨማሪ፤ መጽሐፉ እራሱ አንድ መጽሐፍ የሚወጣው ሌላ ታሪክ ከበስተጀርባው ተፈጠረበት።

"አልወለድም" ከብዙ መከራና ስቃይ በኋላ በ1955 ዓ.ም ለሕትመት በቅቶ ነበር። በመጀመሪያ የመጸሐፉን አካሄድ የገመገሙት የሳንሱር አባላት አጻጻፉን በግልጽ እንዲህ ነው ብሎ ለመወሰን ባለመቻላቸው በውስጣቸው ጥርጣሬን ቢያሳድርባቸውም በብዙ መፍጨርጨርም ቢሆን ለሕትመት እንዲበቃ ሆነ። ብዙም አልቆየም ሲብሰለሰል የከረመው ጉዳይ መጽሐፉ እየታተመ የስርጭት ጉዞውን ለመጀመር ሲሰናዳ ፈንድቶ ወጣ። መጽሐፉ ሕትመቱን እንዲያቆምና ከአንባቢያን እጅ እንዳይገባ ፈጣን የሆነ አስቸኳይ እገዳ ከላይ ተላለፈ። እውነቱን ለመናገር የዚህ መጽሐፍ ይዘት በቀጥታ የዘውዳዊውን ሥርዓት ሥጋት አነበረም። በግልጽ የአማርኛ ቃላት ወደ ቤተ መንግሥቱ የሚወረወሩ ፈንጂዎችንም የታጠቀ አይደለም። በሳንሱር አጥር ሾልኮ ቢያልፍም የሕትመትና የስርጭት ግንቡን ለመዝለል ግን አልተቻለውም። ዙፋናችን ሊደፈር ነው ያሉ ሹማምንትና አንዳንድ አካላት 'የዘፈን ዳር ዳሩ እስክስታ ነው' ሲሉ፤ እሳት ጎርሰው እሳት ለብሰው ተነሱ። ነገሩ 'ምን ያለበት ዝላይ አይችልም' ሆኖባቸው አሊያም ሌላ ምክንያት ቢኖራቸው እንጂ ጉዳዩስ ቅኔ ነበር። ቅኔም ህልም እንደፈቺው ሆኖ፤ ሰሙ ተበርብሮ ቅኔው ሲፈታ፤ ምንም እንኳን ወርቁ ውስጥ ስለ ሥርዓቱ የሚናገሩ ነገሮች ቢኖሩትም የአልወለድም ሀሳብ ግን ከዚያም ያለፈ ነበር። ቅኔውም ሌላ ቅኔን ያዘለ በመሆኑ ወርቁ እያደር የሚገባ ነበር። በግልጽ እንዲህ ነው ባትልም ነገር ግን እንዲህ ለማለት አስበህ ነው በማለት በጠላትነት ፈረጁት። ምስቅልቅሉ የወጣ ግዙፍ ጨለማ የሕይወቱን ብርሃን ጋረደው።

1967ዓ.ም የዘውዳዊው ሥርዓት ማብቂያ የ"አልወለድም" መጽሐፍ መጀመሪያ ሆነ። ለአንዱ ሲጨልም ለአንደኛው ነጋ። ንጉሥ ሄደ ንጉሥ መጣ። ያለው እንዳለ ሆኖ፤ የያዘውን እንደያዘም ለ"አልወለድም" ጥሩ አጋጣሚ ነበር። ከላዩ ተጭኖ ያዳፈነው የእገዳ ቀንበር ተነስቶ፤ ዳግም ለንባብ በቃ። በጊዜው በነጻነት የሚነበብበትን መብት ቢቸረውም የተፈላጊነቱና የተነባቢነቱን ያህል ዳግም የሕትመትን ደጅ እንዲረግጥ ግን አልተደረገም ነበር።

"አንድ ሰው ሲያልፍ ስለ መድሃኔአለም አለችውና /እናቱ መሆኗ ነው/ ሳንቲም ሲሰጣት ከእጇዋ ላይ ከነበረው ሌላ ሳንቲም ጋር ተጋጭቶ ቅጭል ሲል በሆዷ ውስጥ ከተኛሁበት ብንን አልሁ። ከእንቅልፍ መንቃት ብቻ አይደለም፤ ከድንቁርና ስሜትም ነቃሁ።" በማለት አልወለድም ገና በእናቱ ሆድ ውስጥ ሳለ የእርሱንና የተሸከመችውን እናት መጥፎ እጣ ፈንታ ትንቢታዊ በሆነ መልኩ ታየው። ገና ሳይወለድ ይህንን ስቃይ መታገልና ከባርነት ነጻ ለመውጣት መፋለሙን ጀምሮ ነበረ። ከተኛበት ነቃ። ህጻኑ አልወለድም የተፈጥሮን ህግ ሽሮ አልመወለድ የማይቻለው ነገር ነበርና በመጨረሻም ተወለደ። ነገር ግን የተወለደውም ለነጻነት ትግልና ለአርነት ነበር። ከተወለደ በኋላም አላማው እናቱ የተዘፈቀችበትን ረሀብንና ድንቁርናን አሸንፎ ከዘመናት ቀንበር እሷን ነጻ ማውጣት ነበር። ይህቺ ምስኪን እናት ኢትዮጵያ ነበረች፤ ህጻኑ አልወለድም ደግሞ ለሀገራቸው የብርሃንን ላምባ ለመለኮስ ከንፋሱ ጋር የሚታገሉ ልጆቿ ናቸው።

አልወለድም፤ መለወጥ አለብን! እስከመቼስ ነው በእንዲህ አይነት ሁኔታ የምንኖረው? የሚል የለውጥ መንገድ ጠራጊ ቢሆንም፤ ለውጥ ናፋቂነቱ ግን እንደ ነውጥ ናፋቂ አመጸኛ አስቆጠረውና በጨቋኞች መዳፍ ስር ወደቀ። አልወለድም ለምድራዊ ሰቆቃ ታልፎ ተሰጠ። ለእስር፣ ለእንግልት እና ለግርፋት ተዳረገ። ከዚህም የተነሳ በመጨረሻዋ ሰዓት በጥይት ግንባሩን ብለው ደፉት። እሱም እንዲህ አለ፤ "ወላጆቼ ወይም ፈጣሪዬ ወደዚህ ዓለም እንድመጣ ፈልገው እንደሆን አስቀድመው ወደ ዓለም መጥቼ ከዓለም እስክወገድ ድረስ በሰላም፤ በፍቅር፤ በደስታ ከሁሉም ይልቅ በነፃነት ልኖር የምችልበት እድል ማዘጋጀት ነበረባቸው። ይህንን ስላላገኘሁ ግን በአመፅ ተወልጄ በአመፅ ሞትሁ" በማለት ተራኪው ሞቱንም ያረዳናል።

የአልወለድም ታሪክና እውነት ትናንት በነበረ የሚታለፍ አይደለም። ደራሲው አቤ ጉበኛ ትናንትናን ብቻ ሳይሆን ዛሬና ነገንም ጭምር እያየ የጻፈው በመሆኑ ለአፍታ እንኳን የማይቀዘቅዝ የዘመናት ወላፈን ነው። አቤ "አልወለድም" ሲል በመጽሐፉ የወከለው ገጸ ባህሪ በርግጥም በራሱ የተመሰለ ነበር። ይህ መጽሐፍ የእርሱን ውስጣዊ ማንነት በማውጣት በታሪክ ጎልቶ እንዲወጣ ቢያደርገውም በ1968 ዓ.ም የታተመው "ፖለቲካና ፖለቲከኞቹ" የተሰኘውን መጽሐፍ ጨምሮ በተመሳሳይ መልኩ ጭቆናና ድንቁርናን የተጋፈጠባቸው ሌሎች ሥራዎችም አሉት። በዘውዳዊ ሥርዓት ወቅት የጀመረውን ወርቃማ የብዕር ትግል በደርግም አልተገታም ነበር። በሁለቱም ሥርዓቶች ለእስራትና ለእንግልት ተዳርጓል፤ በተለይ ደግሞ አልወለድምን ተከትሎ የመጣው ዱላና ያፈራው ጠላት ብዙ ነበር። የደራሲው የመጨረሻ እጣ ፈንታ አልወለድም ከተሰኘው ገጸ ባህሪ የተለየ አነበረም። አቤ ጉበኛ የካቲት 4 ቀን 1972 ዓ.ም አዲስ አበባ ጎጃም በረንዳ አካባቢ ማንነታቸው ባልታወቁ አካላት በድንጋይ ተቀጥቅጦ ሞቶ ተገኘ። ነብሰ ገዳዮች በበዙባት ምድር ፍትህ ከወዴት ይገኛል? ሲል አልወለድም ለእናቱ የጠየቃት ጥያቄ ምላሹ እራሱ አቤ ጉበኛ ሆነ። ያለ ፍትህ ተወለደ፤ ያለ ፍትህ ኖረ፤ ያለ ፍትህ ሞተ። ሲኖር እንዲያ የተጠማትን ፍትህ፤ ከሞት በኋላም ነብሱ ተጠማችው። የአሟሟቱ ጉዳይ እንቆቅልሽ እንደሆነ ተደፋፍኖ ቀረ።

ስለምን በድህነት ተወልደን አድገን በድህነት እንሞታለን? ይህ ፈጽሞ መሆን የለበትም። ደስታ ያስፈልገናል፤ ነጻነታችን ሊጠበቅ መብታችንም ሊከበር ይገባል በማለቱ፤ የመጽሐፉ አልወለድም በሽብርተኝነት በከሰሱት ባለጠመንጃ ጉልበተኞች መገደሉ የራሱ የትንቢት ፍጻሜ ነበር። አቤ ጉበኛ ለረሀብ፣ ለድርቅ ለመሀይምነትና ድንቁርና "አልወለድም" ሲል ለጨለማ ሞቶ ለብርሃን ተወለደ። እኛስ ዛሬ ለየትኛው ይሆን እምቢ፤ አሻፈረኝ ስንል አልወለድም የምንለው? ለኑሮ ጉስቅልናና ሕይወት? ለፖለቲካ እንቆቅልሽ? ለዘረኝነት?...ለሃይማኖተኝነት?... ለጥላቻና በቀል? ወይንስ...?

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ


## የጉራማይሌ ቋንቋ ተፅእኖ

አስመወርቅ ከበደ

ከሰው ልጅ የመግባቢያ መሳሪያዎች ውስጥ አንዱ የንግግር ቋንቋ ነው። የንግግር ቋንቋ መቼና የት እንደተጀመረ በእርግጠኝነት የሚያስረዳ መረጃ ባይኖርም ከሰው ልጅ ዝግመተ ለውጥ ሂደት ጋር የተሳሰረ እንደሆነ ይነገራል። በአሁኑ ወቅት ቋንቋ ከሉዓላዊነት ጋር ተያይዞ የሰው ልጅ አብሮ የመኖር እና የመገናኘት እድልን እያሰፋ መጥቷል። በዚህም አንዱ የሌላውን ቋንቋ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ በራሱ ቋንቋ ውስጥ እየቀየጠ የመናገር ባህል አዳብሯል። ሰዎች ታዲያ ቋንቋን ቀላቅለው ወይም ጉራማይሌ የሚናገሩት በተለያዩ ምክንያቶች እንደሆነ የቋንቋ ምሁራን ይገልፃሉ። ይህ ልምድ የራሱ ተጽእኖ እንዳለውም ይጠቅሳሉ።



መስፍን ፈቃደ(ዶ/ር)



ሰጠኝ ማየው(ዶ/ር)

መስፍን ፈቃደ(ዶ/ር) በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የስነ-ጹሑፍና የባህል መምህር ናቸው። የሀዲስ ዓለማሁ የባህል ጥናት ተቋም ዳይሬክተርም ሆነው ይሰራሉ። እርሳቸው እንደሚገልፁት ቋንቋን ቀላቅሎ /ጉራማይሌ/ መናገር ከመደበኛው የቋንቋው መድብለ ቃላት ጋር አብሮ ስለማይሄድ የሌላውን ቋንቋ በንግግር ውስጥ ማስገባት የሚፈለገው መልእክት እንዳይደርስ ያደርጋል። ጉራማይሌ የቋንቋ ለአብነት የአማርኛ ቋንቋ ንግግር ውስጥ በተደጋጋሚ የእንግሊዘኛ ቋንቋን ወይም ሌላ ቋንቋን አስገብቶ መናገር ነው። ይህም በተናጋሪውና መልእክት ተቀባዩ መካከል የተሟላ ተግባቦት እንዳይኖር ከማገዱም በላይ ቋንቋው እንዳያድግ እንቅፋት ይሆናል።

የጉራማይሌ ቋንቋ ንግግር አዋቂነትን ለመግለጽ ተብሎ የመጠቀም ሁኔታ እንዳለ ጥናቶች ያመለክታሉ። ይሁንና አንዳንዴ ለመግለጽ የተፈለገውን ቃል በመደበኛው ቋንቋ የማይገለጽበት ሁኔታ ሲፈጠር ቃሉን አስገብቶ የመጠቀም ሂደት አለ። እንዲያም ሆኖ ግን ቋንቋን ቀላቅሎ መናገር ተገቢ አይደለም። አንዳንዴ ግን በሚዲያ፣ በመደበኛ ማስተማር ስርዓት እና በንግግር ወቅት ለመግለጽ የተፈለገውን ቃል መደበኛው ቋንቋ የማይገልጽ ከሆነ ቀላቅሎ መናገር የሚቻልበት ሁኔታ ይኖራል።

ዳይሬክተሩ እንደሚሉት፣ ቋንቋ ቀላቅሎ መናገር አድማጭ መልዕክቱን በትክክል እንዳይረዳ፡- ቋንቋው እንዳያድግ ብሎም የቋንቋው ሥርዓትና ቅንብር እንዲፈርስ ያደርጋል። ለምሳሌ አንድ የህግ ባለሙያ ስለህግ ትንታኔ በሚሰጥበት ወቅት ሀሳቡን የሚገልጽ የተሟላ ቃል እያለ የሌላን ቋንቋን የሚጠቀም ከሆን የተማረውም ሆነ ያልተማረው መልእክቱን በሚገባ እንዳይረዳ ያደርጋል።

በኢትዮጵያም ከታችኛው እስከላይኛው ትምህርት እርከን ይህ ቋንቋን ደባልቆ ወይም ጉራማይሌ የመናገር ዝንባሌ በስፋት ይታያል። ከዚህ አንፃር ይህ ሁኔታ ለመቀልበስ ተማሪዎች ትምህርታቸውን በሚከታተሉበት ወቅት የሚማሩት በእንግሊዘኛ ቋንቋ ከሆነ ያልተቀላቀለ እንግሊዘኛ መጠቀም፡- ከታችኛው የክፍል ደረጃ ጀምሮ መደበኛ መዝገበ-ቃላትን ማስቀመጥ እና ቀላቅሎ መናገርን እንደስልጣኔ ለሚመለከቱ ሰዎች ድርጊቱ ተገቢ አለመሆኑን መናገርና ግንዛቤ መስጠት ይገባል።

በደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ የእንግሊዘኛ ቋንቋ መምህር ሰጠኝ ማየው(ዶ/ር) በበኩላቸው እንደሚናገሩት፣ ቋንቋን ቀላቅሎ መናገር ሁለት ቋንቋዎች በሚነገሩባቸውት አካባቢዎች የማይቀር ቢሆንም፡- እንግሊዘኛ ቋንቋ የሚገኘው በብዛት በትምህርት ቤቶች በመሆኑ ያልተማረው ህብረተሰብ የሚነገረውን መልእክት በትክክል መረዳት ይቸግረዋል።

ቋንቋን ቀላቅሎ መናገር በስፋት በሁለት ምክንያቶች ሊመጣ ይችላል። የመጀመሪያው ተናጋሪው ቋንቋውን አጠቃሎ የማይችል ሲሆን፡- ሌላኛው ቋንቋው እራሱ ክፍተት የሚታይበት ሲሆን በተለይ አዳዲስ የመጡ የቴክኖሎጂ ቃላት የሚገልጽ ቃል ሲያጥር የመቀላቀል ሁኔታ ይፈጠራል። ይህም አድማጩ ላይ ብዥታ መፍጠር፣ አድማጩ ለእኔ ሊነገር ያልተፈለገ መልእከት አለ ብሎ እንዲያስብ ከማድረጉም ሌላ የሌላን ቋንቋ የማበረታታት ሁኔታ እንዲፈጠር ያደርጋል። በተጨማሪም አዋቂነትን ለመግለጽ፡- ከሌላኛው ቋንቋ ተናጋሪ ተቀባይነት ለማግኘት ፡- በልማድ እና ሚስጥር ለመደበቅ ቋንቋን ቀላቅሎ የማውራት ሁኔታም ይኖራል፡፡

እንደ ዶክተር ሰጠኝ ገለፃ፣ በሶስት ዓይነት መልኩ ቋንቋ ቀላቅሎ የመናገር ሁኔታ አለ። የመጀመሪያው በመደበኛው ቋንቋ ሃሳብን ጨርሶ ከተናገሩ በኋላ ቀጣዩን በሌላ ቋንቋ መናገር፡- ሁለተኛው በአንድ ዓረፍተ ነገር ውስጥ ሌላ ቋንቋ አስገብቶ መናገርና ሶስተኛው አጫጭር ቃላትን በንግግር መሀል ማስገባት ናቸው፡፡

አዳዲስ የቴክኖሎጂ ቃላት ሲመጡ አቻ ትርጉም ሊሰጡ የሚችሉ ቃላትን በመፍጠር ረገድ በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴርም ሆነ በሚመለከታቸው አካላት ሰፊ ሥራ ሊሰራበት ይገባል። በተጨማሪም በቋንቋ ዙሪያ ተገቢውን ስልጠና መስጠት ያስፈልጋል፡፡

# ዓለም አቀፍ

## ሰሜን ኮሪያ ወታደራዊ የስለላ ሳተላይት አመጠቀች

ሰሜን ኮሪያ በዚህ ዓመት ካልተሳኩላት ሁለት ሙከራዎች በኋላ ወታደራዊ የስለላ ሳተላይት በተሳካ ሁኔታ ወደ ሕዋ መላኳን አስታወቀች። ሰሜን ኮሪያ ይህን ያስታወቀችው መስከረም ወር ላይ የሩሲያው ፕሬዚደንት ቭላድሚር ፑቲን እና ኪም ጆንግ ኡን ከተገናኙ በኋላ ነው።

የሩሲያ ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን ከሰሜን ኮሪያው አቻቸው ኪም ጆንግ ኡን ጋር በተገናኙበት ወቅት ሞስኮ ሳተላይቶችን ለፒዮንግያግ እንደምትሰጥ ቃል ገብተው ነበር። ደቡብ ኮሪያ እስካሁን ሳተላይቱ ሥራ ስለመጀመሩ ባታረጋግጥም፣ ሰሜን ኮሪያ ከሩሲያ ድጋፍ አግኝታለች ብላ እንደምታምን ገልጻለች።

ሳተላይቱ መምጠቁን ተከትሎም ከሰሜን ኮሪያ ጋር በአውሮፓውያኑ 2018 ወታደራዊ ውጥረትን ለማርገብ የገቡትን ስምምነት ወደ ጎን በማለት ከሀገሪቷ ጋር በምትዋሰንበት ድንበር የደኅንነት ሥራ ማጠናከር እንደምትጀምር አስታውቃለች። ማሊንግዮንግ-1 የሚል ስያሜ የተሰጣት ሳተላይቷ፣ በትክክል ወደ ምህዋሯ መግባቷንና ሳተላይቷ ኪም ጆንግ ኡን በተገኙበት መምጠቋን ሰሜን ኮሪያ የመንግሥት ዜና ወኪል (ኬሲኤንኤ) ዘግቧል።

ይህንን ተከትሎም ከኒዩክሌር ሚሳይል ማበልጸግ ጋር በተያያዘ ሰሜን ኮሪያ ላይ ማዕቀብ የጣለው የተባበሩት መንግሥታት እንዲሁም አሜሪካንና ጃፓንን ጨምሮ ሌሎች ሀገራት ድርጊቱን አውግዘዋል። የተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ "የባሊስቲክ ሚሳይልን በመጠቀም በሰሜን ኮሪያ የሚደረግ ማንኛውም ሳተላይት ማምጠቅ ከጸጥታው ምክር ቤትን ውሳኔ ጋር የሚጻረር ነው" ብለዋል።

ዋና ጸሐፊው ጨምረውም ሰሜን ኮሪያ ኒውክሌር ከማበልጸግ ጉዞዋ እንድትመለስ ጥሪ አቅርበዋል። ዋይት ሃውስም እንቅስቃሴውን በተባበሩት መንግሥታት ውሳኔ ላይ የተቃጣ አሳፋሪ ጥሰት ነው ያለ ሲሆን፣ የጃፓን ጠቅላይ ሚኒስትር ፉሚዮ ኪሺዳን በሀገራቸው ኦኪናዋ እና በፓስፊክ ውቅያኖስ አቅጣጫ ሳተላይት መምጠቁን አውግዘዋል።

የጃፓን መንግሥት የኦኪናዋ ነዋሪዎች መጠለያ ውስጥ እንዲገቡም ድንገተኛ ማስጠንቀቂያ ሰጥቷል። ሳተላይቱ ከተያዘለት እቅድ እና ፒዮንግያንግ ለጃፓን ካሳወቀችው የጊዜ መርሃ ግብር ስምንት ቀናት ቀደም ብሎ የተፈፀመ ነው።

ሰሜን ኮሪያ በዚህ ዓመት ሁለት ጊዜ ማለትም ግንቦት እና ነሐሴ ወር ላይ ሙከራ ያደረገች ሲሆን ሁለቱም ሳይሳኩላት ቀርተው ነበር።

የጃፓኑ ጠቅላይ ሚኒስትር ኪሺዳ ሳተላይት መምጠቁን አጥብቀው ያወገዙ ሲሆን የባሊስቲክ ሚሳይል ቴክኖሎጂን ተጠቅሞ ሳተላይት ማምጠቅ የተባበሩት መንግሥታት የጸጥታው ምክር ቤት ውሳኔን በግልጽ የጣሰ ነው ሲሉ ኮንነውታል።

"ለሕዝባችን ደኅነንት ትልቅ ስጋት የሆነ በጣም አሳሳቢ ጉዳይ ነው" ብለዋል ጠቅላይ ሚኒስትሩ። ኬሲኤንኤ የሰሜን




ኮሪያን የሕዋ ምርምር ተቋም ጠቅሶ እንደዘገበው ሳተላይቱ የመጠቀው ከቻይና ጋር በሚያዋስነው ሰሜን ምዕራብ ከሚገኘው ሶሄ የሳተላይት ማምጠቂያ ጣቢያ ነው።

ሰሜን ኮሪያ በስኬት አምጥቄዋለሁ ያለችው የስለላ ሳተላይት ስለመሆኑ አልተረጋገጠም። ሮኬቱ የስለላ ሳተላይት መሆኑ ከተረጋገጠ ግን በዚህ ዓመት በሰሜን ኮሪያ የተደረገው ሦስተኛ ሙከራ ይሆናል።

የስለላ ሳተላይቱ ለሰሜን ኮሪያው መሪ ኪም ጆን ኡን በቀጣይ የሚቃጡ ጥቃቶችን ለመከታተል እና የራሳቸውን ኢላማ በትክክል ለመምታት ይረዳቸዋል ተብሏል። ይህ ሴኡል በ2025 አሳካዋለሁ ካለችው አምስት የስለላ ሳተላይቶች የመጀመሪያው እንደሆነም ቢቢሲ ዘግቧል።

## ለጉብኝት ወደ ሌላ ሀገር የሄዱት ፕሬዚዳንት በውሻ መነከሳቸው አነጋገረ

ለጉብኝት ወደ ሌላ ሀገር የሄዱት ፕሬዚዳንት በውሻ መነከሳቸው አነጋጋሪ ሆኗል። በውሻ ንክሻ የደረሰባቸው ፕሬዚዳንት የኦስትሪያ ፕሬዚዳንት ናቸው። እንደስካይ ኒውስ ዘገባ ፕሬዚዳንቱ ለይፋዊ ጉብኝት በሞልዶቫ በተገኙበት ወቅት የጓደኝነት ሕግን የጣሰው የሞልዶቫ 'የመጀመሪያ ውሻ' እጃቸውን ነክሶ ጉዳት አድርሶባቸዋል።

ነገር ግን የውሻው ድርጊት የኦስትሪያውን ፕሬዚዳንት አሌክሳንደር ቫንደር ቤለን እና የሞልዶቫውን ፕሬዚዳንት ማይ ሳንዱን ግንኙነት አላሻከረውም። ፕሬዚዳንት ቫንደር ቤለን ይቅር ብለዋል። ባለፈው ዓርብ በሀገሪቱ ሚዲያዎች የተለቀቁ ተንቀሳቃሽ ምስሎች እንደሚያሳዩት ቫኔደር ቤለን ከሳንዱ ጋር በሞልዶቫ ዋና ከተማ ቺሲናው ጋር ቆመው ታይተዋል።

የኦስትሪያው ፕሬዚዳንት ውሻውን ለማሻሸት ጎንበስ በሚሉበት ወቅት እጃቸውን ነክሷቸዋል። ፕሬዚዳንት ሳንዱ በውሻቸው ድርጊት በእንግሊዝኛ ቋንቋ ይቅርታ ጠይቀዋል፣ ውሻው ይህን ያደረገው በአቅራቢያው ሰው ሲበዛ በመፍራቱ ምክንያት ነው ሲሉም አብራርተዋል።

ቫንደር ቤለን በሚቀጥለው ስብሰባ ላይ እጃቸው በፋሻ ተጠቅልሎ ከሞልዶቫ ፓርላማ አፈ ጉባኤ ጋር ታይተዋል። ቢሯቸው "በፋሻ የሚድን ትንሽ ቁስል ነው" ብሏል። ፕሬዚዳንቱ በጥሩ ሁኔታ ላይ እንደሚገኙም ቢሮው አክሏል። ቫንደር ቤለን ከሳንዱ እና ከስሎቫንያን ፕሬዚዳንት ናታሳ ፒሮክ ሙሳር ጋር በሞልዶቫ የአውሮፓ ህብረት አባልነት ጥያቄ ጉዳይ ተወያይተዋል።

የኦስትሪያው ፕሬዚዳንት ንክሻው ከደረሰባቸው በኋላ በኢንስታግራም ገጻቸው ትንሽ ችግር ተፈጥሮ ነበር ብለዋል።

ውሻ እንደሚወዱ የገለጹት ቫንደር ቤለን ውሻው ሰው ስለበዛበት ተቆጥቶ እንደነበር መግለጻቸውን አል ዐይን ዘግቧል።

ፖስቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፡- በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፡- በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፡- በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፡- የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፡- በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

# ኅዳር፣ፖለቲካው፣ኢኮኖሚው...

ከ ገጽ 5 የዞረ

መንቀሳቀሳቸው ነበር። አንድ ሶስተኛው የአለም ህዝብ በዚህ በሽታ እንደተያዘም ይነገራል፡- በበሽታው ከተያዙት ውስጥ ከ10 እስከ 20 በመቶ የሚሆኑት ለሞት ተዳርገዋል። ሲኖ ባይሎጂካ የተሰኘ የህክምና ጥናት ማዕከል ባደረገው ጥናት መሰረት፡- በአሜሪካ እስከ 28 በመቶ የሚሆነው ህዝብ በበሽታው ተጠቅቶ ነበር፡- 675 ሺህ ገደማ የሚሆነው ህዝብ ደግሞ በበሽታው ሞቷል። ወረርሽኙ በህንድ የከፋ ነበር።

መረጃዎች እንደሚጠቁሙት፡- 17 ሚሊዮን ህንዳዊያን በበሽታው ህይወታቸውን አጥተዋል። በጃፓን 23 ሚሊዮን ህዝቦችን ያጠቃ ሲሆን 400 ሺህ ገደማ የሚሆኑትንም ገድሏል። እንግሊዝ ሩብ ሚሊዮን፣ ፈረንሳይ ደግሞ 400 ሺህ ዜጎቻቸውን በበሽታው አጥተዋል። እ.ኤ.አ ከጥር ወር 1918 ዓ.ም እስከ ታህሰስ 1920 ዓ.ም በመላው ዓለም ተንሰራፍቶ የቆየው የእንፍሉዌንዛ ወረርሽኝ፣አንድ መቶ ሚሊዮን የሚጠጋ ህዝብ ፈጅቷል፡- የሟቾቹ ቁጥር እስከ 200 ሚሊዮን ይደርሳል የሚሉ መረጃዎችም አሉ።

የወረርሽኙን ጉዳት የከፋ ያደረገው አምራች ዜጎችን በከፍተኛ ሁኔታ በማጥቃቱ ነበር። በበሽታው ከሞቱት መካከል ዕድሜያቸው ከ25 እስከ 34 ዓመት የሆኑ ወጣቶች አብዛኛውን ድርሻ ይወስዳሉ፡- በመሆኑም በሽታው ካደረሰው ሰብዓዊ ውድመት ባለፈ ጥሎት ያለፈው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጠባሳ የከፋ ነበር።

ወረርሽኙ በአፍሪካ በሁለት ዙር ነበር የተከሰተው፡- የመጀመሪያው በፈረንጆቹ በ1918 ዓ.ም የጸደይና የበጋ ወራት ሲሆን ሁለተኛውና የከፋ ጉዳት ያደረሰው ደግሞ በበልግ ወራት የታየው ነበር። በሽታው ለመጀመረያ ጊዜ በአፍሪካ የታየው በወቅቱ የእንግሊዝ ቅኝ ግዛት በነበረችው በሴራሊዮን ዋና ከተማ ፍሪታዎን ሲሆን በአጭር ጊዜ ወደ ሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ተስፋፋ።

ሚስተር መሪ (Murray) የተባሉ አጥኚ Global Pandemic በተሰኘ ጥናታቸው እንዳሰፈሩት፡- የበሽታው ስርጭት ከሰሃራ በታች በሚገኙ ሀገራት ላይ ሰፊ ነበር፡- በክፍለ አህጉሩ የተከሰተው የሞት መጠን በመላው ዓለም በበሽታው ከተከሰተው ሞት ውስጥ የ29 በመቶ ድርሻ አለው። በተለይም በምዕራብና ደቡባዊ አፍሪካ ጥፋቱ የከፋ ነበር፡- በጋና እስከ መቶ ሺህ ዜጎች እንዳለቁ ይገመታል፡- በምስራቅ አፍሪካም ቀላል የማባል ቁጥር ያላቸው ዜጎች ህይወታቸውን አጥተዋል፡- በእንግሊዝ ሶማሊ ሰባት በመቶ የሚሆኑ ህዝቦች በበሽታው ሲሞቱ፣ በኢትዮጵያም ከአርባ ሺህ በላይ ሰዎች በቫይረሱ ሳቢያ ህይወታቸውን አጥተዋል።

ከሰብዓዊ ውድመቱ ባለፈ ወረርሽኙ በአፍሪካ ከባድ ኢኮኖሚያዊ ቀውስ አስከትሏል። በጊዜው አጠራር ደቡብ ሮዴሺያ (የዛሬዋ ዚምባብዌ) አምራች የሰው ሀይል በበሽታው በመያዙ የወርቅ ማውጫ ስፍራዎች እንዲዘጉ ሆኖ ነበር፡- በዚህም በማዕድን ዘርፍ ላይ የተንጠለጠለው የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ክፉኛ ተጎዳ። ወረርሽኙ በማላዊና በዛምቢያም ያደረሰው ኢኮኖሚያዊ ኪሳራ ከፍ ያለ ነበር። በናይጀሪያም፣በተለይ በደቡባዊ የሀገሪቱ ክፍል በሽታው የከፋ ጥፋት በማድረሱና ምርት በማሽቆልቆሉ፣ ቀድሞ ለምግብነት የማይውለው ካሳቫ ለምግብነት መዋል ጀመረ። በአነስተኛ ጉልበትና ያለ ብዙ ልፋት የሚመረተው ካሳቫ ተመራጭ ምግብ ሆነ።

የ1918ቱ የእንፍሉዌንዛ ወረርሽኝ በአፍሪካ ያስከተለው ማህበራዊ ቀውስ ቀላል አልነበረም። በሽታው ዘር፣ ቀለም፣ ሀይማኖት፣ የኢኮኖሚ ደረጃን ሳይለይ ሁሉንም ሰው የሚያጠቃ ቢሆንም ቅኝ ገዢዎች በሽታው ከጥቁር ህዝቦች የመጣ እንደሆነ በማናፈስ የዘር መድልኦ ለማድረግ ተጠቅመውበታል። ይህ ችግር በተለይም በደቡብ አፍሪካ የጎላ ነበር፡- በዚህም ነጮችና ጥቁሮች ማንኛውንም ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎችን በአንድ ላይ እንዳያደርጉ የሚደነግግ አዋጅ እንዲጸድቅ ተደረገ።

በቦትስዋናም በሽታው በርካታ ህጻናትን ወላጅ አልባ አድርጓል። በጋና የሆነው ደግሞ ትንሽ ለየት ያለ ነበር፡- በሽታው ተንሰራፍቶ በርካታ ሴቶች በመጠቃታቸው፣ ከነባራዊው የጋናዊያን ባህልና ወግ ባፈነገጠ መልኩ ባሎች የሴቶች ድርሻ ተደርጎ ይወሰድ የነበረውን የቤት ውስጥ ስራዎች መስራት ግድ ሆነባቸው። ወንዶች ማዕድ ቤት ገብተው በቆሎ መፍጨት፣ ምግብ ማብሰል የመሳሰሉትን ስራዎች ይከውኑ ጀመር።

በኢትዮጵያ በሽታው የታየው የመጀመሪያው የበሽታው ምልክት በዓለም ላይ ከታየ ከአስር ወራት በኋላ በህዳር ወር 1911 ዓ.ም ነው። ከጥቂት ወራት ቀደም ብሎ በሽታው መግባቱ አይቀርም በሚል የቅድመ ጥንቃቄ ስራዎች መስራት እምብዛም የተለመደ አልነበረም። በዚህ ረገድ ሊጠቀስ የሚችለው በኢትዮጵያ የኢጣሊያ ቆንስላ ያደረገው ነገር ነበር።

የታሪክ ምሁሩ ፕሮፌሰር ሪቻረድ ፓንክረስት እ.ኤ.አ በ1990 ዓ.ም ባሳተሙት An Introduction to the Medical History of Ethiopia በሚለው የምርምር ስራቸው ላይ እንደጻፉት፡- በሽታው በውል ያልታወቀ ነበርና ምናልባትም የፈንጣጣ በሽታ ይሆናል በሚል በወቅቱ በኢጣሊያ ቆንስላ ትብብር በሀምሌ ወር 1910 ዓ.ም አስር ሺህ ዶዝ የፈንጣጣ ክትባት ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባ ተደርጎ ነበር። የሆነው ሆኖ ከዘመናዊ ህክምና ጋር ለማይተዋወቀው የኢትዮጵያ ህዝብም ወረርሽኙ ታላቅ መቅሰፍት ነበር። በሽታው ከቁጥጥር ውጪ ወጥቶ በመላው ሀገሪቱ ከባድ ዕልቂት ማስከተል ጀመረ።

ዶ/ር እናውጋው መሃሪ፣ዶ/ር ከንፈ ገበየሁ እና ዶ/ር ዘርጋባቸው አስፋው የተባሉ የህክምና ባለሙያዎች በጋራ ያሰናዱትና በ2013 እ.ኤ.አ የታተመው The Manual of Ethiopian Medical History ላይ እንደሰፈረው፡- የ1918ቱ የእንፍሉዌንዛ ወረርሽኝ ክትባት ለመጀመሪያ ጊዜ የተገኘው በአሜሪካን የቫንደርቢልት ዩኒቨርሲቲ (Vanderbilt University) ምሁራን ሲሆን ወቅቱም በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ነበር።

> **ከሰብዓዊ ውድመቱ ባለፈ ወረርሽኙ በአፍሪካ ከባድ ኢኮኖሚያዊ ቀውስ አስከትሏል። በጊዜው አጠራር ደቡብ ሮዴሺያ (የዛሬዋ ዚምባብዌ) አምራች የሰው ሀይል በበሽታው በመያዙ የወርቅ ማውጫ ስፍራዎች እንዲዘጉ ሆኖ ነበር፡- በዚህም በማዕድን ዘርፍ ላይ የተንጠለጠለው የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ክፉኛ ተጎዳ። ወረርሽኙ በማላዊና በዛምቢያም ያደረሰው ኢኮኖሚያዊ ኪሳራ ከፍ ያለ ነበር። በናይጀሪያም፣በተለይ በደቡባዊ የሀገሪቱ ክፍል በሽታው የከፋ ጥፋት በማድረሱና ምርት በማሽቆልቆሉ፣ ቀድሞ ለምግብነት የማይውለው ካሳቫ ለምግብነት መዋል ጀመረ። በአነስተኛ ጉልበትና ያለ ብዙ ልፋት የሚመረተው ካሳቫ ተመራጭ ምግብ ሆነ**

ከዚያ በኋላ ባሉት ዘመናት በየጊዜው የተሻሻሉ ክትባቶች በምርምር ተገኝተዋል። በ1918 ዓ.ም እንደተከሰተው እንፍሉዌንዛ በወረርሽኝ መልክ ተከስቶ ባያውቅም ዛሬም ድረስ ግን የሰው ልጆች የጤና ፈተና መሆኑን አላቆመም። እ.ኤ.አ በ2012 ዓ.ም ብቻ በመላው ዓለም አምስት መቶ ሺህ ሰዎች በበሽታው ህይወታቸውን አጥተዋል። በዘርፉ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት፡- የእንፍሉዌንዛ ክትባቶች የዋጋ ውድነት መፍትሄ ካላገኘ፣ ህዝቡ ስለ በሽታው በቂ ግንዛቤ ካላገኘ፣ መንግሥታት በሽታውን ለመከላከል ከፍ ያለ ትኩረት ካልሰጡ በእንፍሉዌንዛ ምክንያት የሚከሰተውን ሞት መቀነስ አዳጋች ነው።

የትናንቱን የታህሳስ ወረርሽን ዛሬ ላይ ሆነን ስናስብ ፡- በ1960ዎቹ የተማሪዎች እንቅስቃሴ ከሶቭየት ሕብረት ከአልባንያና ከቻይና ተዳቅሎና እንዳለ ከእነ ኮማው ተኮርጆ እንደ ሕዳር በሽታ ወይም ተስቦ ባሕርና ውቅያኖስ ተሻግሮ የገባው የባዕድ ርዕዮተ አለም ሀገራችንና ሕዝባችንን ካለፉት 50ና60 አመታት ጀምሮ ታማሚ አድርጎ አልጋ እንዳሲያዛቸው እያሰብን ፡- እንደ ሕዳር በሽታ ቀለል ባለ ጉፋንና ትኩሳት ወይም በዩኒቨርሲቲ ግቢ ውይይት ትንተና ስሁት መደምደሚያ ተጀምሮ ለሞት እየዳረገን መሆኑን እያስተዋልን ሊሆን እንደሚገባ ይሰማኛል ።

ወደ ፓርቲ እርዮተ አለም ኀልምሶ ልዩነትን ጥላቻን መጠራጠርን አለመተማመንና መጠፋፋትን ጎንቁሎ የሀገራችንን ህልውና አደጋ ላይ ጥሏል።አሳሯን አብዝቷል። ርዕዮተ አለሙ ይፈታቸዋል ተብሎ ታስበው የነበሩ ችግሮች ሳይፈቱ ይበልጥ ተካረውና ተወሳስበው ባለፉት አምስት አመታት ብቻ ሶስት ጦርነቶችን ቀስቅሶ ኀልቆ መሳፍርት የሌለው ጉዳት በሀገራችንና በሕዝባችን ላይ እያደረሰ ነው።

የሕዝባችንን ጥያቄ ይፈታልናል ብለው ይሄን ርዕዮተ አለም ፕሮግራማቸው ያደረጉ ኃይሎች ለ17 አመታት የትጥቅ ትግል አድርገው ለ27 ገዢ ሆነው ዛሬም ለትግል የተነሱበት አላማ/ኮዝ/ካልተፈታ ትንተናቸውም ርዕዮተ አለሙም ስሁት ነው ማለት ነው።ላለፉት 50ና ከዚያ በላይ አመታት በትጥቅም በፖለቲካ ታግለው ስልጣን ላይ ወጥተው ልሒቃኑ ዛሬም መግባባት ካልቻሉና ከጦርነት አዙሪት ካልወጡ ያንኑ ስህተት እየደገሙ ከሆነ አሁንም ርዕዮት አለሙም ትንተናውም መደምደሚያውም ስሁት ነበር ማለት ነው።

ሀገርንም ሕዝብንም ታማሚ ያደረገው ይሄ ፖለቲካዊ ግሳንግስና ቆሻሻ ሊቃጠልና እንደ ሕዳር ሊታጠን ይገባል እላለ ። እስኪ ሁላችንም ፖለቲካዊ ቆሻሾቻችን ከየቤታችን ወደ አደባባይ አውጥተን እናቃጥላቸው።በምትኩ በአመዱ ላይ ሕዝብን ሀገርንና ትውልድን የሚዋጅ አዲስ ሀገረኛ ፖለቲካዊ ደመራ እንደምር። እዚህ ያላነሳኋቸው ይሄው ስሁት ርዕዮተ አለም የቀፈቀፋቸው ብዙዎቻችን የምናውቃቸው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቆሻሾቻችንንም ማጠን ወይም ማቃጠል አንርሳ ።

ሻሎም ! አሜን።

# ስፖርት





## የአዲስ አበባ ከተማ ዋንጫ በሀዲያ ሆሳዕና አሸናፊነት ተጠናቀቀ

ዓለማየሁ ግዛው



ሀዲያ ሆሳዕናዎች ዋንጫውን ከክብር እንግዳው አቶ ኢሳያስ ጂራ ተቀብለዋል፣

በሰባት ክለቦች መካከል ሲካሄድ ቆይቶ የደረጃና የፍጻሜ ጨዋታዎች በተለያዩ ምክንያቶች ሳይካሄዱ ከወር በላይ ያስቆጠረው 17ኛው የአዲስ አበባ ከተማ ዋንጫ ትላንት በአበበ ቢቂላ ስቴድየም ፍጻሜ አግኝቷል። በዚህም የውድድሩ ተጋባዥ ክለብ ሀዲያ ሆሳዕና በፍፃሜው ጨዋታ ኢትዮጵያ ቡናን በመለያ ምት በማሸነፍ ዋንጫውን ማንሳት ችሏል።

ዳዋ ሆጤሳ በ5ኛውና ተመስገን ብርሃኑ በ13ኛ ደቂቃ ባስቆጠሯቸው ግቦች ሁለት ለምንም ሲመራ የቆየው ሀዲያ ሆሳዕና 27ኛ ደቂቃ ላይ አንተነህ ተፈራ ለኢትዮጵያ ቡና አንድ ግብ አስቆጥሮ የመጀመሪያው አጋማሽ ተጠናቋል። በሁለተኛው 45 ሀዲያ ሆሳዕና ውጤቱን አስጠብቆ ለመውጣት ኢትዮጵያ ቡና ደግሞ የከተማው ዋንጫ ከእጁ እንዳይወጣ ያደረጉት ፉክክር ዘጠና ደቂቃው ሊጠናቀቅ ሁለት ደቂቃ እስኪቀረው ድረስ ግብ አላስተናገደም። 88ኛው ደቂቃ ላይ ግን መስፍን ታፈሰ ለኢትዮጵያ ቡና የአቻነቷን ወሳኝ ግብ በማስቆጠር ጨዋታው ይበልጥ አጓጊ ሆኗል። በመደበኛው የጨዋታ ሰዓት ሁለት አቻ የተለያዩት ሁለቱ የፍፃሜ ተፋላሚዎች ወደ መለያ ምት አምርተዋል። በዚህም ሀዲያ ሆሳዕና ለጥቂት ከእጁ የወጣውን ዋንጫ በመለያ ምት 5ለ4 አሸንፎ መልሶ ማግኘት ችሏል። ሁለት ጊዜ ዋንጫውን የማንሳት ታሪክ ያለው ኢትዮጵያ ቡና ለሦስተኛ ጊዜ አሸንፎ ከኢትዮ ኤሌክትሪክ ጋር የሚስተካከልበትን እድል ሳይጠቀም ቀርቷል።

የፍፃሜ ጨዋታውን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶች እና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ አቶ በላይ ደጀን፣ የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት አቶ ኢሳያስ ጅራን ጨምሮ የፌዴራል እና የከተማ አስተዳደሩ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች አስጀምረውታል። ሻምፒዮናው ሀድያ ሆሳዕና ዋንጫው እና የወርቅ ሜዳልያውን ከዕለቱ የክብር እንግዳ ከአዲስ አበባ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ አቶ በላይ ደጀን እጅ ተቀብለዋል።

ቀን 7፡00 ሰዓት ላይ ቅዱስ ጊዮርጊስን ከኢትዮጵያ መድን ያገናኘው የደረጃ ጨዋታ በፈረሰኞቹ 2ለ0 አሸናፊነት ተጠናቋል። በአህጉር አቀፍ ውድድር ተሳታፊ በመሆናቸው በተስፋ ቡድን በከተማው ዋንጫ የተሳተፉት ፈረሰኞቹ በምድቡ የመጀመሪያ ጨዋታ በኢትዮጵያ መድን በሰፊ የግብ ልዩነት ቢሸነፉም አገግመው በግማሽ ፍጻሜ በኢትዮጵያ ቡና እስከ ተሸነፉበት ጨዋታ ድረስ ተፎካካሪ መሆን ችለዋል። በደረጃ ጨዋታውም ተፎካካሪ በመሆን ኢትዮጵያ መድንን በመርታት ሦስተኛ ደረጃን በመያዝ ውድድሩን ፈጽመዋል። የፈረሰኞቹን የማሸነፊያ ግቦች ሰለሞን ታደሰ እና ሄኖክ ዮሐንስ በ43ኛው እና በ68ኛው ደቂቃ ማስቆጠር ችለዋል። የጨዋታው ኮከብ ተጫዋችም የቅዱስ ጊዮርጊሱ የአብስራ ተስፋዬ ሆኖ የተመረጠ ሲሆን የክሪስታል ዋንጫ እና የ10ሺ ብር ተሸላሚ ሆኗል።

ከመስከረም 07/2016 ጀምሮ በተካሄደው 17ኛው የአዲስ አበባ ከተማ ዋንጫ ሰባት ክለቦች በሁለት ምድብ ተከፍለው የተፋለሙበት ሲሆን በምድብ ሀ ኢትዮጵያ ቡና፣ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ ሀድያ ሆሳዕና እና ሻሸመኔ ከተማ፤ በምድብ ለ ያለፉት ሁለት ተከታታይ የፕሪሚየር ሊግ ዋንጫ አሸናፊው ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ ተጋባዡ አዳማ ከተማ እና ኢትዮጵያ መድን ተደልድለው እንደነበረ ይታወሳል።

የአዲስ አበባ ከተማ ዋንጫ ባለፉት ዓመታት በርካታ ክለቦችን እያፋለመ ሲካሄድ የቆየ ሲሆን 4 የከተማዋ ክለቦችም ዋንጫውን ማንሳት ችለዋል። ዋንጫውን ስድስት ጊዜ በማንሳት ቅዱስ ጊዮርጊስን የሚስተካከል ክለብ የለም። ከፈረሰኞች በመቀጠል ኢትዮ ኤሌክትሪክ (የቀድሞው መብራት ኃይል) ዋንጫውን ሦስት ጊዜ በማንሳት ይከተላል። እአአ በ2014 ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዋንጫውን በማንሳት የውድድሩ አዲስ ሻምፒዮን እንደነበር ይታወሳል።


# የሕዝብ ማስታወቂያ

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት በኦሮሚያ ክልል በልቱ፣ በሂማ፣ ሚኖ ቀበሌዎች፣ በአማራ ክልል ባንባሆና ዋሰል ቀበሌዎች፣ በጋምቤላ ክልል ኡንጉጌ ቀበሌ፣ በቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል አልባሳ ቀበሌ፣ በደቡብ ክልል ቱምና ኦሞራቴ ቀበሌዎች፣ በሶማሌ ክልል ቆራሌ፣ ገለህሙር ቀበሌዎች፣ በአፋር ክልል ኩስሬዋድ ቀበሌ ፣ ለሚያካሂደው ከግሪድ ውጭ ከፀሐይ ኃይል ኤሌክትሪክ ማከፋፈልና መሸጥ የኤሌክትሪክ ንግድ ስራ ፈቃድ እንዲሰጠው ሚያዝያ 11 ቀን 2015 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ጠይቋል፡፡ ስለሆነም የኤሌክትሪክ ንግድ ስራ ፈቃዱ መሰጠቱን የሚቃወም ይህ የሕዝብ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ 10 ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ ከነምክንያቱ፡-

- ስነዳጅና ኢነርጂ ባለስልጣን - አዲስ አበባ

በግልጽ ማንነቱን የሚገልጽ መታወቂያ ይዞ በመቅረብ ተቃውሞውን በጹሑፍ እንዲያቀርብ በአነስተኛ ግሪድ መመሪያ ቁጥር 268/2013 አንቀጽ 10 (4ሐ) መሰረት ይህ የሕዝብ ማስታወቂያ ጥሪ ተደርጓል፡

ፓ.ሳ.ቁ 2554

ስልክ ቁ. 251-0115507733/35/52/54

www.Pea.gov.et

## ነዳጅና ኢነርጂ ባለስልጣን